«ቤታ ዙሪያዉ ገደል እጥሩ በዘበኛ፣

ጨነቀኝ ጠበበኝ ያንተው መገናኛ፡፡»

ከወህኒ ቤቱ ከባድ ዝምታ በላይ ነግሶ የሚሰማው የዋጋ ከፍያለዉ ዘፈን ነው፡፡ የባታ ወህኒ ቤት አጥር ከጥርብ ድንጋይ የተገነባ ነው፡፡ ከአጥሩ በላይ ጉብ ያለው ማማ እታች ሆነው ሲመለከቱት ሰማይን ደገፎ የቆመ ይመስላል። ማማው ላይ መትረየስ ደግነው የሚጠብቁት ወታደሮች ጠርብ--ጠርብ ያከከላሉ፡፡ ዝንብ በአጠገባቸው የሚያልፍ አይመስልም፡፡ ያስፈራሉ፡፡ የእስረኛው እዝነ ልቡና ግን ይህን ሁሉ ከባድ ጥበቃ ጥሶ ወደ ውጭ ዘልቋል። የዋጋን ዘፈንና ሙሾ በጸጥታ ያዳምጣል፡፡ በዐይነ ህሊናው ይመለከታታል። የውጭውን አየር እየናፋቀ---እየጓጓ---አንዳንዴ በተስፋ!--ሌላ ጊዜ ያለተስፋ!... ትሩፋትና ራሔልም የባታ ወህኒ ቤት ሰሰባ ሆነዋል፡፡ እንደ ሌሎች እስረኞች ሁሉ እነሱም የታሪከኛዋን እብድ የዋጋን ዘፈን በሩቁ ማዳመጣቸውን ቀጥለዋል፡፡

ዋጋ እንዲህ እንደ አሁኑ የእብዶችን ጎራ ሳትቀላቀል የፋሲለደስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበረች፡፡ በፍቅር እቅፍ ውስጥ ሳትወድቅም የከፍሏ ተፎካካሪ ተማሪ ነበረች፡፡ ፍቅር አደባባይ አውጥቶ ጉድ እስከ ሰራት ጊዜ ድረስም እንገቷን የደፋች ዐይን አፋር እንደ ነበረች በስፋት ይነገርላት፡፡ መከብብ አበጀን ወዳ እጅ ለእጅ ተያይዛ በአደባባይ ስትከንፍ ግን «ትንቢተኛዋ ጃንተከል ዋርካ ጉድ ሰራቻት፡፡ ንግርቷ ደርሶ ዋጋን ገሀድ ወጣቻት፡፡ በአደባባይ አጋለጠቻት» ተብሎ በጎንደር ኗሪ ሁሉ ብዙ ተወርቶባታል፡፡

ከፋሲል ግንብ ወረድ ብሎ የአራዳን መንገድ ተከትለው ሲሄዱ እድሜ ጠገቧና ታሪከኛዋ ጃንተከል ዋርካ ትገኛለች፡፡ አፄ ፋሲል እንዳስተከሏት ይነገርላታል፡፡ ጃንተከል (ጃንሆይ የተከሏት) እንደ ማለት ነው፡፡ የዘመንን እሻራ ይዛ ይኸው ዛሬም ትኖራለች፡፡ ዘመንን ተሻግራ ሰመኖር ነገን በተስፋ እየተመለከተች እንደ ቆመች አለች፡፡ ከጥንት ጀምሮ ቅርንጫፏ ተንዘርፍፎ መሬት ሊነካ የደረሰ ይመስላል እየተባለ ይነገራል፡፡ ዛሬም ያው ነው መሬት ሊነካ ጥቂት የቀረው ይመስላል፡፡ ከዱሮ እንስቶ ኗሪዉ ከፀሐይ ቃጠሎ ይጠለልባታል፡፡ ሲደከመው ጥላዋ ስር አረፍ ብሎ ትንፋሽ ይወስድባታል፡፡ አዛውንቶች ተሰባስበው ያሰፈ ትዝታቸውን እያወጉ ይዝናኑባታል፡፡

ከዚህ ሁሉ ባሻገር ግን ጃንተከል ዋርካ የጎንደርን ኗሪ ሁሉ ስጋት ላይ ጥላው ትኖራለች፡፡ የሚዝናናባትን ያህል--- ጥላ ማረፊያ የመሆኗን ያህል--- የኋላ ዘመን ታሪክ የሚዘከርባትን ያህል--- መሽቶ በነጋ ቁጥር ደግሞ በጥርጣሬ ዐይን ሲያስተውላት ይኖራል....

የጃንተከል ዋርካ መሬት የነካች እለት፣

ሴቱ ወጣ ወጣ ወንዱ ከትት ከትት፡፡

የጃንተከል ዋርካ መሬት ስትነካ፣

ወንዱ እንቢ እንቢ-- ሴቱ እንካ እንካ፡፡

እየተባለ ከጥንት ጀምሮ ሲነገር ይኖራል፡፡ የዋርካዋ ቅርንጫፍ መሬት የነካለት ሴት የሆነች ሁሉ ዐይነ ጥላዋ ይገፈፋል፡፡ እንገቷን መድፋቷ ይቀራል፡፡ ዐይናፋርነቷ ይጠፋል፡፡ እንደ ጥንተ-ጧቱ ወግና ልማድ በስንት ልመናና አማላጅነት መገኘቷ ቀርቶ ራሷው እፍ አውጥታ ወንድ ትጠይቃለች፡፡ ወንድ ትለምናለች፡፡ የሴትነት ከብሯን ሽጣ ትበላለች፡፡ እየተባለ ምንጩ ያልታወቀ አፈ-ታሪክ ይተረካል፡፡ ትንሽ ትልቁ በአጠገቧ ባለፈ ባገደመ ቁጥር ገልመጥ ገልመጥ እያለ ቅርንጫፍ ቅርንጫፏን ሳያስተውል አይሄድም፡፡ በተለይ የሴት ልጅ ወላጅ የሆነን የጎንደርን ኗሪ ሁሉ ስጋት ውስጥ ከታው ትኖራለች፡፡ እንዳንዱ የጠናበት እባት ደግሞ ሌሊት ሌሊት እየተደበቀ መሬት ሊነካ የተንዘረፈፈውን ቅርንጫፏን ሲከረከም ያድራል እየተባለ ሀሜቱ ውስጥ ውስጡን ይወራል፡፡ ይኸው ስንት ዓመት ሙሉ ቅርንጫፏ መሬት ሊነካ የደረሰ ይምሰል እንጂ እንድም ቀን መሬት ነክቶ እየሁ የሚል የለም፡፡ እድሜ ጠገቧ ጃንተከል ዋርካ ዛሬም እስከ ከፉ ንግርቷ ለታሪክ ምስከርነት እንደ ቆመች አለች፡፡

ዋጋና መከብብ በጓደኞቻቸው «ከተፋቀሩ አይቀር እንዲህ ነው እንጂ-- አጹብ ድንቅ ፍቅር!» ተብሎ ተደንቆላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍቅራቸው አደባባይ ወጥቶ የጎንደርን ኗሪ ሁሉ «እቤት ጉድ! ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም!» አሰኝቷል፡፡ በየጠጅ ቤቱ በአፈ ድስት ብርሌ ጠጁን እየጠጣ የዋጋንና የመከብብን የአደባባይ ፍቅር የአንድ ሰሞን የወሬ ማማሚቂያ አድርጎት ከርሟል፡፡ ዋጋን የሴት ዐይን አውጣ ብሎ አውግዞ ኮንኗታል፡፡ አሳዳጊ አክስቷ ሳይቀር ከፉ ጠብ ተጣልተዋት ነበር፡፡

«አሳፍረሽኛል! ቀጥቼ እንዳላሳደግሁሽ ሁሉ እንገቴን አስደፍተሽኛል፡፡ የሰፈር ቡና ማጣጫ አድርገሽኛል፡፡ በየመሸታ ቤቱ ስሜን አስነስተሽዋል፡፡ ባልወልድሽ ነው-- ማጠኔ ባያፋራሽ፡፡ ዐይንሽን አልየው፡፡» ብለው ከቤታቸው አስወጥተዋት ነበር፡፡ በጎረቤት አማላጅነትና በስንት ልመና ነው መልሰው ያስገቧት፡፡

መከብብ ራሱ ስንት ፈተና ተቀብሏል፡፡ በዋጋ የተነሳ ከስንት ጎረምሳ ጋር ቦክስ ገጥሟል፤ ጩቤ ተማዟል፡፡ ዋጋ ቆንጆ ናት፡፡ ባህር ዳርቻ ላይ ብቻዋን እንደ በቀለች ጥንቅሽ መለሎ! አየቀኑም ቢሆን ሴቶች እንኳ ሳይቀሩ የመሰከሩላት እዚህ ላይ ቀረሽ የማትባል ልቅም ያለች ቆንጆ!

መከብብ ፀረ አብዮተኛ ተብሎ ባታ ወህኒ ቤት ሲወርድ የጎንደር ሰው ሁሉ ያዘነው ለዋጋ ነበር:: ፍቅራቸው እደባባይ ወጣ ተብሎ በተለይ እሷን «ዐይን ይብላሽ» እንዳላላት ሁሉ አሁን መከብብ ሲታሰር ደግሞ «ያችን ልጅ ምን ሊውጣት ይሆን? እንዴት ልትሆነው ነው?» ብሎ ያላዘነላት አልነበረም::

አክስቷ «ዐይንሽን አልየው» ብለው አንዳላባረሯት ሁሉ በለቅሶ ብዛት እንደ ጨው ሟሙታ እንዳታልቅ ሰጉ:: እንደ ተባለውም ዋጋ የምትይዘውን የምትጨብጠውን አጣች:: እንብታ አልበቃት አለ:: ጧት ማታ መገኛዋ ባታ ወህኒ ቤት ሆነ:: በደርግ ሰላዮች ጥርስ ውስጥ ገባች:: የኋላ ኋላ የፀረ-አብዮተኛነት እጣ ለሷም ደረሳት:: ባታ ወህኒ ቤት ወረደች::

ለዋጋ መታሰር ምክንያቱ መከብብ ነው ተባለ:: ለእሱ መያዝ ጦስ የሆነው ደግሞ የአንድ የደርግ ከፍተኛ ባለስልጣን ሞት ነበር:: ለመከብብ ብቻ ሳይሆን ለብዙ የጎንደር ወጣቶች ያች ቀን የእስር፣ የሞትና የሰደት ጥሪ ነበረች:: ሟች በጠራራ ፀሐይ ሲኒማ እዳራሽ ፊት ለፊት ጫማውን ያስጠርጋል:: መኪናው ትንሽ ፈቀቅ ብላ ቆማለች:: ጃርባውን ለሱቆቹ ግድግዳ ሰጥቶ ከጎኑ የሻጠውን ሽጉጥ አስር አስር ጊዜ እየነካካ አካባቢውን ባለማመን እየተገላመጠ ይመለከታል:: በጥንቃቄ ራሱን ይጠብቃል:: ጫማ ጠራጊው ትንሽ ልጅ

«ጋሼ ሰንት ሰዓት ነው?» ብሎ ከመጠየቁ ማን እንደ ተኮሰው ባልታወቀ ጥይት ባለስልጣኑ ሰው ግንባሩ ላይ ተመትቶ ሲወድቅ አንድ ሆነ:: እንደ ተቆረጠ ግንድ ዘፍ ብሎ ሲወድቅ በአካባቢው የነበረ ሰው ሁሉ ቀበሮ እንደ ገባበት በግ በረገገ:: ሁሉም ወደ አገኘው አቅጣጫ የነብሰ እውጭኝ ሩጫ ተፈተለከ:: ሊስትሮው ከመቼው እቃውን ሸክፎ አካባቢውን ጥሎ ሲጠፋ ፍጥነቱ ከዐይን ቀድሟል:: ፒያሳ ቀውጢ ሆነች:: ማን አባራሪ ማን ተባራሪ እንደ ሆነ አይታወቅም:: ሁሉም ይሮጣል:: ሁሉም ይሸሻል:: ያን ቀን ወታደሮቹ ለየላቸው:: ያገኙትን ወጣት ሁሉ በጅምላ በሰደፍ እያዳፉ መያዝ---ማፈስ ብቻ ሆነ :: በእያንዳንዱ ኗሪ ቤት እየገቡ ፈተሹ---መነጠሩ::

«ልጄ ከምንም ነገር የለበትም አላሰወሰድም» ብላ ለልጁ የተሟገተች እናት በግፍ በሰደፍ ተቀጠቀጠች---ተረገጠች---ተዋረደች:: ከልጆቻቸው ጋር ለጥቂት ቀን የታሰሩ እናቶችም ነበሩ::

መከብብ የታሰረው በዚህ ክፉ ቀን ነበር:: አንድ ለናቱ ነው---ብቸኛ ልጅ:: ጠላ ሸጠው ያሳደጉት:: አባቱ በልጅነቱ ነው የሞቱበት:: እንደ ህልም--እንደ ህልም ነው ትንሽ ትንሽ ትዝ የሚሉት:: እናቱ እንደ ነገሩት ከሆነ ጠንካራ ሠራተኛ ነበሩ::

«አበጀ የሰራው ቤት የእድሜ ልክ ነው:: ግንብ ያሰንቃል» እስኪባል ደረስ የተመሰከረላቸው እናጢ:: እንደ ተለመደው አንድ ቀን የእለት ሥራቸውን ለማከናወን ማልደው ነበር ከቤት የወጡት:: ሥራ ቦታ እንደ ደረሱ ላብ በጠገበች የቆዳ ኮርጇቸው

የተለያየ ቁጥር ያለቸው ምስማሮች ሞልተው ጣራ ሊያዋቅሩ በመሰላል ይወጣሉ:: ወራጅና ማገር ለማያያዝ ገና አንድ ሁለት ምስማር መምታታቸው ነበር:: ድንገት ሳያስቡት ሚዛናቸውን ሳቱ:: እግራቸው ተንሸራተተ:: ከላይ ከጣራ እንስተው ክፉ አወዳደቅ ወደቁ:: ታመው አልጋ ያዙ:: የሚጓጉለትን አንድያ ልጃቸውን ሳያሳድጉ በተኙበት ቀና ሳይሉ ቀሩ:: እናቱ ወ/ሮ ወሰኔ

«ከአበጀ ወዲያ ወንድ እርም ይሁንብኝ» ብለው በብቸኝነት ተቀመጡ:: ሰንቱ ለሚስትነት ቢመኛቸውም እሳቸው ግን አንድያ ልጃቸውን «የእንጀራ አባት ዐይን አይገርፈውም:: ሆዱን አይገምተውም» ብለው ጠላ እየሸጡ ብቸኛ ልጃቸውን በብቸኝነት አሳደጉ:: እንዲህ የባሰው ነገር ሊመጣ በዋጋ ሰበብ እንዱ በጩቤ ወግቶ እንዳይገለው ሲሰጉ ውለው ሲሰጉ ያድሩ ነበር:: ካጠገቧ እንዳይደርስ መክረውታል:: ለምነውታል:: ዋጋን እስጠልቶ አንዲለያይላቸው ለእርባ እራቱ ታቦቶች ተስለዋል:: ስለታቸውን የፍቅር አምላክ ሳይሰማው ቀረ እንጂ:: ቢጨንቃቸው

«ያጠባ ጡቴን እሸቼ እረግምሃለሁ» እስከማለት ደርሰው አስፈራርተውት ነበር:: የማይሆን ሆኖ ሲያገኙት

«እንግዲህ ምን አደርጋለሁ? እንተን ደስ ታለችህ እንደ ወደድካ ልጄ አትሳቀቅ:: ግን አባክህ መከብቤ በአባትህ አጥንትና በእጠባ ጡቴ ይዠሃለሁ እጅ ለእጅ ተያይዞ አደባባይ ለእደባባይ መዞር ይቅርባችሁ:: ከሰው ዐይን መግባቱ ደግ አይደልም::» ብለው መክረውታል::

መከብብ በፀረ-አብዮተኛነት ተፈርጆ የተያዘው ከቤቱ ነው:: በአጋጣሚ እናቱ ቤት ውስጥ አልነበሩም:: ጠላ ሸጠው--ከትንሹ ትንሽ--ከትልቁ ትልቅ ሆነው--በብቸኝነት ያሳድውጉት ብቸኛ ልጃቸው በቅልብ ወታደሮች ሲቀጠቀጥ-- ከምርመራ ጣቢያው አላደርስ ብሏቸው እንዲያ ባፍ ባፍንጫው የደም ጎርፍ እሰኪ ወርድ እየደበደቡ-- በሰደፍ እያዳፉ ሲወስዱት አንኳንም አላዩ:: ጎረቤቶቹ እንኳን ያሳደጉት ልጅ በጨካኞች እጅ ግብቶ እንደ እባብ ሲቀጠቀጥ አላሰችል ብሏዋቸው በየደጃፋቸው ቆመው በአንባ ተራጭተውለታል:: ከማልቀስ የዘለለ ምንም ባለማድረጋቸው እያዘኑ-- እየተቆጩ---

እናቱ አገር አማን ነው ብለው ከዋሉበት ውለው ሲመለሱ ጎረቤቱ ሁሉ ለመናገር ተፈራርቶና ተጨንቆ እንዲሁ መንቆራጠጥ ብቻ ሆነ። በኋላ ተመካክረው በዘዴ ቡና አቤታቸው እንዲያፈሉ አደረጓቸው:: ቡናው ላይ ሁሉም ተሰባሰበው የባጥ የቆጡን እያወሩ አብረዋቸው ሲጫወቱ አመሹ። የወይዘሮ ወሰኔ ልብ ግን እልተረጋጋም:: ቡናውም ላይ---ወሬውም ላይ አልነበረም:: አሁንም አሁንም ውጭ ውጭውን ይመለከታሉ:: ቢድናቸው ብቻ ነው አቤት ውስጥ ያለው:: ለይተው ያላወቁት እንዳች ነገር

መንፋሳቸውን ረብሾታል:: ነፍሳቸው እንደ ተጨነቀች ማንም እይቶ ይናገራል:: ከጎረቤቶቹ በእድሜ ገፋ ያሉት እዛውንት ቀስ ብለው ለመናገር ዳር ዳር እሉ::

«መከ ---መከ» ሸማግሌው ጎረቤት ያሳደጉትን ልጅ ስም መጥራት እልሆንላቸው ብሎ ተንተባተቡ::

«እ! ምን አሉኝ!? መከብብ ምን ሆነ? ልጄ ምን ሆነ አሉኝ?» የመከብብ እናት በተቀመጡበት ውሃ ሆኑ::

«ኧረ ቀስ በይ ወሰኔ! አሁን ምን ሆነ ስል ሰማሽ? እሉ አዛውንቱ የሚያደርጉት ጠፍቷቸው እሳቸውም እየተርበተበቱ::

«ልጄ በጤናውማ አይደለም:: እስካሁን ምን ያስመሸው ነበር? የኔን የናቱን አንጀት ሲያውቀው» እሉ የመከብብ እናት እቅላቸውን እንደ መሳት እያደረጋቸው::

«ወሰኔ እንግዲህ አንድ ጊዜ እሱ ካመጣው ጠንከር ብሎ.....» አዛውንቱ ጎረቤታቸው ገና ተናግረው ሳይጨርሱ

«ም--ን! ምን-- አሉኝ!? መከብብ-- ምን ሆነ ነው ያሉኝ!?» ብለው በተቀመጡበት ወደ ኋላቸው ዝልፍልፍ ብለው ፍንግል አሉ:: እፋፍሰው አነሷቸውና ወስደው አልጋ ላይ አጋደሟቸው::

«ፀበል! ቶሎ በሉ ፀበል!» እሉ አዛውንቱ በድንጋጤ ዐይናቸው ፈጦ:: በየቤቱ የመጣው የሚካኤል---የገብርኤል ---የማርያም.....ፀበል ሁሉ ተረጨላቸው:: የእርባራቱ ታቦት ፀበል አንድ አልቀረም:: ከሁሉም ቤት እየመጣ ልብሳቸውና የተኙበት ብርድልብስ እስኪ ርሰ ድረስ ጠመቋቸው:: ወይዘሮ ወሰኔ ግን ንቅንቅ አላሉም:: እያ ሞት እጅሬ ከንፉን ዘርግቶ ተቀብሏቸዋል:: የወ/ሮ ወሰኔ ነገር አበቃ!! የሚንሰፈሰፉለትን የአንድ ልጃቸውን መጨረሻ ሳያዩ---የልጅ ልጅ መሳም እንዳማራቸው ይችን ዓለም--- እስከመጨረሻው ላይመለሱባት ሄደዋል::

******

መከብብ ከምርመራው ቦታ ሲደርስ ተዳከሞ ነበር። ቀድመውት የመጡ ብዙ ወጣቶች እንደ እሱ የደም አላባ ተነክረው አያቸው:: ወንዶች ከተቀመጡበት ትይዩ ሴት እስረኞችም ተኮልኩለዋል:: እንደ ወንድሞቻቸው ደም በደም እስኪሆኑ ተቀጥቅጠዋል:: በተለይ እንደኛዋ ወጣ ካለው ግንባሯ ላይ የሚወርደው ትኩስ ደም ፊቷን አልብሶታል:: ደሟ አልቆ እንዳትሞት ያሰጋል:: ተዝለፍልፋ መሬት ላይ ወድቃለች:: ሌሎቹ ሴት እስረኞች እንዳይረዷት ተከልክለው በጭንቀት ዐይን ዐይኗን ያዩዋታል:: የሚደንቀው ነገር ግን

ከሁሉም ወጣት ፊት ላይ ቆራጥነት ይነበባል:: መከብብ ወጣቶቹን ገና ሲያያቸው ነበር ለእሱም የተጋባበት ይመስል የልብ ልብ የተሰማው:: ድካሙ ሁሉ ለቀቀው፤ ስቃዩ ተረሳው:: ሁሉም ሳይነጋገሩ ይግባባሉ «የትግሉ ነው ሕይወቴ....» የሚለውን መዝሙር በልባቸው ይዘምራሉ::

«እሱን እስገባው! ጥጋብ የወጠረው ልቡ ይተንፍስ:: ያበጠ ትከሻው ሲሟሸሽ አብዮት ቀርቶ ቂጣ ለመገልበጥ አያስብም» አለ መከብብን እየተመለከተ:: ሌሎቹ ወታደሮች ተሳሳቁ:: መከብብን የሰደበውና የገላመጠው ወታደር ጥቁረቱና ወዙ ኑግ ልጥልጥ አስመስለውታል:: ጠቅሰል ጠቅሰል ያደረገው ቅጠል አረንጓዴ ዩኒፎርሙ የእጅ ጠንቿውን ፍጥ-ርቅ አድርጎ ይዞት የጠበበው ይመስላል:: መከብብን በስደፍ እየጎሻሸሙና እያዳፉ ለማይቀረው ምርመራ ይዘውት ገቡ:: ከፍሉ በቀን ሆኖ እንኳ ጨላማ ነው:: አንደኛው መርማሪ ሙብራት አበራ:: ርቃ የተሰቀለችው እምፖል ጭል ጭል እንደሚል ኩራዝ በቂ ብርሃን አትሰጥም:: በተለይ ከውጭ ለሚገባ ሰው ነፍስን ያስጨንቃል:: በየቦታው በደም የተነከረ ቁርጥራጭ ጨርቅ ወዳድቋል::

ወለሉ በደረቀ ደምና በትኩስ ደም ጨቅይቷል። የከፍሉ ሽታ ውስጥ ሳይገቡ ገና በር ላይ ይገፋተራል:: ያው ጡንቻማ ወታደር ገፍትሮ ወደ ውስጥ ወረወረው:: ተፍገምግሞ ባፍጢሙ ተደፋ መከብብ:: ብዙ እጆች ተረባረቡበት:: «ገልብጠው!» አለ ያው ፈርጣማ ወታደር:: ሙቼም ከመጀመሪያው ነው ጠምዶ የያዘው:: በኤሌክትሪክ ገመድ አንዱ ገራፊ ሲደከመው ሌላው እየተተካ እየተፈራረቁ ወረዱበት:: በጩኸት ስቃዩን እንዳያስታግስ እንኳ ያ በደም የተጨመላለቀ ቁርጥራጭ ጨርቅ ተሲቃቅሞ አፉ ውስጥ ተጠቅጥቋል:: ከንዳቸው እስኪዝል ገረፉት:: ራት ለመብላት ሲሄዱ ሁሉ በሁለቱ ጠረጴዞች መካከል በተጋደመው ግንድ ላይ እጅ እግሩ ታስሮ እንደ ዶሮ ተዘቅዝቆ «ወፌላላ» እንደ ተሰቀለ ነበር::

ከእራት በኋላ ተዝናንተው በአዲስ ጉልበት ተመልሰው መጡ:: በእነሱ እምነት ይሞታል ብለው ነበር:: ሰው ያን ያህል ተገርፎና እንደ ዶሮ ተዘቅዝቆ ለብዙ ሰዓት ይቆያል ብለው አልገመቱም:: ፈርሰና ደም ተፍቶ እንደ ሚሞት እርግጠኞች ነበሩ:: መከብብ አፉ ውስጥ የተጠቀጠቀውን ጨርቅ እንደ ምንም በምላሱ ገፍቶ በአንድ በኩል አየር ማግኘት ችሎ ነበር:: እስትንፋሱ አልቆመችም፤ ግን ነገር አለሙ ዞሮበት ሁሉን ነገር ረስቷል::

«እስከአሁን በሕይወት ይኖራል ብለህ ነው? እስቲ ትንሽ ጣል ጣል አድርግበትና ሞክረው» አለ ያው ወጣምሻ በወዝ የተንጨፈጨፈ ወታደር:: ጥላቻው ውሎም አልበረደለትም::

አንድ ሁለት ጊዜ ከጠበጠቡት በኋላ አውርደው እጅና እግሩን ፈተው ወለሉ መሀል እንደ ጉማጅ ግንድ ዘፍ አድርገው ጣሉት:: ያ ነገረኛ ወታደ ምራቁን ተፋበት:: በሩን እላዩ ላይ ዘግተውበት እየተሳሳቁ ሄዱ:: መከብብ ስቃዩ የታወቀው ጧት ላይ ነበር:: ከብርዱ ጋር

ተንሰፈሰፈ:: ወደ አዕምሮው ሲመለስ ሁሉም ነገር ወለል ብሎ ታየው:: መታሰሩን ሲሰሙ እናቱና ዋጋ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ማሰብ አስፈራው:: ከአዕምሮው ለማስወጣት ቢሞክርም ተራ በተራ እየመጡ ሰንቅር ይሉበታል:: ይባስ ስቃዩን አበዙበት:: በር ደንገት ተከፈተ::

«ሊጅሬው እስከ አሁን አለህ አልሞትክም!? እንደ ድመት ጠንካራ ነፍስ ነው ያለህ በል! ከግማሽ ቀን ያላነሰ እንደ ብቅል ተዘቅዝቀህ ውለህ አሁንም ትተነፍሳለህ:: ጥሩ በልተሻል ማለት ነው:: ቆይ! ለሁለተኛ ዙር እንገኛለን!»

«ሽሮ ዝቀህ ልብህ ሲያብጥ ጊዜ እንደ እናትህ ቂጣ መስሎህ መንግሥት ልትገለብጥ ተነሳህ:: ግድ የለም ከዚያ ሁሉ ዱላ በኋላ አሁን በሕይወት መገኘትህ ለኛ የሚበጅ አንድ ነገር ቢኖር ነው:: ትናንት ያየኸው ቅምሻ ነው:: ዛሬ ዋናው ይጀምራል:: ዐይንህ እያየ ስጋህ ተከትፎ ከማለቁ በፊት በሰላም የምታውቀውን ምሥጢር ሁሉ ብታወጣ ይሻልሃል» አለው እጁን ከኪሱ ውስጥ ከቶ ቁልቁል በንቀት እየተመለከተው::

«የሽሮ ድንፋታዉ ውሃ እስኪገባበት ነው:: የአናርኪስት ድንፋታው ደግሞ ከእኛ እጅ እስኪገባ ነው:: ትሰማለህ! ዲስፐሊን --ምናምን እያልክ ብትገግም የምታተርፈው ስቃይ ብቻ ነው:: ጠንካራ የተባሉት ጓዶቻችሁ ሳይቀር መጨረሻ ላይ ያልተጠየቁትን ሁሉ ነው የሚወሸክቱት:: ከንቱ ላይቀርልህ አጉል ስቃይህን አታብዛ:: የምታውቀውን ሁሉ ተናግረህ በሰላም ብትኖር ይሻልሃል:: ሁሉንም ሳትደብቅ የምትናገር ከሆነ ያው ወንበሩ ላይ ተቀመጥ» አለው ወረቀትና እስከርቢቶ እያዘጋጀ::

«መጀመርያ የታሰርኩት ምን ስላደረኩ ነው? ምን ወንጀል እንደ ሰራሁ እኮ አላወቅሁም:: ከቤቴ ይዛችሁ አመጣችሁኝ:: ምንም ጥያቄ ሳልጠየቅና ጥፋቴ ሳይነገረኝ እኮ ነው ይህ ሁሉ ድብደባ የደረሰብኝ» አለ መከብብ በደከመ ድምጽ:: እጅና እግሩን ለማንቀሳቀስ ሲሞክር ይህ ነው የማይለው ስቃይ እየተሰማው::

«ይችን ይወዳል ሰውየው!! እስከዚህም ደፋር ነሽና! እውነትም ያበጠ ልብ ነው ያለሽ! እ! የማነሽ ወጠጤ አባክሽ!? ቆይ ልክ ትገባልህ:: ዐይንህን በጉጠት ነው የምናወጣው:: እየሰማህ ነው ቆዳህን የምንገፈው:: እናርኪስቷ ኢሕአፓ ደርሳ ስታስጥልህ እናያለን!» አለው ወታደሩ ተናዶ:: ዝቶም አልቀረ እያረፈ እየተነሳ ቀጠቀጠው:: መከብብ የሰው ልጅ ይችለዋል ተብሎ የማይታሰብ ስቃይ ተቀበለ:: ሬሳው ማለት ይቻላል ባታ ወህኒ ቤት ተወስዶ ከመሰሎቹ ጋር የተወረወረው:: እስር ቤት ያሉ ጓዶች የተለየ እንክብካቤ ባያደርጉለት ኖሮ ወዲያው ሟች ነበር:: ለሽንት የሚሄደውና የሚቀመጠው በድጋፍ ነው:: ውጭ መውጣት ስለማይችል ስንቅና ልብስ ማንኛቸው እንደሚያቀብሉት አያውቅም---- እናቱ ይሁኑ ዋጋ?

በየክፍሉ የታሰሩ እስረኞች የተለያዩ ኮሚቴዎችን አቋቁመው ጊዜውን ያለጭንቀት ለማሳለፍ ይጥራሉ:: የመዝናኛ ኮሚቴ፣ የተጎዱ እስረኞችን ተንከባካቢ ኮሚቴ፣ የትምህርት--- የጤና---የስፖርት --የምግብ ኮሚቴ.... የመሳሰሉ:: ሌላው ጥሩ ነገር በፖለቲካ እስረኞች መካከል ስንቅ የሚመጣላትና የማይመጣለት እስረኛ ተብሎ ልዩነት አይደረግም:: ከየቤቱ መጣው ምግብ ሁሉ አንድ ላይ ተሰብስቦ በኮሚቴው አማካኝነት እኩል ይከፋፈላል:: የህክምና ሙያ ያላቸው እስረኞች ደግሞ እንደ መኩብብ የተጎዱ እስረኞችን ልዩ እንክብካቤ ያደርጉላቸዋል:: እርስ በርስ የሚያደርጉት መተዛዘንና መደጋገፍ ጠባቂ ወታደሮችን ሳይቀር ያስቀናል::

ዋጋ በእስረኛ መጠየቂያ ጊዜ መከብብን ልትጠይቀው ስትመጣ ጥቁር ልብስ አለበሰችም:: ነጠላ አላዘቀዘቀችም:: ድንገት ቢያያት እንዳይደነግጥ አስባ ነበር:: እሱም ግን መውጣት አይችልም:: ምርመራው ገና ሰላላለቀ ከውጭ ሰው ጋር መገናኘት አይፈቀድለትም:: ያም ባይሆን ራሱን ችሎ መራመድ ስለማይችል ከክፍሉ አይወጣም:: ስንቅና ልብሱን አቀብላ በእንባ እየታጠበች ትመለሳለች:: መኩብብ በዚያ ስቃይ ውስጥ ሆኖ የዋጋን የመረረ ለቅሶ አለማየቱና የእናቱን ሞት አለመስማቱ በጅቶታል:: ከአካልና ከመንፈስ ጉዳቱ በላይ ሀዘንኑና ጭንቀቱ ከግምት በላ ይሆንበት ነበር::

ዋጋ የታሰረችው በመከብብ ሰበብ ነው እንጂ ያገኙትባት መረጃ አልነበረም:: ለነገሩ መረጃ የሚጠየቅበት ዘመንም አይደለም:: የወታደራዊው አምባገነን መንግሥት ካድሬዎች አይነ ውሃው ያላማራቸውን ሁሉ የፀረ-አብዮት ታፔላ ለጥፎ ለማሰር ምክንያት አይፈልጉም:: የዋጋ እስር ምክንያት ግን መከብብ ነው:: የእሷ ነገር አይሆንለትምና ከፊቱ ላይ ሰናሰቃያት ምሥጢር ያወጣል ከሚል ስሌት ነበር::

ዋጋ ምርመራ ቦታ ደርሳ ገና መከብብን ስታየው እሱ ለመሆኑ እስከትጠራጠር ድረስ ተንገላቷል:: የተረፈ አከላት አልነበረውም:: የጎንደር ሰው ጉድ! እስኪላት ድረስ በፍቅር የወደቀችለት ሰው ፊቱ አብጦ እንደ ካርቦን ጠቁሯል:: መላ አካሉ በድብደባ ብዛት ሽባ ሆኗል:: ለመጀመርያ ጊዜ ፋሲለደስ ትምህርት ቤት መግቢያው በር ላይ ከጓደኞቹ ጋር እየተጫወተ ሲስቅ አይታው ወከክ አድርገው ብርክ ያስያዟት ሀጫ በረዶ የመሰሉት የፊት ጥርሶቹ የሉም:: ረግፈው ድድ ብቻ ይዞ ቀርቷል:: በቃ! ያኔ ነው ዋጋ ከቶርቸሩ በፊት ራሷን የገደለችው:: እነሱም ዝተው አልቀሩም ዐይኑ እያየ አሰቃዩዋት:: የእግሮቿና የእጆቿ ጥፍሮች በረው እስኪ ሄዱ ድረስ እየተጋገዙ የዱላ ውርጅብኝ አወረዱባት:: መከብብ ጭንቀቷንና ስቃዩዋን ላለማየት ዓይኑን ጨፍኖ ወደ ውስጥ አለቀሰ:: የጣር ድምጿን ላለመስማት ጆሮውን በጣቱ ደፈነ::

«የምታውቀውን ምሥጢር ሁሉ ካላወጣህ ገና ዐይንህ እያየ እንደ ዶሮ ብልት ገነጣጥለን እፊትህ እንገላታለን» ቢሉም የመጣውን ለመቀበል በቆራጥነት ራሱን አዘጋጀ:: ድርጅቱንና ጓዶቹን አሳልፎ ከቶም ቢሆን እንደማይሰጣቸው እንደ ነብሱ በሚወዳት በራሷ በዋጋ

ማለ---ተገዘተ:: «የትግሉ ነው ሕይወቴ...» የሚለውን መዝሙር ደጋግሞ በልቡ ዘመረ:: ዋጋ ራሷ የዋዛ አይደለችም:: ገና በህዋስ ደረጃ ያለች ቢሆንም የመለመላትን ጓድ ስም አሳልፋ አልሰጠችም:: ቶርቼሩን ጥርሷን ነክሳ ቻለችው:: የመከብብ እንዲያ መጎዳት ደግሞ በደርግ መንግሥት ላይ ያላትን ጥላቻ እንደ ብረት አጠነከረው:: ልቧ ጠጠረ:: ጥፍሯ አይደለም ዐይኗ ቢወጣ እንኳ ፍንከች እንደማትልላቸው ለራሷ ቃል ገባች:: እሷም እንደ መከብብ በፍቅሯ ማለች:: በቃ! ተዘጋ!

******

ጎንደር ውስጥ የመጀመሪያዎቹ የቀይ ሽብር ሰለባ ከሆኑት አንዱ መከብብ ነበር:: ለመቀጣጫ ሰው እንዲያየው ተብሎ ፒያሳ ላይ አስከሬናቸው ፀሐይ ሲበላው ዋለ:: የጎንደር እናት እንባዋን እንደ ራሄል ወደላይ ረጨች:: እንባዋ ግን ጸርሀ አርያም አልደረሰም:: ፈጣሪ ምህረቱን አላወረደም:: ግፈኞችንም አልቀጣም:: ዋይታና ሰቆቃ ገና አላበቃም:: የበደል ፅዋ ግን ሞልታ እየፈሰሰች ነው:: ኢትዮጵያ በልጆቿ ደም ታጠበች:: እጆቿን ወደሰማይ ዘርግታ «ሔሉሄ! ኤሉሄ!» አለች:: ጎንደር «እግዚኦ! ይማሀረነ--ይሰውረነ ከመዐቱ!» እያለች እሪ! ብላ አለቀሰች ለልጆቿ---- ለነመከብብ....

«ለአንድ ቀን እንኳ ዓይኑን ሳታይ መዋል የማይሆንላት ዋጋ ምን ይውጣት ይሆን?» ሲል ከልቡ አዘነላት የጎንደር ሕዝብ:: እንደ ውብ ሙዚቃ ድምጹን ሳትሰማ ማደር የሚያቅበጠብጣት ዋጋ አሁን ለዘለዓለሙ ላትሰማው ነው:: መከብብ እበጀ ሕይወቷን የሚያለመልም የአስትንፋሷ ያህል ነበር:: የጃንተከል ዋርካ የንግርት መከለቻ ተደርጋ የተቆጠረችው ዋጋ ለመከብብ ያላትን ፍቅር መደበቅ ሳትችል ቀርታ ነበር:: አሁን ግን ያ ሁሉ የለም! የመከብብ ነገር ለዘለዓለም የማይገለጥ የተዘጋ ፋይል ሆኗል::

«ምነው ባታ ወህኒ ቤት አብረው እንዳወረዷት ሁሉ አብረው ሬሳዋን ፒያሳ ላይ ዘርግተውት በነበር» ብሎ ብዙ ሰው ያን ከፉ ሞት እንኳ ለሷም ተመኝቶላታል:: ዋጋን ግን ቀይ ሽብር አለፋት:: የቁም ስቃይ እንድትቀበል ፈረዱባት::

የመከብብ መሰዋት ወሬው ሴት እስረኞች ክፍል ሲደርስ ዋጋ እንዳትሰማ በሹክሹክታ ነበር የተወራው:: የሆነ ነገር መቼም ተደብቆ አልቀረም:: ዘግይታም ነበር የሰማችው:: የተፈራው አልቀረም:: የእሷ ነገር እንቅልፍ ባይኗ ሳይዞር እንደ ለፈለፈች ውላ እንደ ለፈለፈች ማደር ሆነ:: ባትሞትም ሕሊናዋን ሳተች:: አንድ ሁለት ጊዜ ራሷን ለመግደል ሙከራ አድርጋ ከሽፎባታል:: ግማሽ ጎኑ ከተደረመሰ ሽንት ቤት ዘላ ገብታ በሰንት መከራ ተጎትታ ወጥታለች:: ለጥቂት ነበር ከሞት የተረፈችው:: ሌላ ጊዜ ደግሞ የወደቀ ሰለት አግኝታ ጎሮሮዋን በጥሳ ልትጥል አንገቷን ስትገዘግዝ ተያዘች:: ለሁለተኛ ጊዜ ሞት አልፏት ሄደ:: አሁን ድረስ ጠባሳው አንገቷ ላይ ወፍራም ማተብ መስሎ ተጋድሞ ይታያል::

«ዋጋ አንዳንዴ መለስ ሲሊላት ራሷን ሳታውቅ አትቀርም:: የፍቅረኛዋ መሰዋት እየታሰባት ይሆናል ራሷን ለማጥፋት የምትሞከረው» ይላሉ የእስር ቤት ጓደኞቿ በሀዘኔታ:: ከብዙ ምርመራ በኋላ ሀኪም መሰከረላት:: ዋጋ ከፍያለው እብድ ናት:: ከሰር ተለቀቀች::

ጎንደር ከተማን እየዞረች ስትዘፍን፣ ስታለቅስና ስትሳደብ ስትውል አይደከማትም:: ሰው ሁሉ እንደ ጦር የሚፈራቸውን የጎንደሩን አስተዳዳሪና የደርግ ሙሉ አባሉን እንኳ ሙልጭ አድርጋ ስትሰድባቸው እብድ መሆኗ በጅቷታል::

መላኩ ተፈራ የእግዜር ታናሽ ወንድም፣

የዛሬን ማርልኝ ሁለተኛ አልወልድም::

በዚህ ዘመን የልብን ለመናገር ማበድ ጥሩ ነው ለካ ያሰኛል-- ዋጋን ላየ:: እብደት እንኳ ከእቅሙ ሲፈልጉት እንዲህ በዋዛ የሚገኝ አልሆነም:: የወታደር ዩኒፎርም የለበሰ ሰታይ ጭራሽ ይብሰባታል:: የዘፈኑና የሙሾ ግጥም የሚታወሳት--- የመፈከሩ ጋጋታ የሚመጣላት መለዮ ለባሽ ሰታይ ነው:: በመከብብ የተነሳ ከቤታቸው እስከ ማስወጣት የደረሱት እከሰቷ ከአንጀታቸው አዘኑላት:: ደም እንባ አለቀሱላት:: ቢቸግራቸው ይዘዋት ጸበል ለጸበል ተንከራተቱ:: መጣፍ አስገለጡላት---በደብተራ አስደገሙላት---ፉቅራ አስቀሩላት:: በዘመናዊው ሕክምና ጣሩላት የዋጋን ጤንነት የሚመልስ ግን አንድም አልተገኘም:: መጨረሻ ላይ መላ ሲያጡ «አዬ ቆንጆ ብላሽ! እያዩ ማዘን!» ብለው ተሰፋ ቆርጠው ተዋት::

በጎዳር የገባ የተሰቦ በሽታ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እናትና አባቷን ተራ በተራ ሲነጥቃት ገና የሶስት ዓመት ጨቅላ ነበረች ዋጋ:: በለሳ እርባያ በታች ከቆላው ታናሽ እህታቸውን ቀብረው ዋጋን በጉንፋቸው ይዘው ጎንደር ከተማ መጡ መሃኗ አከስት:: የእህታቸውን ልጅ እንደ ልጃቸው ተንከባክበው አሳደጓት::

«ለወግ ማረግ ትበቃለች--ትዳራለች---ትኳላለች--ጧሪ ቀባሪዬ ትሆነኛለች» ብለው ዓይናቸውን በተሰፋ ጥለውባት አስተማሯት:: አሰረኛ ከፍል ደርሳ ነበር:: ምን ያደርጋል! የአብዮት እሳት የልጅነት ፍቅሯን በላው:: እሷንም አርመጠመጣት:: አብዮት ይጠቀም---በቃ! ዋጋ አበደችለት::

ዋጋ አዘወትራ የምትሄድባቸው ቦታዎች የታወቁ ናቸው:: ፒያሳ አደባባይ እየሱሰንና አራዳ ባታ ወህኒ ቤት አካባቢን አትለቅም:: ያለ እረፍት መዞሯ-- ቆሻሻ መሰብሰቧና ባገኘችው ቦታ ሁሉ ወድቃ ማደሯ ነው እንጂ እንደ ሌሎቹ እብዶች ልብሷን አልጣለችም:: ደርሳ ልደባደብ አትልም:: ብቻ ወታደር ሰታይ ደሟ ይፈላል:: ያኔ ሁሉም ነገር ይታያታል:: ሙሾውን -- ዘፈኑን --መፈከሩን ታወርደዋለች:: ግጥሙን በቃሏ ስትወጣው አንዲት ቃል ዝንፍ አታደርግም::

«ዋጋ እኮ እውቆ አበድ ናት:: እስቲ የምትናገረውንና ግጥሟን አዳምጡ:: በቃል ሳይሆን ወረቀት ላይ የምታነብ እኮ ነው የምትመስለው» እያሉ የሚያሟት ብዙዎች ናቸው:: ወፎች ወይ እርግቦች ሰብሰብ ብለው የወዳደቀ ጥራጥሬ እየለቃቀሙ ካዩች እየሮጠች ሄዳ ታባርራቸዋለች:: ተመልሰው እንዳያርፉ እየተከላከለች ጎብረተሰቡ በድብቅ የሚለውን እሷ ባዋጅ ታንጎራጉረዋለች::

«እንዲህ ወደ ጠለምት ወፌቱ ብረረ፤

ወልቃይት ጠገዴ ወፌቱ ብረረ፤

በለሳ እርማጭሆ ወፌቱ ብረረ፤

በኢትዮጵያ ሁሉ ወፌቱ ብረረ፤

ታጋይ ሞቷል ብለሽ ለታጋይ ንገሪ፡

ትላለች ድንጋይ ወደላይ እየወረወረች:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ያገኘችውን የወዳደቀ ወረቀትና የእስክርቢቶ ቀፎ ሁሉ ሰብስባ ይዛ ለቅሶዋን ታቀልጠዋች::

የተማሪዉ ደብተር አልጠፋም ተገኘ፤

የተማሪዉ እርሳስ አልጠፋም ተገኘ፣

ጎንደር ከፒያሳው ላይ በደም እየዋኘ::

ይህ እንጉርጉሮ ብዙ ጊዜ የሚመጣላት ፒያሳ አካባቢ ስትሆን ነው:: አስፓልቱ ላይ ኳ ብላ ትተኛለች፤ ትንከባለላለች:: እጅ እግሯን ታፈራግጣለች:: የሰበሰበችውን ወረቀት ትቀዳድዳለች:: ስክርቢቶ ቀፎውን ትሰባብርና ትበታትነዋለች:: ጥቂት ቆይታ የተለመደ ዙረቷን ትቀጥላለች:: ባታ ወህኒ ቤት አካባቢ ስትሆን ደግሞ አራዳ ገበያ ውስጥ የወዳደቀ ጎመን ካገኘች እሱን እየለቃቀመች የማይቀረውን ሙሾዋን ታወርደዋለች::

ያባ ሳሙኤልን ጎመን አትብሉት እርም ነው፤

አድጎ የጎመራዉ በሰው ስጋ ደም ነው።

«ቱፍ- ቱፍ -አይታያችሁም? እዩት ይህን ሥጋ መሬት ላይ ጥለውት--በፀሀይ ተለብልቦ--ሸቷል እኮ» ትልና ቋቅ እያደረጋት የሰበሰበችውን የጎመን ቅጠል ሁሉ በመጠየፍ ትወረውረዋለች ::

ፍቅረኛዋ መከብብ እንደ ታሰረ ነበር አእምሮዋን ነካ ያደረጋት:: በቀይ ሽብር መሰዋቱን የሰማች ጊዜ ደግሞ ለየላት:: ለዚህ ነው ወታደር ስታይ ደሟ የሚቆጣው:: የእንጉርጉሮዋና የዘፈን ግጥሞቿ ከእስርና ከቀይ ሽብር ጋር የተያያዙ የሆኑት መከብብ በደመነፍስ ስለሚታሰባት ሳይሆን አይቀርም:: ወትሮም እብድ የተነካበትን ውሉ- ነገር አይሰትም:: የሚሏት ብዙዎች ናቸው:: «እብድና ሰካራም የልቡን ይናገራል» እንዲሉ:: አውቃም ይሁን ሳታውቀው ልጁ ወይ እህት ወንድሙን--ባል ወይ ሚስቱን ወይ ዘመዱን ቀይ ሽብር የበላበትን የጎንደርን ኗሪ ሁሉ ቁስሉን እየነካካች እልቅሳ ታስለቅሰዋለች:: ልጅን ያህል ነገር የተነጠቀ ወላጅ የግፍ ግፍ-- የበደል ላይ በደል ጮክ ብሎ እልቅሶ እርሙን እንዳያወጣ እንኳን በአብዮት ሰይፍ ተከልክሷል:: ሀዘኑን «እም!!» ብሎ በሆዱ እምቆ ይዞታል:: ለፀረ-አብዮተኛ ሞት አይለቀሰም:: እርግዶ አይረገድም:: የአብዮት ኃጢያት ነው ተብሎ:: ወላጅ ሁሉ ግን እንባውን ወደ ውስጥ ማፍሰሱን አልተወም:: ጮሆ እልቅሶ ባይወጣለትም ወደ ሆዱ መንሰቅሰቁ አልቀረለትም:: እንባው አልቆ ደሙ ጠብ እስኪል:: ለዚህ ሁሉ ዋጋ እብደቷ በጅቷታል:: እንደ ፈለገች ሙሾዋን እየደረደረች ለቅሶዋን ታወርደዋለች:: የሚያገኟት ወታደሮች ሁሉ በመሳሪያ ያስፈራሯታል:: ንዴቱ የባሰባቸው ወታደሮች ይዘው ሊደበድቧት ሲሞክሩ ደግሞ

«ኤክሰኪዩዝሚ...ፕሊስ--አይ ላብ ዩ» ትላቸዋለች:: ለቀዋት ራቅ ስትል ደግሞ «ፋሸሽቱ ደርግ ይወድማል! ባንዳ ሁሉ ይደመሰሳል! እናታችሁን!» ትላቸዋለች:: ድንጋይ የምትወረውረው ለነሱ ሲሆን ነው::

«ቆይ አንቺ አውቆ እበድ ትገኛለሽ!» ይሉና ይዝቱባታል:: ሌላ ጊዜ ሲያገኟት በለደፍ እያዳፉ እየደበደቡ ሁለተኛ እንዳይደግማት ያስጠነቅቋታል:: ምን ያደርጋል! ነገም ያው ናት--- እብዷ ዋጋ---!

«ኃይሌ ሽሜ ጉጉ ይሻለን ነበር:: ትሻልን ሰድጄ ትብሰን አመጣሁ አሉ። ውይ ነዶ ከእሳት ወደ ረመጥ:: መከብብ ሞተ ሞተ---ጥላሁን ሞተ ሞተ---ማርታ ተደገመች:: በቃ! ምን ይጠበስ? በቃ ሞት ብቻ!---ሌላ ምን ተገኘ?---አላየንም አብዮት:: ቂ..ቂ..ቂ..አሃሃሃ! እሃ---አሃሃሃ» ልቧ ፍርስ እስኪል ትስቃለች::

ባታ ዙርያው ገደል መውጫው በዘበኛ፣

ጨነቀኝ ጠበበኝ ያንተው መገናኛ:: ትዘፍናለች::

ባታ ወህኒ ቤት እንኳን ውስጡ አካባቢው ይከብዳል:: እግር ጥሎት በጥጉ የሚያልፍ ሰው ሁሉ ድምጹን ጥፍት አድርጎ ኮቴው እንዳይሰማ ሹክክ ብሎ ነው:: ጥላውን አያምንም:: በጣም ካልተቸገረ በስተቀር በአካባቢው ዝር የሚል ሰው አይገኝም:: ግቢው ውስጥማ ምኑ ይጠየቃል? ማማው ላይ መትረየስ ደግነው የሚጠብቁት ወታደሮች ቁልቁል

እየተመለከቱ አላፊ አግዳሚውን ሰው ሁሉ ይገላምጣሉ—ያንቋሽሻሉ፡፡ ሰማይ ጥግ የደረሱ-- ፀሐይ የወጣችው ለነሱ ብቻ ይመስላቸዋል፡፡ ጧት ማታ ሀፍርና ቁር ሳይገድባት ለእስረኛ ልጇ ስንቅ ቋጥራ የምትመላለሰውን እናት በንቀት ያዋከባሉ፡፡ ካሻቸውም የያዘችውን ስንቅ በካልቾ ደፍተው እየገፈታተሩና እያንገላቱ ይመልሷታል፡፡ አብዷ ዋጋ እውነት ብላላች፡፡ ባታ ወሀኒ ቤት መውጫው ያስጨንቃል፡፡ ዙሪያውን የተገነባበት ጥርብ ድንጋይ ተራራ የተጫነን ያክል ይከብዳል፡፡ አዲሶቹ እስረኞች ትሩፋትና ራሄል የባታ ወሀኒቤት ድባብ የተጫናቸው ይመስላሉ፡፡ በጸረ- አብዮተኛነት ተጠርጥረው ከአንበሳሜ ተነድተው ባታ ወሀኒ ቤት ከገቡ ገና ሳምንት አልሆናቸውም፡፡

አርብ ቀን ነው፡፡ ትሩፋትና ራሄል ብቻ አቤት ውስጥ ነበሩ፡፡ ይነበብ ለመስከ ሥራ ወጥቷል፡፡ በአጋጣሚ ድሌ ከጓደኞቹ ጋር ሀሙሲት ሄዶ ነበር ያደረው፡፡ አንዲት ጥቁር አረንጓዴ ላንድሮቨር መኪና ሰትበር መጥታ ከነትሩፋት በር ላይ ቆመች፡፡ አንበሳሜ ለስራ ጉዳይ አልፎ አልፎ ከሚመጡት የመንግሥት መኪናዎች በስተቀር ለሕዝቡ መደበኛ አገልግሎት የሚሰጥ የመጓጓዣ መኪና አልነበረም፡፡ ድንገት ብቅ የሚሉትን መኪኖች ትንሽ ትልቁ ወጥቶ አንደ ብርቅ ያያቸዋል፡፡ ሰትበር መጥታ ከትሩፋት በር ላይ የቆመችው መኪና በሰው ተከበበች፡፡ ወደ ሐሙሲት ለመሄድ የተነሳ መንገደኛ ካለ ደግሞ የሚተባበረው ሾፌር ቢያገኝ አጋጣሚውን ለመጠቀም ድምጹን አለሳልሶ መጠየቁ የተለመደ ነው፡፡ ዛሬ ግን እንደዚያ የሚሆን ነገር አልነበረም፡፡ ከመኪናዋ ላይ በፍጥነት የወረዱት አራት ወታደሮች መሳሪያቸውን ደግነው ቦታ ቦታ ሲይዙ ፍጥነታቸው ከዐይን ቀድሟል፡፡ መኪና ብርቅ ሆኖበት ሊያይ የወጣው ሰው ሁሉ ድምት አንደ ገባበት የእይጥ መንጋ ሲበታተን ደቂቃ አልወሰደበትም፡፡ ሁለት የታጠቁ ወታደሮች ደግሞ ትሩፋትንና ራሔልን እጃቸውን በካቴና አቆራኝተው አያዳፉ ከቤት ይዘዋቸው ወጡ፡፡ ነፍሰጡር ለሆነችው ትሩፋት እንኳ ያዘነ ልብ አልነበራቸውም፡፡ ለእሰር ያበቃቸው ምክንያት ምን አንደሆነ መጠየቅ አልቻሉም፡፡ ከአንበሳሜ ተነድተው ባታ ወሀኒ ቤት ሴት እሰረኞች ጋር ተቀላቀሉ፡፡

ትሩፋት ቀደም ብለው የታሰሩትን እስረኞች ሁኔታ በጽሞና መከታተል በመጠኑም ቢሆን ጊዜዋን ያለ ጭንቀት እንድታሳልፍ ይረዳታል፡፡ ከታሰሩት ሴት አሰረኞች ሁሉ ይበልጥ ስሜቷን የሚስቡት ደግሞ ሁለት እብሮ አደግ ገበሬ ሴቶች ነበሩ፡፡ በከተማ በብልጣብልትነት ያልተበረዘው እስከነ ተፈጥሮው ያለው ንግግራቸውና ወጋቸው ይጥማታል፡፡ እርስ በእርስ መተሳሰባቸው ይገርማታል፡፡ የሚሉትን ሁሉ ትኩረት ሰጥታ ታዳምጣቸዋለች፡፡ ምንጊዜም ወሬያቸውና ጭንቀታቸው በሳት ተቃጠሎ ሰለ ወደመው ንብረታቸውና የእርሻ መሬታቸው ብቻ ነበር፡፡ የአነሱ ትልቋ ፕላኔት መንደራቸው ናት፡፡ ከእሷ ውጭ ሌላው ዓለም ምናቸውም አይደለም፡፡

ከአነሱ የውሎገብ የአግር መንገድ የሚያስኬድ መንደር ውስጥ የሚኖር የጋራ ዘመዳቸው የሰባት አመት ልጁን በማደን ይድራል፡፡ የሰርግ ጥሪ ይደርሳቸውና ተነስተው ይሄዳሉ፡፡ የሰርጉን ደስታ ገና በወጉ ሳያጣጥሙ ቤታቸው በጠሳት መቃጠሉን ይሰማሉ፡፡ ይነስም

ይብዛ ቤት የማይዘው ነገር የለም፡፡ እድሜ ልክ ያካበቱት ያለ የሌለ ንብረታቸው በእሳት ጋይቶ አመድ መሆኑን ሲሰሙ በደንጋጤ ተውጠው እያለቀሱ እየወደቁ---እየተነሱ ከመንደራቸው ይደርሳሉ፡፡ እየሆነ የጠበቃቸው ነገር ግን ፈጽሞ ያላሰቡት ነበር፡፡ መንደራቸው በገበሬ ማኅበር የአብዮት ጥበቃ ታጣቂዎች ይታመሳል፡፡

«ጓዝ ንብረታችሁን አሸሽታችሁ ባዶ ቤት አቃጥላችሁ ጸጥታ አደፍርሳችኋል፡፡ አብዮት ለመቀልበስ ታስቦ የተፈጸመ ሴራ ነው» አለ የገበሬ ማኅበሩ የአብዮት ጥበቃ ዋና ተጠሪ፡፡ መሳሪያውን ከአንድ እጁ ወደሌላው እጁ እያዟዟረ ንዴት ከወዲያ ወዲህ እያንቆራጠጠው፡፡ እነ ወይዘሮ ሙሉመቤት ከአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ጭራሽ አነሱው ወንጀለኞች ሆነው አረፉት፡፡ አመዳቸው ቡን አለ፡፡ የተናገረውን በትክክል ያዳመጡት አንኳ አልመሰላቸውም፡፡ ተቆጥቶ ያዙኝ ልቀቁኝ ወደ ሚለው የአብዮት ጥበቃ ግራ በመጋባት አተኩረው ተመለከቱ፡፡

«መንጋ ኢዲዩ ሁላ! ከናንተ አቅም ብሶ ባዶ ደሳሳ ጎጆ በማቃጠል መንግሥትን ለማታለል መሞከራችሁ ነው ይብልጥ የሚያናድደው፡፡ ቶሎ በል አጃቸውን በካቴና አስገባልኝ» አለ የአብዮት ጠበቃ ኃላፊው ወደ ሌላው የአብዮት ጥበቃ ዞር ብሎ፡፡ ለዚህ ሁሉ መንስኤው የአንደኛዋ ገበሬ ሴት ባለቤት ሸፍቶ ከኢዲዩ ጋር መቀላቀሉ ነበር፡፡ ሰበብ ሲፈልጉላቸው አንጂ የገዛ ቤታቸውን አሳት እንደማይለቁበት እነሱም ልቦናቸው ያውቃል፡፡ ከሰርጉ ቤት እንደ ደነገጡ ወጥተው-- ሲባከኑ መጥተው ግራ እንደ ተጋቡ የግፍ ግፍ በሰደፍ እየተዳፉ ተነድተው ባታ ወሀኒ ቤት ተወረወሩ፡፡

እነዚህ ምስኪን ገበሬ ሴቶች መሽቶ በነጋ ቁጥር የሚነጋገሩት መንግሥት ጉዳዩን ሲረዳው በእርግጠኝነት ትክክለኛ ፍርድ እንደሚሰጣቸው ነበር፡፡ ቤታቸውን በግፍ ያቃጠለው ባላጋራቸው ተይዞ የእውነት ብይን አግኝተው ካሳ እንደሚካሱ ነበር፡፡ ጧት ማታ የሚያሰቡት ቶሎ ተፈርዶላቸው የተቃጠለ ቤታቸውን መልሰው የሚያቋቁሙበትን መንገድ ነበር፡፡ ሰርከለት የሚወዘወዙት የእርሻው ወቅት እንዳያልፍባቸው ነበር፡፡ የተማማኑበት ፍርድ ደግሞ ቀኑን ቀን እየወለደው እየራቀ ይሄዳል፡፡ እየራቀ---እየራቀ--- ሚያዚያ ሲያልቅ ይኸው ድፍን አንድ አመታቸው፡፡

ትሩፋት እነዚህ ሴት ገበሬዎች ከሁሉም እስረኞች በላይ በጣም ያሳዝኗታል፡፡ እሷ እስከ አሀቷ የታሰረችበት ምክንያት በእጅጉ ቢገርማትም የአነዚህ ሴት ገበሬዎች የግፍ እስር ደግሞ ያንገበግባታል፡፡

«ሰው እድሜውን ሙሉ የኖረበትን የራሱን ቤት እንዴት ያቃጥላል? ሊያስሯቸው ከፈሰጉ አንኳን ምናለበት ሌላ ምክንያት ቢፈጥሩላቸው» ትላለች፡፡ ምንም በማያውቁ ንጹሃን ወገን ላይ ሁለት የጭካኔ ዱላ ባንድ ጊዜ ማሳረፍ ይሆንባታል፡፡ የደርግ መንግሥትን ግፍና ጭካኔ መግለጫ ቃላት ታጣለታለች፡፡

በባታ ወህኒ ቤት ሴት እስረኞች በአንድ ክፍል ውስጥ ነው የታጎሩት፡፡ እንደ ወንድ እስረኞች የፖለቲከና ደረቅ እስረኛ ተብሎ ነገር የለም፡፡ ከፍሉ እንደ አጥሩ ሁሉ ከከባድ ጠርብ ድንጋይ የተገነባ ነው፡፡ ከወርዱ ጠበብ ብሎ ቁመቱ ረጅም ነው፡፡ መሀል ላይ አካፋይ ለመስራት ታስቦ ይመስላል ተጀምሮ ቀርቷል፡፡ ሁለት ጠባባብ መስኮቶች ቢኖሩትም ከጣራው ርዝመት የተነሳ ሩ---ቅ ናቸው፡፡ ብርሃን እንደ ልብ አያስገቡም፡፡ በዚያ ላይ ወፍራም የብረት ፍርግርግ ተደርጎባቸዋል፡፡ ከፍሉ ናዳ የተጫነን ያህል ከብድ ይላል፡፡ ጣራው ረዝሞ ጭልም ስለሚል ከመሬት በታች ያሉ የሚመስል ስሜት ይፈጥራል፡፡ ተዘግቶ የሚውለው ወፍራሙ የብረት በር ሳይቀር የከፍሉን ጫና በእጥፍ ከፍ እንዲል አድርጎታል፡፡ ከወርዱ የጠበበው የከፍሉ አቀማመጥና የድንጋይ አገነባቡ ትንፋሽ እስኪያጥር ድረስ አፍን--ጭንቅ ያደርጋል፡፡ ነፍሰጡር ሲሆኑ ደግሞ ምን ያህል እንደሚከፋ የሚያውቀው እንደ ትሩፋት የደረሰበት ብቻ ነው፡፡ የወለሉ ሊሾ ፈራርሶ ያገጠጠው ድንጋይ ጉርባጤው ጎን አያስጥልም፡፡ ፍራሽ ማስገባት አይፈቀድም፡፡ በዚያ ላይ መተኛት የሚቻለው በወረፋ ነው፡፡ ግማሹ ሲተኛ ግማሹ ይቆማል ወይ ይቀመጣል፡፡ በቶርቸር ብዛት ከደከሙ፣ ከታመሙና ከትሩፋት በስተቀር፡፡

በሩ ስር አንድ አነስተኛ ጉርድ በርሚል ተቀምጧል፡፡ ለሽንት ተወጥቶ በሩ ከተዘጋ በኋላ የሆድ ህመም ያጋጠመ እንደሆን ሁሉም ነገር በርሚሉ ውስጥ ይጠናቀቃል፡፡ እንዲህ ያለ ችግር ሲከሰት የከፍሉ ሽታ መፈጠርን ያስረግማል፡፡ ከሁሉም በላይ ህመም ያጋጠማት እስረኛ የሚደርስባትን ጭንቀት መግለጽ ያስቸግራል፡፡ በእስረኞቹ መካከል ነውርን ገልጦ በርሜሉን መጠቀም የሚያደርሰው የመንፈስ ስብራት እንዲህ በቀላሉ የሚገለጹት አይደለም፡፡ በምርመራ ጊዜ በቶርቸር ከሚደርሰው የአካል ስቃይ ያላነሰ በባታ ወህኒ ቤት የማደሪያ ከፍል ውስጥም እንዲህ ያለ የስነልቦና ጉዳት ያጋጥማል፡፡ የባታ ወህኒ ቤት ሌላው አስገራሚው ነገር ሕጻናት ልጆችም ከእናቶቻቸው ጋር እስርን ገና በጨቅላነታቸው ይቀምሷታል፡፡

«ወዣደሉ ያሸንፋል! ወዣደሉ ያሸንፋል!» አለች አንዲት ከእናቷ ጋር አብራ የታሰረች ሦስት ዓመት ገደማ የሚሆናት ሕጻን ልጅ። ባለችበት ሆና ዘለል ዘለል ለማለት እየሞከረች፡፡ ወደ ጥግ በኩል ፊቷን ለግድግዳው ሰጥታ ተሸፋፍና ተኝታ የነበረችው አገሬ የምትባለዋ እስረኛ ድንገት ቱግ ብላ ተነሰታ

«ዝም በይ! አቁሚ!» ብላ ጮኸችባት፡፡ ሕጻኗ መዝለሏንም መዘመሯንም ወዲያው አቁማ በድንጋጤ አፍጣ ተመለከተቻት እናቷን ሙጭጭ አድርጋ እየያዘች፡፡ እናት ልጇን ወደ ጉያዋ ሸጉጥ አደረጋት፡፡«ምን አጠፋች» በሚል አስተያየት አገሬን እየተመለከተች፡፡ እስረኛው ሁሉ አገሬ ላይ አፈጠጠ፡፡ መሳሳቷ የገባት ወድያው ነው፡፡ ሕጻኗን ልጅ ልታባብላት ሞከረች፡፡

«ሚሚዬ ነይ፤ አይው ይህን እሰጥሻለሁ፡፡ አዲስ መዝሙር ደግሞ እኔ አስተምርሻለሁ» አለች አገሬ ትራሷ ስር አስቀምጣው የነበረውን ብስኩት አውጥታ እጇ ላይ ዘርግታ፡፡ ልጅቷ ትንሽ ከቆየች በኋላ ዘና ማለት ጀመረች፡፡ ቀስ በቀስም ቀረበቻት፡፡

«ላባደሩ ያቸንፋል! ላባደሩ ያቸንፋል! በይ ጎሽ! ሌላም ብስኩት አለኝ እሸጥሻለሁ» አለች አገሬ፡፡ መዝሙሩን ደጋግማ ልታስተምራት እየሞከረች፡፡ ትሩፋትና ራሄል አገሬ ለምን እራስ ነብር እንደ ሆነች አሁን ገብቷቸዋል፡፡ «ወዛደርና ያሸንፋል» የሚሉት ደርግና ደጋፊዎቹ የሚጠቀሙባቸው ቃላት ናቸው፡፡ «ወዛደሩ ያሸንፋል!» እንደ ማለት፡፡ ኢሕአፓ ደግሞ በበኩሏ «ላባደርና ያቸንፋል» የሚሉትን ቃላት ትጠቀማለች፡፡ ስሜታዊነቷን አልወደዱትም፡፡ በፖለቲካ እስረኛ ስም ጆሮ ጠቢም አብሮ እንደሚታሰር ሳይታልም የተፈታ ነው፡፡ ደግሞ ደህና ቤተሰብ ያላት ሳትሆን አትቀርም፡፡ በየሳምንቱ ልብሷ ታጥቦ ሲመጣ ከሽቶ ባህር ተነከሮ የወጣ ነው የሚመስለው፡፡ ያን በስንት ሰው ላብና ትንፋሽ የታፈነ ከፍል ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ጠረኑን ይቀይረዋል፡፡ እስር ቤት ውስጥ ሆናም ምቾቷን ለመጠበቅና እንዳይከፋት ይመስላል ቤተሰቦቿ የማያደርጉላት ነገር የለም፡፡ እሷ ግን ይህን ያህል ቦታ አትሰጠውም፡፡

አገሬ በራሷ ላይ ያላት መተማመን የሌላውን እስረኛ መንፈስ ያጠነክራል፡፡ ወጣ ካለው ግንባሯ ስር ከኮፈናቸው ወጣ ወጣ ያሉት ፈጣጣ ዐይኖቿ ደፋር መሆኗን ይመሰክራሉ ግን ታበዛዋለች፡፡ አጉል ድፍረት አላስፈላጊ መስዋዕትነት ያስከፍላል፡፡ በዚህ አጉል ድፍረቷ በየጊዜው ምርመራ ቦታ እየተወሰደች አሳር መከራዋን አይታለች፡፡ በተለይ የአንድ ጊዜው ገጠመኟ እጅግ ዘግናኝና መፈጣሯን የጠላችበት ነበር፡፡

«አገሬ የምታውቂውን ምሥጢር ብትነግሪን እኮ እንዲህ አትሰቃይም ነበር» አላት ፊት ለፊቷ የተቀመጠው መርማሪ ወታደር ጠረጴዛው ላይ ፈርጣማ ክንዶቹን አሳርፎ ፊቱን በጆቹ መዳፎች ደግፎ ዐይን ዐይኗን እያየ፡፡

«እንድዋሽ ነው የምትፈልገው? እውነቱን ነግሬሃለሁ፡፡ እኔ ከምንም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ የለሁበትም፡፡ የወላጆቼ ቤት ኮርኒስ ሳይቀር ፈርሶ ምንጥር ተደርጎ ተፈትሿል፡፡ መሳርያ ቀርቶ ወረቀት እንኳን አልተገኘም፡፡ ልታምነኝ ይገባል፡፡ የምታሰቃዩት ከምንም ነገር የሌለች ንጹህ ሴት ነው» አለች ኮስተር ብላ፡፡

«ደረቅ! ደረቅ ነሽ! አጉል ድርቅና ደግሞ ስቃይሽን ከማብዛት በስተቀር ምንም አያዋጣሽም፡፡ ተጠቁመሽ ነው የተያዝሽው፡፡እንደ ሌሎቹ ወጣቶች ታፍሰሽ እንኳን አይደለም» አለ ሁለመናዋን በዐይኑ እየዳሰሰ፡፡

«ሰዎች በጥላቻ ተነሳስተው ሊጠቁሙ ይችላሉ፡፡ የጠቆመኝ ልጅ ደግሞ ላውጣሽ ብሎ ጠይቆኝ እንቢ ስላልኩት ነው፡፡ የሚገርመው ግን ዘዴው ሰርቶለታል፡፡ የጊዜውን ሁኔታ

ተጠቅሞ ቁጭቱን ሁሉ ተወጥቶብኛል:: እንዲህ ቆሳስየና ከሰውነት ተራ ወጥቼ ቢያየኝ እንዴት ደስ እንደሚለው አስብ:: እናንተም እየተባበራችሁት ነው» ይህን ስትል መርማሪ ወታደሩ የጠቆማትን ልጅ በቅናትና በጥላቻ አሰበው:: በልቡ እንዴት እንደሚበቀለው እየዛተ::

«የምትናገሪው እውነት ለመሆኑ ምን ማረጋገጫ አለሽ?»

«እሱም እኮ ይህንን አውቆ ነው የተጫወተብኝ:: ምስክር ይዞ አይጠይቀኝ ነገር::»

«ልጁን አምጥቼ ፊት ለፊት አገናኛችሁና ኋላ ታፍሪያለሽ:: ፀረ አብዮተኛነትሽ ዳግም ከተረጋገጠ ደግሞ እንችን አያድርገኝ!»

«ይምጣ!» አለች አገሬ በእርግጠኝነት:: «ይምጣ! ፊት ለፊት ያግኘኝና እስቲ አልጠየኳትም ይበል! እርግጠኛ ነኝ እንዴት ሲያስቸግረኝ እንደ ነበር እሱ ቢክድ እንኳን ዐይኑና ሁኔታው ያሳብቁበታል:: እንቢ ስላልኩትማ ነው ጠቁሞ ቂሙን ሁሉ የተወጣብኝ» አለች:: የጠቆማት ልጅ በድብደባ ብዛት ሌሊቱን ምቶ ማደሩን በጓድ ወታደሮች በኩል ደርሷታል:: ከፊቷ የተቀመጠው መርማሪ ወታደር ግን በወቅቱ ተረኛ ስላልነበር ስለ ልጁ መሞት ገና ያወቀውና የደረሰው መረጃ አልነበረም:: በምርመራ ወቅት በድብደባ ብዛት የሚሞቱ ሰዎች መኖራቸው የተለመደ ነው:: አንድ ተረኛ መርመሪ ወታደር ቶርች ሲያደርግ (ሲደበድብ) ሰው ቢሞትበት ምንም እንዳልተፈጠረ በመቁጠር አስከሬኑን የትም ሊጥለው ይችላል:: የሰው ነፍስ በማጥፋት ወንጀል እንደማይከሰስ ያውቀዋል:: የፈረደበት ቤተሰብ ስንቅ ይዞ ሲመጣ «ተቀባይ የለም» በሚሉ ሁለት ቃላት ብቻ መርዶውን ይሰማል:: በሀዘን የተኮማተረ አንጀቱን ታቅፎ በቤቱ ጓዳ አልቅሶ ዝም ይላል::

መርማሪ ወታደሩ ቅናት ውስጥ አንጀቱን ቅጥል ሲያደርገው ተሰማው:: የጠቆማትን ልጅ እዚህ ምርመራ ቦታ አስመጥቶ እንዴት እንደሚያስቃየው እያሰበ እያለ አንዳች ተፋታታኝ ሙቀት መላ አካሉን ወረሰው:: እንደ አቦ ሸማኔ ሳብ-- ረገብ ብሎ ሙትት ካለው ሸንጧ ውስጥ መዋል አሰኘው:: ደረቱ መሀል አቅፉ ውስጥ እምቅ– ጭምቅ ማድረግ አማረው:: ውጥርጥር ቅስፍ የሚያደርግ ስሜት ተፈታተነው:: ትኩሳቱ ቶሎ ካልበረደ እቶን እሳቱ እንድዶ አቃጥሎ አቅልጦ የሚጨርሰው መሰለው:: ከተቀመጠመት ድንገት ብድግ ብሎ እላይዋ ላይ አንዣበበ:: ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ሲል ሰማችው:: ፈራችው:: ይባስ ብሎ እጁን ትከሻዋ ላይ አሳረፈ:: ቀፈፋት:: ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ:: ጠብደል ጠደብደል ፈርጣማ ወታደሮች ያን ሁሉ ቶርቸር እየተፈራረቁ ሲወርዱባት እንደ አሁኑ አልደነገጠችም:: አልፈራችም:: ያለምንም ማወላወል በቆራጥነት ተቋቁማዋለች:: አሁን ግን ፈራች::

«ምን አለበት እውነቱን ተናግረሽ ከስቃይ ብትገላገይ? መሞት ትፈልጊያለሽ ማለት ነው አገሬ? ልጅነቷን ያልጨረሰች እንደ አንቺ ያለች ቀዘባ ወጣት ሞት አይገባትም:: በፈጠርሽ አገሬ እውነቱን አውጭና እኔንም ገላግይኝ:: ምን አለበት በስቃይሽ እንዳዝን ባታደርጊኝ?» አለ እንደ ቆመ:: እጁን እላይዋ ላይ አላነሳም:: መደባበሱንም አላቋረጠም::

«መዋሸት አለብኝ ማለት ነው?» አለች ራስዋን ከተቀመጠችበት ወንበር ወደ ጫፍ እያወጣች::

«በእናትሽ አገሬ ተይ! ስንተዋወቅ! ለምን ካልሆነ ነገር ውስጥ አድገባ ትገፋፊኛለሽ? ይልቅስ አውነቱን ተናገሪና በሰላም ፈርመሽ ውጭ:: ከፈርማ በኋላ ማንም ጠያቂ እንዳይኖርሽ አደርጋለሁ:: ፋይልሽ ጭራሽኑ እንዲጠፋ ልተባባርሽ ሁሉ እችላለሁ::»

«እንዴት ነው ያልሆንኩትን ሆንኩ የምለው?»

«እሱ የአናርኪስት ሁሉ ድርቅና ነው:: አይጠቅምሽም:: ይልቅስ መልማዮችሽ እነማን እንደ ሆኑ አሳውቂ:: የደበቅሽውን መሳሪያ አስረክቢ:: ለማን ደቼ ይድላው ብለሽ ነው የምትሰቃይው? ለማንም ስልጣን መወጣጫ እንችን የመሰለች ለግላጋ ወጣት የአብዮት ሰይፍ ሊቀላት አይገባም» አላት በልምምጥ:: ትንፋሹ በዝቶ ቃላቶቹ እየተቆራረጡበት:: እሷ ደግሞ በሽሽት ከወንበሩ ጫፍ ወጥታ ልትወድቅ ደርሳለች::

«እኔ እኮ እንዴት መዋሸት እንዳለብኝ አላውቅም:: እንኳን መሳሪያ ልደብቅ ቀርቶ የማንም የፖለቲካ አባል እንዳልሆንኩ ስነግርህ ካላመንከኝ የልቤን እንዴት አድርጌ ነው ማሳየት የምችለው?»

«አንቺና መሰሎችሽ የማይገባችሁ ነገር መርማሪ ወታደሮች ስንባል እንደ ሰው የሚያፈቅር ልብ ያለን አይመስላችሁም:: ለሰው ልጅ በተለይ አንቺን ለመሰለች ውብ ወጣት የሚያዝን አንጀት የተፈጠረብን አታድርጉንም:: እኛም ግን ሰዎች ነን -በሰው አምሳል የተፈጠርን::» የሰውነቷን መንቀጥቀጥ የሚገነዘብበት ሕሊና አልነበረውም:: የሚያዳምጠው የውስጥ ስሜቱን ብቻ ነበር:: ቅ---ስስፍ አድርጎ የያዘውን አንዳች ውጋት:: አገሬ ደግሞ መውሰድ ያለባትን እርምጃ እያሰበች ነበር:: መጮህ አያዋጣትም:: እዚህ ግቢ ውስጥ በድብደባ ብዛት የሚጮኸው አልፍ አላፍ ሰው ነው:: በመጮህ የማንንም እርዳታ አታገኝም:: ይህንን ከምር የፈጀ ገመሬ ዝንጀሮ የሚያከል ሰው መታገል ደግሞ ፈጽሞ የማይሆን ነው::

አሁን እጁ ጠንከር እያለ ነው:: ወደ ጡቶቿ ሲደርስ ግን መታገስ አልቻለችም:: ሳታስበው በኃይል መንጭቃው ስትነሳ ፍጥነቷ ለራሷም አልታወቃትም:: በዱላ ብዛት የቆሳሰለ የእግሯ ስቃይ አልተሰማትም:: ቅጽበታዊ አነሳሷ ያልጠበቀው ስለነበር እሱንም በጣም አስደነገጠው:: የተወጣጠረ አካሉ ከመቅጽበት ሙሽሽ አለ:: እቶን እሳት ያሰበሰው

የመሰለው ግለት ብ--ርድ አለለት። ይለበልበው-- ያቃጥለው የነበረው እሳተ-ነበልባል ውሀ እንደ ተቸለሰበት ፍም ችስስ ብሎ ጥፍት ሲል ታወቀው። መላ አካሉ ያነሰ መሰለው። በምትኩ ህፍረትና እልህ ሁለመናውን ይዞ ይንጠው ጀመር። ባለ በሌለ ኃይሉ ከወዲያ ወዲህ በጥፊ አላጋት። ወለሉ ላይ ባፍ ጢሟ ተደፋች። ያፈረጠመ ጡንቻው እስኪዝል ድረስ ወረደባት። ወደ ወህኒ ቤት ስትመለስ ያን ቀን ነፍሷ ያድራል አልተባለም ነበር። የእጅና የእግር ጥፍሮቿ አንዱም አልነበሩም። እግሯ ተተልትሎ ተተልትሎ አውሬ የበጫጨቀው ስጋ መሰሏል። በአፍ በአፍንጫዋ ደም እንደ ውሃ ይወርዳል። እንዲያ ሆና አገሬን ያየ «የሰው ልጅ የማይችለው መከራ የለም» ያሰኛል።

ባታ ወህኒ ቤት ሴት እስረኞች የታሰሩት በተለያየ ምክንያት ነው። የሚገርመው ግን ካለነዚያ ሴት ገበሬዎች በስተቀር ሁሉም «እንሞታለን» ብለው ይፈራሉ። የታሰሩበት ምክንያት ይከበድም ይቅለለም ጊዜውን አያምኑትም። ወታደር ባዩ ቁጥር ይበረግጋሉ። በዚያ ላይ ደግሞ እስረኛው ሁሉ የየራሱ አመል አለው። በተለይ ለየት ያለ ሁኔታ የሚታይባቸው ደግሞ አሉ። ለምሳሌ ጠቆር ፈርጠም ያለችው እስረኛ ከሌሎቹ እስረኞች የበለጠ ትፈራለች። እንደ ደነገጠችና እንደ ተርበተበተች መሽቶ ይነጋላታል። ሁሉም እስረኛ እንደ ሲኦል ወደ ሚቆጥረው ምርመራ ክፍል እንኳ አልተወሰደችም። እንድም ቀን ግርፋት፣ ስቃይይና መከራ አላጋጠማትም። ለምን እንዲህ እንደምትፈራ ሁሉም እስረኛ ይገርመዋል። አንድ ቀን እንዲሁ እንደልማዷ

«እኔስ መቼም አልወጣ! አይለቁኝም! ይገሉኛል» እያለች ስትርበተበት ሌላኛዋ እስረኛ

«ወንጀልሽ ምን ያህል ከባድ ቢሆን ነው እስከ ሞት የሚያደርስሽ? የኢሕአፓ አባል ሆነሽ ወረቀት ስትበትኚ ሳይሆን አይቀርም የተያዝሽው» ጠየቀች ማዶ ፊት ለፊቷ የተቀመጠችው እስረኛ።

«አባ ደሞ ማነው ራቴዋ!? ኧረ እኔ አላውቀውም።»

«እንግዲያው ሰርቀሽ መሆን አለበት» አከለች ፍቅርተ የአገሬ ጓደኛ ናት፣ እሷም የፖለቲካ እስረኛ።

«ኧረ እድሜ ለእናቴ! ቀጥታ ነው ያሳደገችኝ። ከድህነት በስተቀር የእጅና የአፍ አመልም የለብኝ» አለች እየተኩራራች። ትከሻዋን ነፋ አንገቷን ሰበቅ አድርጋ።

«የኢሕአፓ ወይ የኢዲዩ አባል ካልሆንሽ---- የጠባብ ቡድኖቹ የሻቢያና የትህት ተላላኪ ካልሆንሽ ወይ ደግሞ ስትሰርቂ ካልተያዝሽ--- በምን ምክንያት ነው ታድያ ባታ ወህኒ ቤት ልትገቢ የቻልሽው? ሰው ገለሽ መሆን አለበት» አለች አገሬ። በእስረኞቹ እንከብካቤ እያገገመች መጥታለች። እግሯ ድኖ ሙሉ በሙሉ መርገጥ ባትችልም በሁለት ሰው ድጋፍ ትንሽ ትንሽ መንቀሳቀስ ጀምራለች።

«ኧረ በሰማም! ምን አልኩሽ ራቴዋ!? የምድሩ ስቃይ ሳያንሰኝ ደሞ የሰማይ ቤቴ ይዘጋ! ወይ ጉድ! ጆሮ አይሰማው የለ! አፍሽን ሞልተሽ ስትናገሪው ትንሽ እንኳን አይዘገንንሽም! ምን ያለሽው ጨካኝ ነሽ አንቺየዋ!» አለች።

«የወንጀልሽ ዓይነት እኮ ግራ አጋባን። እንዲህ ፍርሀት ለቆ 'እሞታለሁ! አይለቁኝም!' የሚያሰኝ ምን ጥፋት ሰርተሽ ነው ታዲያ? ሁልጊዜ እየፈራሽ ከምትርበተበቺ የሰራሽውን ንገሪንና ይውጣልሽ።» አለች አጠገቧ የተቀመጠችው እስረኛ።

«ከምሰራበት ቤት ደመወዝ ጨምሩልኝ፤ ያለዚያ አሰናብቱኝ ብዬ በመጠየቄ ነው አሰሪዎቼ ተዚህ እምጥተው የወረወሩኝ እንጂ ሌላ አበሳም የለብኝ» አለች ድምጿን ዝቅ አድርጋ ወደ በሩ በስጋት እየተመለከተች። ወድያው መነፋረቅ ጀመረች።

«የማይታመን ነገር ነው የምትነግሪን! ደመወዝ መጨመር ወይ ማሰናበት ሲችሉ አሰሪዎችሽ ለምን እንድትታሰሪ አደረጉ?» አለች ፍቅርተ። ሁሉም እስረኞች በጥርጣሬ ዐይን አዩዋት። ወንጀል አልሰራሁም ባይዋን እስረኛ።

«አይውላችሁማ!» አለች አሁንም ስጋት እንደ ያዛት ወደ በሩ እየተመለከተች «አይውላችሁማ ከኚያ ተትልቁ ሰውዬ---እኚያ እንኳን እንደ ጦር ተሚፈሩት ተገኘሁ ቅምጥ ቤት ነው የነበርኩ። ጌትየው ሲመጡ እግር አጥቤ በቅባት የማሽም እኔው ነበርኩ። ምሥጢር ታወጣለች ተብዬ ነው የታሰርኩ» ስትል እስረኛው ሁሉ በድንጋጤ ዐይኑን አፍጦ አፉን ከፍቶ ተመለከታት።

«ምነው ደመወዝ ጨምሩልኝ ብዬ የጠየኩ ቀን ልሳኔን በዘጋው ኑሮ! በጉልበቴ ሽቅየ በሽተኛና ደካማ እናቴን እንዳልጦር። ባዶ ቤት ተዘግታ መሞቷ ነው እንግዲህ። እኔንም ይገሉኛል! አይተውኝም!» ብላ ማልቀስ ጀመረች። ሁሉም አዘነላት።

«አይዞሽ! አንቺ እንደምታስቢው ነገሩ ከባድ ላይሆን ይችላል። ለቅጣት ትንሽ ቀን አቆይተው ይለቁሽ ይሆናል» አለች አገሬ እርግጠኛ ባትሆንም ያጽናናቻት መስሏት።

«አይ ወጉ እያ! ሳይለቁኝ ቀሩ! እንደዚያ ቢያስቡ ኑሮማ ወይ ደመወዜን መጨመር ወይ ደሞ ተቤታቸው ማስወጣት አይቀልም ነበር። አይ እምሳኬ! በየለው ቤት ተገርዶና ተንከራቶ መብላት ምን ኃጢያት አለውና ለዚህ መከራ ዳረከኝ። ወይኔ እናቴ!» እዬዬዋን አስነካችው። ፖሊስ ይመጣብሻል ባትባል ኖሮ ማቆሚያ አልነበራትም። እስረኛው ሁሉ አዘነላት። ከጎንደሩ ዋና አስተዳዳሪ ውሽማ ቤት የነበረች። ብዙ ምሥጢር ያየች--- የሰማች። መውጫም የላት።

የባታ ወህኒ ቤት ሌላው አስገራሚ ነገር ደግሞ የህልም ዓይነት ለጉድ ነው። ህልም ሳያልም የሚያደር ሰው አይገኝም። የእንደኛዋ ግን ከሁሉም ይብሳል። ከፉው አመሏ ታድያ

እስረኛውን ሁሉ ፍቱልኝ እያለች መወትወቷ ነበር:: አንድ ቀን እንዲሁ እንደ ለመደችው ፈጠራ የመሰለ ህልሟን ለትቀበጣጥር::

«የዛሬ ሕልምሽን የምፈታልሽ እኔ ነኝ:: ሳታሳሰች ያለምሽውን በትክክል ንገሪኝ» አለች ፍቅርተ:: አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር አታወራም:: አገሬ ጋር ግን አፍ ለአፍ ገጥመው ሲወያዩ ይታያሉ:: ብዙውን ጊዜ በራሷ ሐሳብ ተውጣ ዝም ነው የምትል:: ዛሬ ደርሳ ህልም ፈቺ ለትሆን ሁሉም ለመስማት ጆሮው ቆመ::

«አውነትሽን ነው? አሰቲ ማሪያምን በይ:: ሕልም መፍታት ትችያለሽ?» አለች ሕልም • አላሚዋ::

«አዎ እችላለሁ ማርያምን! አንች ብቻ ያየሽውን በትክክክል ንገሪኝ::»

«ኧረ አሱንስ አሳምሬ እነግርሻለሁ» አለች:: አቀማመጧን አያስተካከለች:: «ይኸውልሽማ! ጥጥ ነድፌ--ነድፌ እያመለመልኩ ፈትየ ለስንዝር አገልግሌን በልቅ ሙልት አደርጋት ይመስለኛል:: ዛዲያልሽ ድንገት ተጎረቤት ሰው ይጠራኝ ይመስለኛል:: ብድግ ብዬ ደጃፌን ሳልዘጋው ወጥቼ አኸዳለሁ:: ስመለስ ተየት መጣ ሳልለው እንድ ቀንዳም ጥቁር ፍየል ጠላታችሁ አመድ ይሁን ልቁን በሙሉ እመድ አድርጎ በልቶት አገኘዋለሁ:: በጣም አዝናለሁ፤ አለቅሳለሁ:: ተናድጄ ባገኘሁት ፍልጥ እንጨት ልመታው ሰል ደሞ በአሱ ብሶ ቀንዱን አሹሎ ሊወጋኝ አለነ ይመጣብኝ ይመስለኛል:: ተዚያ ወድያማ ጠላታችሁ ድንግጥ ይበል! በድንጋጤ ባትቼ ወድያውኑ ነቃሁ:: »

«ህልሙን ያየሽው መቼ-- ማለቴ ጊዜውን ታስታውሽዋለሽ?» ጠየቀች ፍቅርተ:: ለፍችው እየተዘጋጀች::

«ንጋት ላይ ነው– ንጋት ላይ:: ለሽንት ውጡ ስንባል ብዙም አልቆየን» አሰች::

«እንግዲያውማ ልንገርሽ ስሚ ፈትል እድሜ ነው። ትልቁ ቀንዳም ፍየል ሰይጣን ነው:: በዚህ ዘመን ደግሞ ሰይጣን ማን እንደሆነ ታውቂያለሽ አይደል?» አለች ፍቅርተ:: ለሚቷን ለማንበብ እየሞከረች::

«ኧረ እኔ ወት አባቴ አውቄው!» አለች ሕልም አላሚዋ:: የፍቹ አዝማሚያ አላማራትም:: የመስማት ፍላጎቷ ሞተ::

«ጥቁሩ ፍየል ፈትልሽን ከበላው እድሜሽ ማጠሩን ያሳያል:: ንጋት ላይ መሆኑ ደግሞ የጊዜውን ቅርበት ያመለክታል» አሰቻት ፍቅርተ ፍርጥም ብላ:: አዚሁ አስር ቤት ውስጥ ሲባል ሰምታ ከወሰደችው ልምድ እንጂ ስለ ሕልም ፍቺ የምታውቀው ነገር ኖሮ አልነበረም::

ያልተቋጨ ጉዞ

«ሳልለርቅ ለረቅሽ ተብዬ ነው የታሰርኩ» የምትለዋ እስረኛ ወሽመጧ ቁርጥ አለ:: አዬዬዋን አቀለጠችው:: በሰንት ማጽናኛ ነበር ዝም እንድትል የተደረገው::

«ፍቅርተ ምነው እንዲህ ጨከንሽባት? በጭንቀት ለማሰቃየት እኮ ባታ ወህኒ ቤት ራሱ ከበቂ በላይ ነው:: ልክ አይደለሽም!» አለች አገሬ አዝናባት:: የአገሬን ያህል ባይሆንም የወፌላላ ቶርቸር ፍቅርተም አልቀረላትም:: እጅ አግሯ ፈንድቶ አንድ ሰሞን ይህ ነው የማይባል ሰቃይ አይታለች:: ሆኖም

«ፖለቲካ ብሎ ነገር ምንም አላውቅም! የምንም ድርጅት አባል አይደለሁም» በሚለው አቋማ ጸንታ እለካሁን ቆይታለች::

«ተያት እባክሽ! ጆሮ ላትሆን አትቀርም:: አዚህ እኛ ጋር ህልም ፍቱልኝ ምናምን እያለች ስትወተውት ትቆይና ከወታደሮቹ ጋር ሄዳ ደግሞ አፍ ለአፍ ገጥማ ስትሞጣሞጥ ብዙ ቀን አይቻታለሁ::»

«አለማወቋ እኮ ነው ፍቅርተ:: አየሄደች የሆነ ያልሆነውን ሹክ ባለች ቁጥር ይፈቷት ይመስላታል:: ምንም ማድረግ የማይችሉ ተራ ወታደሮች መሆናቸውን አንኳ አትገነዘብም:: ደግሞስ ደርግ ለስልጣኑ የሚያሰጋው መስሎ ከታየው ሰላይ ኖረ አልኖረ ከማሰቃየትና ከመግደል ይመለሳል ብለሽ ነው? የእሷ መሰለልና እየሄዱ መንሿከክ በእኛ ላይ ምን ለውጥ ያመጣ መሰለሽ ፍቅርተ?»

«ትክክል ነሽ አገሬ:: የማልመልሰው ነገር ሆኖብኝ ነው እንጂ እኔም ተሰምቶኛል:: ጥሩ ስራ አልሰራሁም:: በስሜት ተነሳስቼ ይችን ምስኪን ሰው ማስጨነቅ አልነበረብኝም» አለች ፍቅርተ ፀፀት እየተለማት:: ቅቤ የተለቀለቀች ትንሽ አንጎቿ የመሰለች የቀይ ዳማ ፊቷ ላይ ሀዘን ተነበበበት:: እስረኞቹ ሁሉ በፍቅርተ ህልም አፈታት ቅሬታ ገብቷቸው ዝም ብለው በየራሳቸው ሀሳብ መቆዘም ያዙ:: ያ እንደ መቃብር የሚከብድ ከፍል የባሰውን ተዘፈዘፈ::

******

«አንተ ማማው ላይ ያለኸው የደርግ ወታደር ፐሊስ አሰገባኝ:: በአናትህ አንድ ጊዜ ብቻ መከብብን አይቼው ልውጣ:: አ! አንድ ጊዜ ብቻ! አ! ሰማ አንተን እኮ ነው! መሰሚያህ ይዘጋና ምን ይዘጋሃል!?» ድንጋይ ወደ ማማው ወረወረች ዋጋ::

«ከዚህ አካባቢ ጥፊ ብያለሁ አንቺ አውቆ አበድ! አንቺን አብድ ናት ብሎ የመሰከረልሽን ሐኪም ነበር መጠፍነግ! እብድ ሳትሆኝ አብድ የሚል ታርጋ ለጥፋሽ እንደ ፈለገሽ የልብሽን ትናገሪያለች:: እንቺን ብሎ አብድ!» ብሎ መሳሪያውን አቀባበሎ ጮኸባት ማማው ላይ ያለው ዘብ::

«ባንዳ ይወድማል! ፋሽስቱ ደርግ ይደመሰሳል! ተኩስ! ወንድ ከሆንክ ተኩስ! የፋሽስት ቡችላ! ፊዲስት! ባንዳ!» ጮክ ብላ ተሳደበች ዋጋ:: ወታደሩ በበኩሉ በንዴት ጦፎ ይሳደባል--ይራገማል--ይዝታል:: የአካባቢው ሰው የሁለቱን ምልልስ እያዳመጠ ውስጥ ውስጡን ይስቃል:: ማማው ላይ ያለው ወታደር ከዋጋ የባሰ አብድ እሱ እንደ ሆነ ይቆጥረዋል::

ለሽንት ወጥተው ለትንሽ ሰዓት ውጭ እንዲቆዩ የተፈቀደላቸው ሴት እስረኞች እንዲሁ ምልልሱን እያዳመጡ በወታደሩ ቂልነት አንገታቸውን ደፍተው ይስቃሉ:: ዋጋን ለዚህ ያበቃትን ይህን ከፉ ጨካኝ ሰው በላ መንግሥት አጥብቀው አየኮነኑ:: ሴት አስረኞች ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም ከከፍላቸው ፊት ለፊት ባለችው ትንሽ ሜዳ ላይ ተቀምጠው ፀሀይ የሚሞቁበትንና የሚናፈሱበትን ጊዜ ምንጊዜም በናፍቆት ይጠብቁታል:: የውጭው አየር ይናፍቃቸዋል:: ቀና ብለው ንጹሁን ሰማይ ማየት ያጓጓቸዋል:: ከወህኒ ቤቱ ግንብ አጥር ውጭ የሚሰማው ድምጽ ያስደስታቸዋል:: ፍርሀት የሚለቀው ቀና ሲሉ ማማው ላይ ያሉት ጠባቂ ወታደሮች መኖራቸው ሲታሰብ ነው:: ዋጋ ዛሬ ዘቡ ጋር ሰድብ ገጥማለች::

ድንገት ከዋጋ ጋር የሚያደርገውን ሰድድብ አቁሞ «እስረኞች ቶሎ ወደ ከፍላችሁ ግቡ ፍጠኑ!» አለ ዘቡ በቸኮላ:: ወድያው አስረኞችን እየያዘች ወደ ምርመራ ቦታ የምታመላልሰው የወታደር መኪና ስትበር መጥታ ግቢው ውስጥ ቆመች:: ሴቷ ወታደር በበኩሏ አስረኞችን ወደ ከፍላቸው ቶሎ እንዲገቡ ማጣደፍ ያዘች:: ሁሉም ሰጋትና ጭንቀት በወጠረው አዕምሮ እየተወለካከፉ ሄደው ከዚያ ከመሬት በታች ከሚመስል ማጎሪያቸ ከፍላቸው ውስጥ ገቡ:: ያ ከባድ የብረት በር «ጓ» ብሎ አላያቸው ላይ ተዘጋ::

«አቤት! ከዚች ሰፊ ዓለም ውስጥ ወጥቶ በጠባቧ የለው መዳፍ ስር መውደቅ እንዴት ይከብዳል! እንዴት ይጨንቃል!» አለች በውስጧ ትሩፋት:: ከባዱን የብረት በር እየተመለከተች:: እላያቸው ላይ በአንዲት ሴት ወታደር በኃይል ተወርውሮ ሲዘጋ የሚያሰማውን ከባድ ድምጽ አትወደውም:: እሷ ብቻ አይደለችም ሁሉም አስረኛ ይጠላዋል::

መሽቶ በነጋ ቁጥር በእስረኛው ልብ ውስጥ የሚብላላው ትልቁ ጭንቀት ደግሞ የአለቱ ተረኛ ተመርማሪ ማን ሲሆን እንደሚችል ማሰቡ ነው:: «እኔ እሆን? እኔ እሆን?» የሚለው ጥያቄ የሁሉም ሰጋት ነው:: በተለይ የምርመራ ጣጣቸውን ጨርሰው ያልፈረሙ እስረኞች ከቶርቸሩ በፊት በጭንቀት የሚገላቸው ይሄ ሀሳብ ነው:: ትሩፋትና ራሄል ከመጡ ከሳምንት በላይ የቆዩ ቢሆንም አስካሁን ለምርመራ አልተጠሩም:: የታሰሩበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ገና አላወቁም:: በፀረ-አብዮተኛነት ሊሆን እንደሚችል ግን ወጣትነታቸው ራሱ በቂ ነው::

የስም ዝርዝሩን በእጁ አስቀድሞ ወደ ሴቶች ከፍል የገባው ወታደር ገና ሲያዩት ያስፈራል:: አራስ ነብር እንደ መሰለ ሰም መጥራት ጀመረ:: የመጀመሪያዋ ተጠሪ ትሩፋት ነበረች:: ተነስታ ስትቆም ዐይኑ ያረፈው ከገፋ ሆዷ ላይ ነበር:: የመገረም ይሁን የመቆጣት ወይ የማዘን ባለየለት ሁኔታ ካስተዋላት በኋላ አንድ የሌላ እስረኛ ስም ጠርቶ ሁለቱን አስከትሎ ከፍሉን ለቆ ወጣ:: ትሩፋት ስትሄድ ራሒልን ዘወር ብላ አየቻት:: ራሒል አፏን በሁለት እጇ አፍን እድርጋ ይዛለች:: ዐይኗ ላይም ውሀ ሞልቶ ነበር:: ትሩፋት «በርቺ» እንደ ማለት ዓይነት ግንባሯን ቋጥራ እጇን ከሆዷ በታች አድርጋ በአውራ ጣቷ ምልክት አሳይታት ወጣች::

መኪናዋ ሽቅብ ወደ ፒያሳ በረረች:: አንድ ረጅም የድንጋይ አጥር ካለው ግቢ ስትደርስ ትልቅ ጥቁር የብረት በር ተከፈና ወደ ውስጥ ዘለቀች:: ትሩፋትና ሴላዋ አስረኛ ከመኪናዋ ወርደው ይዟቸው በመጣው ቁጡ ወታደር እየተመሩ ወደ አንድ ከፍል ተወሰዱ:: ትሩፋት ውጭ እንድትቆይ ተደረገ:: ልጅቷ ብቻ እንደ ተረበሸች ወደ ምርመራ ከፍሉ ገባች:: ግቢው በር ላይ ያሉት የጥበቃ ወታደሮች ዓይናቸውን ከገፋው የትሩፋት ሆድ ላይ አሳረፉ:: ግር እንዳላት ባለችበት ቆመች:: ለጥበቃ ይዘዋወሩ ከነበሩት ወታደሮች አንዱ ወንበር ሰጣትና ተቀመጠች:: ባታ ወህኒ ቤት ከገባች አንስቶ እንደዚህ ወታደር በሀዘኔታ ያያት አንድም ወታደር አልነበረም:: ወንበሩ ላይ ተቀምጣ ምን ልትጠየቅ እንደምትችል ማሰላሰል ያዘች:: ለማታውቀው ጥያቄ መልስ በማዘጋጀት ላይ እያለች ድንገት ፊት ለፊቷ ካለው ከፍል ጀርባ ከፍተኛ የሆነ የስቃይ ድምጽ ሰማች:: በድንጋጤና በጭንቀት ተውጣ ያን ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ድምጽ ስታዳምጥ ይበልጥ ተረበሸች:: ሆዷ ውስጥ ያለው ሽል ጭንቀቷ የተጋባበት ይመስል ከለበሰችው የእርጉዝ ልብስ በላይ አስኪታይ ድረስ በኃይል ተገላበጠ:: ራሷን አዞራት:: አጥወለወላት:: የተቀመጠችበትን ወንበር በሁለት እጇ ጥርቅም አድርጋ ያዘች:: ትንሽ ቆይቶ ያ የስቃይ ድምጽ የታፈነ መሰሎ መጨረሻ ላይ ጸጥ አለ:: ከቆይታ በኋላ ያየችው ግን ከው ብላ እንድትደነግጥ አድርጓታል::

«ተሰፋዬ ነው! አዎ! ያለጥርጥር ተሰፋዬ ነው» አለች በውስጧ:: እንዳይሆን ሆኖ ተደብድቧል:: የማይደማ የሰውነት ከፍል የለውም:: ሄዳ ብትደግፈው -- አይዞህ ብትለው በወደደች:: ጨሃ ማልቀስ አማራት:: ግን ሁሉም አይፈቀድም::

ተሰፋዬና ትሩፋት የሚተዋወቁት ደብረታቦር ነው:: ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ትምህርት ቤት አብረው ተምረዋል:: እሷ ከአስረኛ ከፍል ለመምህራን ኮርስ ስትሄድ የእድገት በኅብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ሳያገኛት ቀረ:: ተሰፋዬ ደግሞ አስራ አንደኛ ከፍል ላይ የሚወሰደውን የማኅበራዊ ኑሮ እድገት ፈተና ተፈትኖ አዋሳ ተመድቦ ነበር:: ከመመረቁ በፊት ዘመቻው አገኘውና ዘመተ:: ጅማ ተመድቦ እንደ ነበር ታውቃለች:: እድገት በኅብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻው ውስጥ ተማሪዎችን በማስተባበር ከፍተኛ ተሳትፎ እንደ ነበረው ሰምታለች:: ከዘመቻ አቋርጦ ከተመለሰ በኋላም ተገናኝተው ነበር:: ያን ጊዜ የድሮው ተጫዋቹና ቀልደኛው ተሰፋዬ አለመሆኑን አስተውላለች:: ወሬው ሁሉ ቁም ነገር

ያዘለና በዚህም ሆነ በዚያ ሄዶ ማላረጊያው «ሕዝባዊ መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስፈልጋል» የሚል እንደ ነበር ተገንዝባለች:: መንግሥት ዘመቻ ያቋረጡ ዘማቾች ሁሉ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ሲያደርግ ተስፋዬም ወደ አዋሳ ተመለሰ:: ትምህርቱን አጠናቆ ተመረቀ:: ጎንደር ዙሪያ በግብርና መስሪያ ቤት ተመድቦ እየሰራ ነበር:: አሁን ደግሞ ይኸው ከፊቷ በደም ተነክሮ መሬት ላይ ተዘርሯል:: በዚህ ጭንቀትና ውጥረት ውስጥ እያለች ስሟ ተጠራና በደመነብስ እየተደነባበረች ሄደች::

ከውጭ ሲገቡ ክፍሉ ይጨልማል:: ወለሉ ዝቅ ያለ በመሆኑ ደግሞ ትሩፋት ስትገባ የበሩን መቃ ቶሎ ባትይዝ ኖሮ ባፍ ጢሟ ተደፍታ ነበር:: ከጠባቧ ወለል ማህል ላይ ከከባድ እንጨት የተሰራና በወጉ ያለሰለሰ ጠረጴዛ ተቀምጧል:: ከጠረጴዛው ኋላ ዩኒፎርም የለበሰው መርማሪ ወታደር ወረቀትና እስክርቢቶ አዘጋጅቶ ይጠብቃል:: ትሩፋት ስትገባ ፊት ለፊት ካለው ወንበር እንድትቀመጥ በጁ ምልክት አሳያት:: ተቀምጣ ሁሉ ተስፋዬ ከፊቷ አልሄድልሽ አላት:: በደም የተነከረው አካሉ—— ያሰማው የነበረው ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ድምጹ ታሰባት:: እዚህ ቦታ ተገኝታ ተስፋዬን እንዲህ ተጎድቶና ተጎሳቁሎ እያየችው ምንም ልታደርግለት ባለመቻሏ ልቧ ቆሰለች:: ተስፋዬ፣ አገሬ፣ ፍቅርተ፣ እሷና ራሔል... ሌሎችም እልፍ አላፍ ወጣቶች የሚታገሉት የተሻለች--- ያደገች--- የበለጸገችና ፍትህ የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለማምጣት ነበር:: ይህን ሁሉ ግፍና ስቃይ እንዲቀበሉ ለምን ይፈረድባቸዋል? አንጀቷ በሀዘን ተኮማተረ:: በዚች ገና የመከራ ጉዞዋ ባላለቀላት አገር ውስጥ ሌላ ፍጡር ለማምጣት መንገድ ላይ በመሆኗ ተፀፀተች:: ከሐሳቧ ስትመለስ ስትገባ ያላስተዋለችው አብራት የመጣችው ልጅ ነፍሷን ስታ ከክፍሉ አንድ ጥግ ላይ ተጥላለች::

«ልጅሽን በሰላም ወልደሽ ማሳደግ የምትፈልጊ ከሆነ የሆነውን ሁሉ አንድም ሳትደብቂ ዘርዝረሽ ተናገሪ:: አብዮታዊ መንግስታችን መሀሪ ነው ይምርሻል:: በማያዋጣ ዲስፕሊን ከገገምሽ ግን ልጅሽንም ራስሽንም ታጫለሽ:: የአብዮት ሰይፍ ይበላችኋል::» የመርማሪው የሚያስገመግም ድምጽ ልጅቷ ላይ በሀዘን ጥላው የነበረውን ዐይኗንና ሐሳቧን እንድትመልስ አደረጋት::

«የማውቀው ነገር ካለ እናገራለሁ:: ለምን እደብቃለሁ?» አለች ወግተው የሚያዩዋትን አይኖቹን እየሸሸች::

«የሰራሽውን ሥራ መች አጣሽውና ነው የማታውቂው ነገር የሚኖረው? እንበላሜ ከተማ ከነማን ጋር ሆነሽ ነው በአብዮታዊ ጓዶቻችንን ላይ ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ እስከ መስጠት ደረጃ የደረሳችሁት? የተጠናከረ ፀረ-አብዮት ኃይል መኖር አለበት:: ካንቺ የሚጠበቀው ይህን ፀረ-አብዮት ኃይል ለመንግሥት አጋልጦ መስጠት ነው:: ይህን ግዴታ ከተወጣሽ ሁሉም ነገር በሰላም ተጠናቀቀ ማለት ነው» አላት አትኩሮ እየተመለከታት::

«ያለዚያ በራስሽ ላይም ሆነ ሆድሽ ውስጥ ባለው ልጅሽ ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ነገር ኃላፊነቱ የራስሽ ይሆናል» አላት አከሎ:: ትሩፋት ድን---ግጥ! አለች::

«የወረዳው ተላላኪ እኮ ጆሮ ነው!»

«ለምን ማስጠንቀቂያ አይሰጠውም?.....» ከመርማሪው ማስፈራሪያ በኋላ በጆሮዋ ያስተጋቡት እነዚህ ምልልሶች ነበሩ::

«ሁሉም ነገር ሰላም እንዲሆንልሽ ከፈለግሽ በጓዶቻችን ላይ ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ እንድትጽፊ ያደረገሽን ኃይል በሙሉ ማጋለጥ ይጠበቅብሻል» አላት መርማሪው ጠንከር አድርጎ::

«የምን ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ?» አለች ከድንጋጤዋ ሳትወጣ::

«ለወረዳው ፖሊስ ዋና እዛዥና ለአስተዳደሩ ተላላኪ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ የጻፍሽው አንቺ መሆንሽን ለመካድ ነው? ምን ዓይነቷ ደፋርና አይናውጣ ነሽ እባክሽ!?» አላት ዐይኑን እያጉረጠረጠ:: ትሩፋት ያልጠበቀችው ጉድ ገጠማት::

«እውነት ነው የምናገረው:: ስለተባለው ነገር የማውቀው ምንም ነገር የለም» አለች ትሩፋት:: መገረምም — መደንገጥም ፊቷ ላይ እየተነበበ::

«ኧረ እባክሽ! አሃሃሃ! አታውቂም አይደል!? ተይ አንጂ! አሃሃሃ—— አሃሃሃ!» ከጣራ በላይ ሳቀ:: «ማሾፍሽን ተይና ይልቅስ በመግባባት ብንሰራ የሚበጀው ለአንቺው ነው:: በሆድሽ ለለተሸከምሽው ጽንስ እንኳ ስትይ የአናርኪስት ቀልድሽን ብታቆሚ ይሻልሻል!» አላት አሁንም በዛቻ::

«በፍጹም አልቀለድኩም! ለነዚህ ሁለት ሰዎች ተሰጠ ስለሚባለው ማስጠንቀቂያ የሰማሁት እንደማንኛውም የእንበሳሜ ኗሪ ነው:: በእውነት ነው የምናገረው ማን እንደ ጻፈባቸው የማውቀው ነገር የለም» አለች ትሩፋት ደግማ:: ንግግሯ መርማሪ ወታደሩን ለማሳመን አቅም አልነበረውም::

«ኧ---ረ! ተ--ይ እንጂ! እውነትሽን ነው!?» ሲል አሾፈ:: ቀጠል አደረገና «አንቺ የጻፍሽው ለመሆኑ የእጅ አሻራሽ መስክሯል:: ልትክጂ አትችይም:: ሳይንሳዊ በሆነ ምርመራ በመሳርያ ተረጋግጧል:: አሁንስ ምን መልስ ይኖርሻል?» አላት:: ከህደቷ እያናደደው:: ትሩፋት ምን ብላ ትመልስ? ምንስ ማሳመኛ ነጥብ ልታመጣ ትችላለች? ዝም አለች::

«አሁን ከአንቺ የሚጠበቀው ተባባሪዎችሽ እነማን እንደሆኑ ማጋለጥ ብቻ ነው:: ሌላው ጉዳይ በሳይንሳዊ ምርመራ በማስረጃ የተደገፈ ስለሆነ ያንችን እምነት ከህደት የሚጠይቅ

አይደለም:: ይልቅ ለዚህ ፀረ-አብዮት ድርጊት ተባባሪዎችሽ እነማን ነበሩ?» አላት ተቆጥቶ::

«አባሪም ተባባሪም የለኝም:: ድርጊቱንም እኔ አልፈጸምኩም» አለች ፍርጥም ብላ::

«ለትለመኝ እንቢ ካልሽና ከብር ካልወደደልሽ በምርመራ ተገደሽ ታወጫለሽ:: እባሎቻችሁ ሁሉ እንዲሁ ነው የሚያደርጉት፡ በኋላ በግዳቸው ማመናቸው ላይቀር መጀመርያ ላይ ግግም ይላሉ::» አላት በንቀት እያስተዋላት:: ዝም ብላ የሚቀጥለውን ጠበቀች::

«እውነቱን ብታወጭ ይሻልሻል! ነፍሰጡር መሆንሽ ፀረ-አብዮተኛነትሽን ለመሸፈኛነት የሚያገለግልሽ መስሎሽ ከሆነ ተሳስተሻል:: ለአብዮታችን ጉዞ እንቅፋት የሆነ ሁሉ በአብዮት ሰይፍ ይወገዳል:: እርጉዝ ምናምን ብሎ ነገር አይሰራም:: ከሁሉም በላይ አብዮቱ! » አላት ግራ እጁን ወደ ላይ አንስቶ::

«ብበኩሌ የሰራሁት ወንጀል የለም» አለች ትሩፋት እንደማያምናት ብታውቅም::

«ኧረ አባክሽ! የመሳሪያ ምላጭ እስከትሰቢ ነበራ የምንጠብቅሽ! የማናት ፈጣጣ አባካችሁ!! ቶሎ - ውሰዱና ለጥብስ አድርሷት:: ከብር ካልወደደልሽ እንዴት ማጋለጥ እንዳለብሽ እናሳይሻለን» ከማለቱ ሁለት ወጠምሻ ወጠምሻ ወታደሮች ገብተው ከንድና ከንዷን ይዘው አፈፍ አደረጓት::

«ብሉ ገመዱን ልትበጥለው ስለምትችል አትስቀሏት:: ሁለት ሰው በአንዴ መሸከም አይችልም:: እጇን ከአግዳሚው ወንበር ጋር ጠፍራችሁ አሰሯትና አንበርከካችሁ «በአናገረች» ጥሩ አድርጋችሁ እናሏት:: 'እናገራለሁ፤ አጋልጣለሁ' እስከትል ድረስ ቂጥ ቂጧን ለብልቡልኝ» አላቸው:: ከዚያው ከፍል ውስጥ ሆኖ ሌላ ጉሮኖ ከመሰለ ከፍል ውስጥ ይዘዋት ሲኪገቡ አሳደርስ ብሏቸው ሁለቱም እየተቀባበሉ ፊቷ እስኪነድ ድረስ በጥፊ አጮሏት:: ልትወድቅ ስትል እየቀለቡ አንገላቷት:: እኳን ለነፍስጡር ሴት ለሴጣም ሴት ቢሆን የማይገባ ነበር:: መቀመጥና መተኛት ቀርቶ ልብሰ እንኳን መልመስ እስኪያቅጣት ድረለ ከወገቧ በታች ቆሳስላ ነበር:: ልብሷ ከቁሰሉ ጋር እየተጣበቀ አልላቀቅ እያለ እንደ .ገና እየቆሰለ ብዙ ቀን አሰቃያት:: የራሔል የትሩፋትን እልህ ሁሉ ነበር የተወጡባት:: ለነገሩ ለትሩፋትም የቀረላት የወፌላላው ለቅላት ብቻ ነበር:: ሁለቱ እትማማቾች ብዙ ጊዜ ምርምራ ከፍል እየተወሰዱ ይህ ነው የማይባል ሰቃይ ተቀበሉ::

******

«ለሽንት ቤት ተዘጋጁ!» እንደ መብረቅ ነበር የጮኸችው ወታደር ቀለሟ:: ከተለመደው መውጫ ሰዓት ቀደም ብሎ ለለ ነበር እስረኞቹ ሁሉ ብርከ ያዛቸው::

«ቶሎ ውጡ! ምን እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ ይጎትታችኋል? መውጣት ካልፈለጋችሁ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ መብታችሁ የተጠበቀ ነው:: በሩን እቆልፈዋለሁ» አለች:: ቤት እስረኛውን ሁሉ ታሽቆጠቁጣለች:: እስረኞቹ «ትንሿ መላኩ» ይሏታል:: ሁሉም እስረኛ እሷ ተረኛ የማትሆንበትን ቀን አጥብቆ ይናፍቃል:: አድራጎቷ ሁሉ በሰው ሰቃይ የምትደሰት ያስመለልባታል:: ለከፋቱ በዚህ የጭንቅ ቀንና ሰዓት ደግሞ እሷ ተረኛ መሆኗ:: እንደ ያዘችው ቆመጥ ጥምልል ያለውን እካሏን እያንከባለለች ወፍራሙን የብረት በር ለመዝጋት ስትቻኮል አንዳንዶቹ በደመነብስ ወደ በሩ ተራመዱ:: ከሽንት ቤት መልሰ ለትንሽ ጊዜ ውጭ መቆየት የተለመደ ቢሆንም ዛሬ አልተፈቀደም:: ወታደር ቀለሟ ወደ ከፍላቸው እንዲገቡ አጣድፋ ወፍራሙን የብረት በር እላያቸዉ ላይ ዘጋችው:: የስረኞቹ የመኖር ተለፋም አብሮ ተከረቸመ:: ከአስር ለዓት በፊት እንዲህ ዓይነት ከለተት የሚፈጠረው የሚረሸኑ እስረኞች ሲኖሩ መሆኑ ከልምድ ይታወቃል:: ሞት በጥፍሩ የሚቧጥጣቸው ነብሶች እርስ በርሰ ተያዩ:: ማን ማንን ያጽናናል?? ሁሉም ለመኖር የምትቃትት ነፍሱን ከውለጥ ያዳምጣል::

ከምሽቱ አራት ሰዓት-- መላአከ--ሞት በባታ ወህኒ ቤት ጥቁር ክንፉን የዘረጋበት ምሽት:: በጨካኝ የአምባገነን የደርግ የስልጣን ጥመኛ ገዥዎች ንጹህ ነብሶች ሊቀጠፉ ጥቁር ዳመና ያንዣበበበት:: ጠባቂ መላዕከት የተጨነቁ ነብሶችን ከቀሳፊ የሞት መንጋጋ ለመከላከል ክንፎቻቸውን ያልጋረዱበት የቀን ጎደሎ! ጨካኙ የሞት መላከተኛ ባታ ወህኒ ቤት ጥቁር ሬንጀሩን ለብሶ ግቢውን የተቆጣጠረበት ጥቁር ምሽት:: በተፈጥሮዋዊው የሞት ሕግ ሳይሆን ሰው በራሱ አምሳያ በሰው እጅ ተይዞ ግባዕተ መሬቱ የተማለለት የቀን ከፉ ...

የውጭ በር ይከፈታል---ይዘጋል:: ከባድ መኪኖች መብራታቸውን አጥፍተው ግቢ ውስጥ እየገቡ ተገጠገጡ:: ፀጥ--- ረጭ ባለው ድቅድቅ ጨለማ ዳ...ዳ..ዳ....የሚል የከባድ እርምጃ ኮቴ ወደ ከፍሉ እየቀረበ መጣ:: ከባዱ የብረት በር በቀስታ ተከፈተ:: አራት ወታደሮች ከነሙሉ ትጥቃቸው በፍጥነት ገብተው የከፍሉን ጥግ ጥግ ያዙ:: መሳሪያዎቻቸውን እስረኞቹ ላይ ደግነው በተጠንቀቅ ቆሙ:: አምስተኛው ወታደር የያዘውን የስም ዝርዝር ለማንበብ እንዲያመቸው በሩ አጠገብ ርቃ ወደ ተንጠለጠለችው አንፖል አንጋጠ ተጠጋ::

«አሁን ሰማችሁን የምጠራችሁ እስረኞች ወደ ሌላ ከፍል የተዛወራችሁ ስለሆነ እንደ ተጠራችሁ እየተነሳችሁ ወደ በሩ ትጠጋላችሁ አዳምጡ!» አለ በትዕዛዝ:: ወረቀቱን ወደ አምፖሏ ከፍ አድርጎ ይዞ ስም ዝርዝር ማንበብ ጀመረ::

«አገሬ ዱባለ፣ ፍቅተ ኃይሉ፣ እልማዝ ደርቤ፣ ምሚና መሀመድ፣ አሰለፈች እንዳርጌ፣ አሰገደች ቢተዉ፣ ለተብርሃን ካህሳይ፣ሙሉመቤት ግርማ፣... የአስራ አምስት ሴት እስረኞች ስም ዝርዝር ተጠራ:: ደመወዝ እንዲጨመርላት እስሪዎቿን የጠየቀችው እስረኛም እንደ ፈራችው አልቀረላትም::

«ታጋይ ቢሞት ታጋይ ይተካል!!

በተባባረ የሕዝብ ክንድ ፋሽስቱ ደርግ ይደመሰሳል!!

ሞት ለባንዶችና ለአድርባዮች!!

ኢሕአፓ ያቸንፋል!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!»

እገሬ የጀመረችው መፈክር በሁሉም እስረኞች ተደገመ:: ያልተጠሩት እስረኞች ጭምር በስሜት አብረው ጮሁ። ከወንድ እስረኞች ክፍልም መፈክሩ---መዝሙሩ ድብልቅልቁ ወጣ:: ባታ ወህኒ ቤት በጩኸት ተናወጠች:: ከውጭ እናቶች ኡኡታውን ያቀልጡት ጀመር:: ዋይታው እገር ያሸብራል:: ጎንደር ከልጆቿ ጋር «ኡ!! ኡ!!» እለች:: በለቅሶና በሀዘን ተናጠች::

ተራቸው መቼ እንደሆነ የማያውቁት ቀሪዎቹ እስረኞች ጓደኞቻቸው ከጎናቸው እየተነጠሉ ሲሄዱ ማየቱ ራሱ በግማሽ ገሏቸዋል:: ሀዘኑ ሁለት እፍ ባለው ሹል ሰለት ልባቸውን ሲቧጥጠው እንቅልፍ በዐይናቸው ሳይዞር አደረ:: የተፈጥሮ ሂደት ነውና ጨለማው ለንጋት ቦታውን ቢለቅም የእስረኛው ልብ ግን ገና ጽልመት እንደ ለበሰ ነበር:: ከባድ የሀዘን ጨለማ እንደ ዋጠው---- ባታ ወህኒ ቤት በታሰሩት እስረኞች ላይ ብቻ ሳይሆን በጎንደር ኗሪ ልብ ውስጥ ሁሉ ጥቁሩ ደመና ገና እልተገፈፈም.....

በተለይ የእነዚያ እሳዛኝ ሴት ገበሬዎች መረሸን የሁሉንም እስረኛ አንጀት በልቷል:: ትሩፋት እንደ ሆደ ሽል ሀዘኑ ነፍስ ዘርቶ ሲገሳበጥ ተሰምቷታል:: ዐይኖቿ ቀልተው እስኪያብጡ እልቅሳላቸዋለች:: ሴቶቹ የታሰሩበትን ጉዳይ እንኳ በቅጡ ሳይገባቸው የዚህ መንግሥት አሰራር እንደ ገረማቸው-- እንደ ደነቃቸውና ነገሩ ሁሉ እንቆቅልሽ እንደ ሆነባቸው ከዓመት በላይ ታሰረው ተንገላተዋል:: የከፋው እሳዛኙ ፍጻሜያቸው ደግሞ የቀይ ሽብር ሰለባ መሆን ሆነ::

«ትሩፋት ለምን እንዲህ ትሆኛለሽ? የደርግ መንግስት በጭካኔ መረሸን የጀመረው ዛሬ ነው? ስንትና ሰንት ወጣት የቀይ ሽብር ሰለባ ሆኖ የለም እንዴ! ነገ ደሞ የኛ ተራ ሊሆን ይችላል:: በማልቀስ የምናመጣው ለውጥ የለም» እለች ራሔል:: ይህን ትበል እንጂ የሷም እንባ እየወረደ ነበር::

«አየሽ ራሄል-- እኛ ምንም ይሁን ምን ደርግን በስልጣኑ መጥተንበታል:: የተለየ ዓላማ ይዘን ተነስተን ነካክተነዋል:: እነዚህ ሁለት እሮጊት ገበሬዎች ግን ንጹሃን ናቸው:: የተወነጀሉበትን 'ጸጥታ ለማደፍረስ ቤታችሁን እቃጥላችኋል:: የኢዲዩ አባሪ ተባባሪ

ናችሁ' የሚለውን ሰንካላ ምክንያት እንኳ ምኑም ሳይገባቸውና ሳያውቁት ነው በግፍ የተረሸኑት::»

«ደርግ በግፍ በየእስፋልቱ ላይ ያሰጣው ወጣት ሁሉ አገር የተሻለችና የበለጸገች እንድትሆን፤ ፍትህ የሰፈነባትና ዲሞክራሲ ያበበባት አገር ለማድረግ ተነሳ እንጂ ሌላ ምን ወንጀል ሲሰራ ተገኝቶ ይመስልሻል ይህ ሁሉ እልቂት የደረሰበት? ይልቅስ መዘዝ እንዳታመጭ በእናትሽ ትሩፋት ዝም በይ::»

«የግፍ ሞታቸው በደርግ ላይ ያለኝን ጥላቻ እጥንቴ ድረስ ዘልቆ እንዲሰማኝ አድርጎታል:: ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? የሚያስለቅሰኝ የእነሱ ሞት ብቻ ሳይሆን በዚህ ጨካኝ መንግሥት ላይ ምንም ማድረግ እለመቻሌን ሳስብ ነው» እለች ትሩፋት እሁንም እየተንሰቀሰቀች::

«ያች እሳባቂ ወታደር ገና አልሄደችም:: እንዲህ ስትሆኚ አይታ ትነግርልሽና ሌላ ችግር ውስጥ ትገቢያለሽ፤ ዳፋው ለእኔም ይተርፋል እወቂ ትሩፊ!» እለች ራሄል በስጋት ወደ በሩ እየተመለከተች::

ያ--እዚማም ወህኒ ቤት እዚሙን ጥሎበት እስረኛው ሁሉ ቅፍፍ—ከብድ እንዳለው ሰነበተ:: እንደ መቃብር ዝምታ ፀጥ— ረ---ጭ ባለው ግቢ ውስጥ እልፎ እልፎ የሚሰማው የዚያች ከፉ ወታደር ደረቅ ሳቅና የቁራ ጩኸት ብቻ ነበር::

******

እጠር ቀጠን ያሉት የጎንደር ክፍለ ሀገር የደርግ ዋና ተጠሪና አስተዳዳሪ ከብስል ቀይ ፊታቸው ላይ ለምልክት ፈገግታ አይታይም:: መልከ መልካም ቢሆኑም ቁጥ--ር ክስ--ክስ ያለው አይታቸው ደብቆታል:: ከአካላቸው በላይ ስልጣናቸው ያገዘፋቸው ይመስላሉ:: ቆፍጠን----ኮስተር እንዳሉ ወንበራቸው ላይ በኩራት ጉብ ብለዋል:: ሲያዩዋቸው የምድሩን ብቻ ሳይሆን የሰማዩንም ዙፋን የጨበጡ ሳይመስላቸው አልቀረም:: በፍርሃት እየራደ አፊታቸው የቆመውን እስረኛ ሁሉ እንደ መርፌ በሚወጉ ትናንሽ ዐይኖቻቸው ይገላምጣሉ:: ያስቆጣቸውን ነገር መገመት ቢከብድም የተቆጣ አንበሳ መስለዋል:: ጠረጴዛው ላይ ፊት ለፊታቸው ያስቀመጡት ሽጉጥ የክፍሉን የፍርሃት ድባብ በእጥፍ አሳድጎታል:: ክፍሉ ለቢሮ መገልገያነት በቂ ቢሆንም እንደዚህ በቁጥር በዛ ያለ ሰው ለመያዝ ግን ጠባብ ነው:: እስረኛው ሁሉ ጥብቅብቅ ብሎ ቆሟል:: ከሰውየው እይታ ለመከለል ይመስላል አንዱ ከሌላው ኋላ ሊቆም ይሞክራል:: ድንገት ወደ እስረኛው ፊታቸውን መለስ አድርገው

«ከመካከላችሁ አሁን እኔን በልቡ የሚረግመኝ ሰው ይኖራል፡፡ እንደ እንቧይ ያፍርጥህ፤ እንደ አክርማ ይሰንጥቅህ የሚለኝ» አሉ፡፡ ሁሉንም በቁጣ እየገላመጡ፡፡ ትሩፋት በዚህ አባባላቸው ክት ብላ ከእንጀቷ ብትስቅ በወደደች፡፡

«ይህንን ሁሉ ግፍ እየሰሩ ሊመረቁ ፈልገው ነበር ታዲያ! የሰው ደም እኮ ያሳብዳል፡፡ ሰውየው ሰይቶላቸው አብደው ይሆን እንዴ?» አለች በስውጧ፡፡

«አንተ የጠጣ ሽማግሌ!» አሉ ቀጠሉና ድክም ወዳሉት ሽማግሌ እስረኛ አተኩረው እየተመለከቱ፡፡ ሁሉም እስረኛ ከው ብሎ ደነገጠ፡፡

«አንተ የጠጣ ሽማግሌ፤ የትልቅ ትንሽ! ፖለቲካ ከእንግዲህ ለአንተ ምንህ ነው? በዚህ እድሜህ ምን ለመሆን አስበህ ነው እማይጠቅምህ ነገር ውስጥ ገብተህ የምትፈተፍተው!?»

«ኧረ ጌታዬ! አንድ ፈጠሪ--- እሱ መድሃኒያለም በሚያውቀው ያሳበሳ.....»

«ዝም በል! ቅሌታም የአንጨት ሽበት!! አንተን ይሉ ኃይማኖተኛ! ባንተ ቤት እልተነቃብህም፡፡ አድኃሪ ኢዲዩ!» ሽማግሌው ተናግሮ የመጨረስ እድል እንኳ አላገኙም፡፡ የስድብ መዓት አወረዱባቸው፡፡ እስረኛው ሁሉ በእዛውንቱ ላይ በደረሰው የስብዕና መዋረድ ተቆጨ፡፡ ተወልደው---- አድገው ይኑስም ይብዛ ለዚች አገር የአቅማቸውን አበርክተው እድሜያቸውን ጨርሰዋል፡፡ ልጃቸው በሚሆን ሰው እንዲህ በተራ ስድብ መብጠልጠላቸው እዚያ የቆመውን እስረኛ ሁሉ በጣም አሳዘነ፡፡ የትሩፋት ልብ ደግሞ ከማዘንም እልፋ ቆስላ እየደማች ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በሚፈጽሙት ግፍና በሚያሳዩት ንቀት እሳት ከላይ ከሰማይ ወርዶ ባለመፍጀቱ በአግዜሩ ትዕግስት ከመገረም ይልቅ አዘነች ትሩፋት፡፡

«እርምህን አውጣ፡፡ ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ምድር የዘውድ እገዛዝ ዳግም ነፍስ እይዘራም፡፡ አጉል በናፍቆት ተንገብግበህ ትምታታለህ እንጂ ከአሁን በኋላ ፊውዳሊዝም ሞቶ ተቀብሯል፡፡ በመቃብሩ ላይ ደግሞ ሶሻሊዝም ያብባል፡፡ በቆራጡ መሪያችን ብልህ አመራር እብዮቱ ግስጋሴውን ቀጥሏል» አሉ አይታቸውን ከሽማግሌው ላይ ሳያነሱ፡፡

«ከእንግዲህ የማስጠነቅቅህ ነገር ቢኖር እንተ መቃብርህ የተማሰ--- ልጥህ የተራሰ ሰው ነህ፡፡ እሰሁ ሰማለት ብትንፈራገጥም አንድ እግርህ እኮ መቃብር ገብቷል፡፡ ልትሞት አንድ ሀሙስ የቀረህ ሽማግሌ ሰው ነህ፡፡ እርፈህ የሰላም ሞትህን ብትሞት ይሻልሃል፡፡» ሽማግሌው ለጥ ብለው እጅ ነሱ፡፡ ምን ያድርጉ? ሐሳብን የመግለጽ እድል አይደለም ሆድ ውስጥ ምን እለ ብለው ጠርጥረው ግስላ ከሚሆኑ ሰውዬ ፊት ነው የቀረቡት፡፡ ማን መልስ ይሰጣል? ዝም ብሎ ማዳመጥ ብቻ!!

ከመቀመጫቸው ተነስተው መንጎራደድ ጀመሩ፡፡ በትረ ስልጣን ዱላቸውን በቀኝ እጃቸው ይዘው ግራ እጃቸውን ይጠበጥቡ ገቡ፡፡ እንደ እራስ ነብር ከወዲያ ወዲህ ይንቆራጠጡ ጀመር፡፡ ከእሳቸው ድምጽ በስተቀር ምርፌ ብትወድቅ ትሰማለች፡፡ ካሰኛቸው እኮ ከፊታቸው እየተንቀጠቀጠ የቆመውን እስረኛ ሁሉ ጠረጴዛቸው ላይ ያለውን ሽጉጥ አንስተው ግንባር ግንባሩን ሊበረቅሱት ይችላሉ፡፡ የጦር መሳሪያ እጅ ውስጥ ካለ ምን የማይገኝ መብት አለ? ባለስልጣኑ ያሻቸውን ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ የተናገሩት ነገር ሁሉ ደግሞ መሬት ጠብ የማይል እውነት ነው፡፡ ማን ደፍሮ ያስተባብላል? የጦር መሳሪያ በእውቀት ያመጥቃል፤ ከበርቴ ያደርጋል፤ እንደ ልብ ያናግራል፡፡ ትክክለኛው እሳቸውና እሳቸው ብቻ ናቸው፡፡ እድሜ ለሽጉጥ፡፡

«አንተስ ገና ቂጥህን በወጉ ሳትጠርግ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ እንድትሆን ማን ነው የመለመለህ!? ማናባክ ነው ያሰለጠነህ!? የከረሜላ ነው ወይስ ያሻንጉሊት መግዣ የሰጡህ?» አሉ ወደ ሕጻኑ ልጅ እስረኛ ዞረው፡፡

«ኧረ እኔ እባቴ ይሙት! ማንም ገንዘብና አሻንጉሊት.....»

«ዝም በል! ውሸታም! ታድያ የትኛውን ርዕዮተ-ዓለም እውቀህ ነው እሁን አንተ? ገና ከመሬት ሳትነሳ ቅጥር ነፍሰ ገዳይ የሆንከው፡፡ በገንዘብ ደልለውህ ነው እንጂ!»

«እናቴ ትሙት! ማርያምን! ምንም ሳላደርግ....»

«ዝም በል ብያለሁ አንት ባለጌ ፈልፈላ! ዳኑ ባንተ አይፈረድም፡፡ በገንዘብ ተታለህ እሳት ውስጥ ስትማገድ ዝም ብለው ያዩ ወላጆችህን ነበር እዚህ አምጥቶ እርባ መግረፍ! አንተን የመሰለ ውሪ ሁሉ ከእንዲህ ያለ የአገር ጥፋት ውስጥ እንዳይገባ መቀጣጫ እንድትሆን አንገትህን ለገመድ መዳረግ ነበር! አስፈራጅ!» አሉ በቁጣ እየተመለከቱት፡፡

«አባቴ ይሙት! ምንም አላደረኩም፡፡ እንትን—እ---የዶሮ ቤት ልሠራ ቆርቆሮ ለመታ ነው የያዙኝ ሌላ ምንም አላደረኩም፡፡ማርያምን እውነ....» ሳግ እየተናነቀው ተናገረ፡፡ በንዴትና በስድብ አቋረጡት፡፡

«ቀጣፊ--ሞላጫ!! 'ደግሞ የዶሮ ቤት ለሠራ ነው' ይለኛል! ለውሸትማ ማን ብሏችሁ? የአናርኪስት እይነተኛ መሰያው ውሸት---ቅጥፈትና---ስርቆት ነው፡፡ አንት ዋሾ! ግልገል ኢህአፓ! ለአንተም ያንኑ ውሸታቸውን ነው ያጠመቁህ» አስር ዓመት ገደማ የሚሆነው ይኸው ልጅ እንባው ዱብ ዱብ አለ፡፡ እስረኛው ሁሉ ለጊዜው የራሱን ጭንቀት ትቶ ለዚህ ሕጻን ልጅ አዘነለት፡፡ ከንፈሩን በውስጡ መጠጠለት፡፡

ትሩፋት «የምናካሂደው የለውጥ ትግል ሰምሮ እምባገነኖች የማይፈነጩበት አገር ተገንብታ ልጅ ተወልዶ ያድግ ይሆን?» እያለች የወደፊቷን ነፃይቱን ኢትዮጵያ በማሰብ ላይ እያለች

የተቆጣው የአስተዳዳሪው ድምጽ ከተጓዘችበት የሐሳብ ጉዞ ደንግጣ እንድትመለስ አደረጋት፡፡

«አሁን ማ ይሙት በማን ለማስፈረድ ነው ሆድሽን እንዲህ የራስ ዳሽንን ተራራ አሳክለሽ ፀረ-አብዮት ካምፕ ውስጥ የገባሽው አንች ደግሞ!?» አሉ ወደ ትሩፋት እየተመለከቱ፡፡ ቀጠሉና «ጊዜው የአብዮት ነው። ሂደቱን ለማደናቀፍ ለመጣ ሁሉ ምህረት አናደርግም፡፡ እርጉዝ—እመጫት ብሎ ነገር አይሰራም፡፡ እርፊሽ በሰላም ልጅሽን ወልደሽ ብታሳድጊ ይሻልሻል፡፡»

ትሩፋት እንገቷን ደፍታ ዝም አለች፡፡ መልስ ሊሰጡ የሞከሩ አዛውንቱ እስረኛና ሕጻኑ ልጅ ምን እንደ ደረሰባቸው አይታለች፡፡ ያሉትን ይበሉ እንጂ ትሩፋት ቃል ትንፍስ እንደማትል ለራሷ ነግራ አንገቷን ደፍታ ቆማለች፡፡ ሀቀኛው አብዮታዊ መሪ ሲፈልጉ ስድብ-- ሲያሻቸውም ዛቻ በብቸኝነት ያወርዱታል፡፡

«ዘውድ ናፋቂ አድሀሪው ኢድዩ—ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳዩ ኢሕአፓ--- የኤርትራና የትግራይ ጠባብ ቡድን ገንጣይና አስገንጣይ ወንበዴ ሁሉ በአብዮታችን ላይ ቢነሱ በቆራጡ አብዮታዊ መሪያችን ብስለት በተሞላበት አመራርና በሰፊው ሕዝብ ክንድ ይደመሰሳሉ! አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል!» አሉ በኩራት፡፡ ለትንሽ ጊዜ ከተንጎራደዱ በኋላ ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡

«በፀረ አብዮተኛነት የተነሱትን ሁሉ እየጠራረገ ባቡሩ ጉዞውን ቀጥሏል፡፡ የሚያቆመው ምንም ኃይል አይኖርም፡፡ ምንጊዜም ጠላቶቻችን ለምሳ ሲያስቡን እኛ ለቁርስ እናደርሳቸዋለን፡፡ መሰረታችን ሰፊው ሕዝብ መመሪያችን እውነተኛው የሶሻሊስት አብዮት ነውና፡፡ እኛም ከጭቁኑ ሕዝብ አብራክ የተገኘን በመሆናችን ባሸናፊነት እንደምንወጣ ለአፍታ እንኳ አንጠራጠርም፡፡ ለሥልጣን በቋመጡ ፀረ-አብዮተኞች ከንቱ ፕሮፓጋንዳ አትወናበዱ፡፡ ይልቅስ ባቡሩ ፈጣን ነው፡፡ ያልተሳፈረበትን ሁሉ በብረት ጎማው እየደፈጠጠ ይጓዛል፡፡ ጨፍልቋችሁ ከማለፉ በፊት መሳፈሩ የራሳችሁ ምርጫ ይሆናል፡፡ መንግሥት ሆደ ሰፊ ነው፡፡ መንግሥት መሐሪና ይቅር ባይ ነው፡፡ በመሆኑም ያላችሁን የንቃተ ሕሊና ዝቅተኛነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለዛሬው ምህረት አድርገንላችኋል» ሲሉ እስረኛው ሁሉ መሬት እስኪነካ ለጥ ብሎ እጅ ቢነሳ በወደደ ነበር የከፍሏ መጥበብ መሬት አላስደረሰችም እንጂ፡፡

«ሆኖም! አጥብቀን የምናስጠነቅቃችሁ ነገር ቢኖር ሳታውቁ በንቃተ-ሕሊና ማነስ ምክንያት ያደማችሁትን አብዮት አቅማችሁ በሚፈቅደው ሁሉ የመካስ ግዴታ አለባችሁ፡፡ ከአሁን በኋላ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በፀረ-አብዮት ካምፕ ተሰልፋችሁ ብትገኙ በራሳችሁ ላይ የሞት ፍርድ እንደ በየናችሁ ቁጠሩት፡፡ ወደ የቦታችሁ ከመበታተናችሁ በፊት ንቃተ—

ሕሊናችሁን ለማሳደግ የአስራ አምስት ቀን አብዮታዊ ስልጠና ትወስዳላችሁ» ሲሉ እስር ቤት የሚቆይ መስሎት እስረኛው ሁሉ ኩምሽሽ አለ፡፡

«ንቃቱን የምትወስዱት ከነገ ጀምሮ ይሆናል፡፡ ቦታው ሲኒማ አዳራሽ ነው፡፡ ከምታርፉበት ቦታ እርፋችሁ ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት የመገኘት ግዴታ አለባችሁ» ሲሉ በስጋት ጉሮሮዋቸው ላይ ተሰንቅራ የነበረችው የእስረኛው ሁሉ ልብ በእፎይታ ከቦታዋ ተመለሰች፡፡ የጎንደሩ ዋና አስተዳዳሪ ግራ እጃቸውን ብድግ አድርገው በመፈክር ንግግራቸውን አሳረጉ፡፡

«ኢምፔሪያሊዝም ይውደም!! ልክ እንደሳቸው እስረኛው ሁሉ የግራ እጁን ቡጢ ጨብጦ እንደ ችቦ ወደ ላይ ሰቅሎ መልሶ በእርግማን እያወረደ እንደ ዘፈን አውራጅና ተቀባይ መፈክሩን አስተጋባ፡፡

አድሃሪው ኢዲዩ፣ ቅጥር ነፍሰ-ገዳዩ ኢሕአፓ፣ ጠባብ ብሔርተኞች ኦነግ፣ ጀብሀ፣ ሻብያና ሕወሀት በተባበረ የሕዝብ ክንድ ይደመሰሳሉ!!

«ይደመሰሳሉ!! አለ እስረኛው በኅብረት፡፡

«ከጓድ ሊቀመንበር ቆራጥ አመራር ጋር ወደፊት!!»

«ወደፊት!!»

ኢትዮጵያ ትቅደም!!

«ኢትዮጵያ ትቅደም!!»

«እናሸንፋለን!!

«እናሸንፋለን!»

ከአስተዳዳሪው ጽሕፈት ቤት መውጣት ሲፈቀድ ሁሉም የየራሱን ጥላ ባለማመን ሹ--ክክ እያለ ነበር የወጣው፡፡ የጓጉለት ንፁህ አየር ግን ውጭም አልነበረም፡፡ የደስ ደስ የነበራት ጎንደር በሞቀ ፈገግታዋ አልተቀበለቻቸውም፡፡ የፖለቲካው አየር እሷንም ከብድ ብሏት አኩርፋለች— ከልጆቿ ጋር፡፡

******

ፍንትው ብላ የወጣችው ሙሉ የምሽት ጨረቃ ከጠራው ሰማይ ላይ እንደ ፈርጥ ትፈልቃለች፡፡ እንደ ወትሮው ቢሆን ኖሮ ጎንደር ላይ በዚች ጨፍ በምታስለቅም ጨረቃ ስንት ጨዋታ ነበር፡፡ ጎረቤቱ ሁሉ ውጭ ይሰባሰብና እንደ ኢድሜ ተዋረዱ ወጉን እየሰለቀ

ይዝናናባት ነበር:: በዚች ውብ የጨረቃ ምሽት እዛውንቶች ያለፈ ትዝታቸውን እየተረኩ ወደ ኋላ ይጓዙ ነበር:: ጎረምሶች የልጃገረዶችን ቀልብ ለመሳብ ትግል በመግጠምና የከንድ ንጥቂያ በማድረግ ጉልበታቸውን ይፈታተኑባት ነበር:: ተረት ተረት--እንቆቅልሽ---እንካ ሰላንትያ የመሳሰሉት ጠያቂ ጨዋታዎች የሚጥሙት እንዲህ በጠራች ሙሉ ጨረቃ ውጭ ከቤት ታዛ ተቀምጠው ሲጨወቱት ነበር:: ቀልዱ--ብሽሽቁ ሁሉ የሚጥመው በሙሉ የምሽት ጨረቃ ጊዜ ነበር:: ዛሬ ግን ሁሉም በየቤቱ ተከቷል:: ምድጃው ሥር አንገቱን ደፍቶ ይቆዝማል:: ዛሬ ጨረቃ ብቻዋን ደምቃለች:: በቀልድ-- በጨዋታ-- በሳቅ ያጀባት የለም:: ያ ልብን ንሁልል የሚያደርገው ምትሀታዊ ውበቷና ቀዝቃዛ ብርሀኗ ከላይ ቢፈለም ልብ ያለው አልነበረም:: ጎንደር ላይ ሁሉም ነገር «ነበር» ሆኖ ቀርቷል:: እድሜ ለአብዮት.....!

«እስከ አፍጢሙ የታጠቀው ፋሽስቱ ደርግ በሕዝብ ክንድ ይደመሰሳል» አለ ድልነሳ:: በእህቶቹ መፈታት ደስ ብሎታል:: እነሱ በፀረ-አብዮተኛነት ተይዘው ወደ ጎንደር ሲነዱ እሱ ማታውኑ ሀሙሲትን ለቆ አደረ::

«እናቸንፋለን!!» አለ እያዩ ክድሴ ቀበል አድርጎ::

«በጦር መሳሪያ ጋጋታና በኃይል የሕዝብ አመፅ አይገታም!» አለ ድልነሳ ደገመና:: ገና ሙሉ ለሙሉ እፍላ ጉርምስና ላይ እንኳን ያልደረሰችው ልቡ በወኔ ተሞልታ::

«እናቸንፋለን!» አለ እያዩ አሁንም ግራ እጁን ጨብጦ ወደ ላይ እያነሳ::

«እንቺ ለምሳ ስታሰቢያቸው እነሱ ለቁርስ ያደርሱሻል» አለች ራሔል የኒያን ከሰታራ የደርግ ባለሰልጣን ንግግር እስታውሳ:: በወፌላላ ግርፋት የቆሰለው እጅና እግሯ ገና እልዳነም:: እብጠቱም ብዙ እልጎደለም::

«እራት ብሉና ውጡ ሂዱ:: ጨረቃ በመሆኗ ነው እንጂ ጊዜው መሽቷል» አሉ የእያዩ እናት:: ከጎንደር ከተማ ውጭ ከሌላ ቦታ የሚመጡ ተማሪዎችን በመቀለብ ይተዳደራሉ:: ከባላቸው ጋር ተፋተው ሁለት ልጆቻቸውን በብቸኝነት ያሳድጋሉ:: እያዩንና መለረትን:: ድልነሳም በዚሁ በቅለባው ሰበብ ገብቶ ቤተኛ ሆኗል:: የእድሜ እኩያሞች በመሆናቸው ድልነሳና እያዩ ጓደኛሞች ለመሆን ጊዜ አልወሰደባቸውም:: ከሁሉም በላይ ጓደኝነታቸውን ይበልጥ ያጠበቀው ደግሞ በኢሕአፓ የወጣት ሊግ ከንፍ አባል መሆናቸው ነው:: የእያዩ እናት ድልነሳን እንደ ልጃቸው ያዩታል::

«እናንተ ልጆች አትነሱም ማለት ነው? እራታችሁን ብሉና ውጡ እያልኩ መሰሎኝ» አሉ ደገሙና:: ሁሌ እንደ ሰጉ ነው:: ወታደር ሲያዩ የልባቸው ምት ይጨምራል:: ለእሳቸው ነፍስ አይደለም ለልጆቹ:: እነድልነሳን የሰሟቸው አይመለሱም:: የወቅቱ የፖለቲካ ወሬ ጆሮዋቸውን ደፍኖታል::

«እንዴት ሰው ብትንቁ ነው እንዲህ እየለፈለፍኩ በልታችሁ ከምትኸዱበት የማትኸዱ እናንተ ልጆች!» አሉ የእያዩ እናት ለሦስተኛ ጊዜ ቆጣ ብለው:: ድንጉጥና ፈሪ ይምሰሉ እንጂ የአቶባርኮን የእናቶች የኡኡታ ኮሚቴ የሚመሩት እሳቸው ናቸው:: ከምሽቱ እራት ሰዓት ሲሆን ይጀምራል ኡኡታው:: እናቶች ቤት ለቤት እየተቀባበሉ የሚያሰሙት «ኡ-- ኡ ታ» ሰማይ የሚሰነጥቅ ይመለላል:: ድብልቅልቅ ያለው የእናቶች ጩኸት ጎንደር ከተማን ጫፍ እስከ ጫፍ ሲንጣት ያመሻል::

የጎንደር ወጣት የኢሕአፓ አባል ይሁንም አይሁንም ከወታደራዊው መንግሥት ይሸሻል---ይሸሽጋል:: እፈሳው ሌሊት ሌሊት ስለሚብሰ አብዛኛው ወጣት ከቤቱ አያድርም። በቀሃ-በአንገረብ-- በተገኘው ጫካ ሁሉ ሌሊቱን መሽጎ ያድራል:: የነእያዩ ማደርያ የቀሃና የአንገረብ ወይ ደግሞ ከጎንደር ጫካዎች እንደኛው መሆኑ ነው::

ጎንደር የአብዮት እሳት እየለበለባት ነው:: ሌላው ቀርቶ እንደ ወትሮው ሁሉ አድባራቱና ገዳማቱ እንኳ ማሕሌተ ዝማሬያቸውን እየተቀባበሉ ከእድማስ እድማስ አያለሙም:: የነግህና የተሰያት ተረኛ ቀዳሾችን ለመቀስቀስ ደውሎች አይደወሉም:: ጸጥ--- ረጭ ብለው ትንፋሻቸውን ወደ ውስጥ ውጠዋል:: በእዘቦት ቀን ሳይቀር ደጇ ሰላም ሳይሳለም የማይውለው የጎንደር ምዕመን በሰንበት ቀንም ቀርቷል:: በምትኩ በየቀበሌው እዳራሽ አብዮታዊ ንቃት ይሰጠዋል:: ካድሬ ሁሉ ለሚ ሳያገኝ እንደ ቁራ ሲጮህ ይውላል:: ጭንቀት--- ውጥረት ከተማዋን ሊያፈነዷት ደርሰዋል:: እናት ማጀቷ ውስጥ ተደብቃ ገመድ በልብሷ ውስጥ ታጥቃ ታለቅሳለች:: ሰላም ቀን እንዲያመጣ እጆቿን ወደ ሰማይ ዘርግታ ፈጣሪዋን ትማጸናለች:: አባት የሚያደርገው ግራ ገብቶት ይቅበዘበዛል:: በየመሸታ ቤቱ ባፈድሰት ብርሌ ጠጅን እየተጎነጩ- እዝማሪ አቁሞ ግጥም እየተቀባበሉ የሚዝናኑባት ጎንደር በሀዘን አንገቷን ደፍታ ከልጆቿ ጋር ጭንቅ ውጧት ታቃስታለች::

ትሩፋትና ራሄል የጎንደር ከተማ ሁኔታ ከባታ ወህኒ ቤት የተሻለ ሆኖ አላገኙትም:: ጎንደር ከተማን ቶሎ መልቀቅ ፈለጉ:: የእብዮት እሳት የሚነድባት ጎንደር እንደ ዱሮው «ቆዩብኝ--- ቆዩብኝ እዩኝ--- እዩኝ» እትልም::

ትሩፋት ጎንደር ከተማን ከመልቀቋ በፊት እበራሽን ማግኘት ፈልጋለች:: ታስራ ሳትጠይቃት በመቅረቷ ቅር ቢላትም «ባትለማ ወይም የጊዜው ባለስልጣን ስለሆነች በጓዶቿ ዐይን ውስጥ እንዳትገባ ፈርታ ይሆናል» ብላ ገምታለች::

******

«ይቺን አጭር ሕይወት ይበልጥ ለማሳጠር ምን እስቸኮለሽ ትሩፋት? ፈጣሪ ራሱ የአፍሪካውያን እድሜ ረጅም እንዲሆን የፈለገ አይመሰልም:: እሰቲ አስተውይው በሽታ የሚጨርሰው---- በድርቅ ሳቢያ በርሀብ አለንጋ እየተገረፈ የሚረግፈው---ከዚህም የባሰ

በእርስ በእርስ በጦርነት የሚጨራረሰውን ሕዝብ ሲታይ የእግዜር ቁጣ ነው የሚመስለው» አለች አበራሽ። መታሰሯንና የታሰረችበትን ጉዳይ ትሩፋት ስትነግራት። መታሰሯን እንኳ አላወቀችም ነበር።

«ግን ምን ማድረግ ነበረብኝ አበራሽ?

«እርፈሽ መቀመጥ ነዋ የነበረብሽ! የጊዜውን ሁኔታ እያየሽ ተንደርድረሽ እሳት ውስጥ መማገድ ነበረብሽ?»

«አሁንም አላመንሽኝም ማለት ነው? እስከ አሁቴ የታሰርኩት ባልሰራሁት ስራ ነው አበራሽ። እውነቱን ነው የነገርኩሽ።»

«አሱ እንኳን የድርጅታችሁ ዲሲፕሊን ጠንካራ እንደ ሆነ አውቃለሁ። ምንም ነገር እንድትነግሪኝ አልጠብቅም»።

«በፈጠረሽ አበራሽ! ፖለቲካ ውስጥ ብኖርበት ኖሮ ትዳር የምመሰርት ይመስልሻል? ትዳር እኮ ድርብ ሀላፊነት ይጠይቃል። እኔ ደግሞ ታውቂያለሽ ዙሪያዬንን በብዙ ሀላፊነት የተከበብኩ ሰው ነኝ። የፖለቲካ ድርጅት አባል ለመሆን የተመቻቸ ሁኔታ የለኝም» አለች ትሩፋት።

«የእጅ አሻራ የሚመረመረው እኮ ሳይንስ በወለደው ዘመናዊ መሳሪያ ነው። ሆኖም አንቺንም ላለማመን ይቸግረኛል። አብረን በኖርንባቸው የጓደኝነት ዓመታት ውሸትና ማስመሰል የማይሆንልሽ ሰው መሆንሽን አውቃለሁ። ዛሬ ግን ፖለቲካ የሚሉት ነገር መጥቶ እናትና ልጅ እንኳን ከማይተማመኑበት ወቅት ላይ ደርሰናል። እኔንም አትፍረጅብኝ።»

«እንግዲያው ልንገርሽ እይደል አበራሽ! መሳሪያዉ ራሱ መመርመር አለበት። እውነት ነው የምልሽ በዚህ ዓይነት ብዙ ንጹሃን ዜጎች አልቀዋል ማለት ነው። አመንሽኝም--- አላመንሽኝም ለሁለቱ ሰዎች ተጻፈ የተባለውን ማስጠንቀቂያ በፍጹም እኔ አልጻፍኩትም።»

«ለማመንም--- ላለማመንም አስቸጋሪ ነው የሆነብኝ» አለች አበራሽ ግራ ተጋብታ።

«የማዝነው አንቺ ስላላመንሽኝ ብቻ አይደለም አበራሽ። በዚህ መሳርያ የተሳሳተ የምርመራ ውጤት ምክንያት ስንት ንፁሃን ዜጎች ያለ ጥፋታቸው ሕይወታቸው ማለፉን ሳስብ ነው። እኔ መቼም አስከ አሁቴ በእግዚአብሔር ቸርነት ተርፌያሁ» አለች ትሩፋት ሀዘን ውስጥ ውስጧን እየሰበለባት።

«ትሩፋት ጊዜው ስር ነቀል ለውጥ የሚካሄድበት የአብዮት ወቅት ነው። ጥድፊያ የበዛበት። ለማስተዋልና ለማጣራት ፋታ የማይገኝበት። የደፈረሰው እስኪጠራ ድረስ እንዲህ አይነት ስህተት ቢያጋጥም የሚያስደንቅ አይሆንም። አገራችን የምታካሂደው ፈጣን የለውጥ እንቅስቃሴ ነው። ይህንን አትርሺ።

«መቼም አብዮቱ የሚካሄደው ለሕዝብ እድገትና ለዕልና ነው። ለድንጋይ፣ ለአፈር፣ ለውሃ፣ ለሜዳውና ለተራራው አይመስለኝም። ሕዝብ እንዲህ እንደ ቅጠል እየረገፈ አብዮቱ የሚካሄደው ለማን ጥቅም ሲባል ነው ታድያ?»

«ሁለት ዓይነት ሕዝብ ይኖራል። የአብዮት መንገድ የሚከተልና በአንጻሩ ደግሞ የፀረ-አብዮት መንገድ የሚከተል። የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ለማስከበር ሲባል ፀረ ሕዝብ ሁሉ በአብዮት እሳት መበላቱ አይቀረም። በሌሎች አገሮችም የሆነው እንዲሁ ነው። አንቺም ብትሆኚ በለስ ቀንቶሽ ዛሬ ወጥተሻል። ከእንግዲህ በሰላም መኖር ከፈለግሽ የፀረ አብዮት ካምፕን ምርጫሽ አታደርጊም። ትሩፌ ይህን የምነግርሽ ከድሮው የጓደኝነታችን ስሜት ውስጥ ሳልወጣ ነው» ብላ አስተውላ ተመለከተቻት።

«አውቃለሁ አበራሽ ጓደኝነታችን ለዘለዓለም ይኑር!» አለች ትርፋት መፈከር እንደምታሰማ ሁሉ ግራ እጇን ወደላይ አንስታ። «'በማስተዋል መኖር አለብሽ' ለምትይኝ ግን እንዴት ነው ማስተዋል ያለብኝ? ለሁለቱ ሰዎች ማስጠንቀቂያ በተሰጠ ማግስት የእጅ አሻራና ጽሑፍ እንድንሰጥ ተደረገ። ነገሩ ተረስቶ ብዙ ወሮች ካለፉ በኋላ ውጤቱ ሲመጣ ወንጀለኛዋ እኔ ሆኜ ተገኘሁ። ራሄል እቤት ውስጥ አብራኝ በመገኘቷ ብቻ ነው ወህኒ የወረደችው። ምንም ጥፋት ሳይገኝባት ነው ይህን ሁሉ ስቃይ የተቀበለችው።»

«አሁን ይህ ሁሉ ማለቃቀስ ለምን ተፈታን ነው?»

«ለምን ተፈታን ሳይሆን መታሰርም አልነበረብንም ነው። በተለይ ራሔል ያለምክንያት ነው ያ ሁሉ ግርፋት የደረሰባት። እስቲ ይታይሽ አበራሽ ከእንዲህ ዓይነቱ ዱብዳ ነገር እንዴት ነው መጠንቀቅ የሚቻለው?» አለች ትሩፋት በዚች አገር እንዴት መኖር እንደሚቻል እያሳሰባት።

«እሱ እንኳን የጠረጠሩት ነገርም ይኖራል።»

«ምን ሊጠረጥሩ ይችላሉ?»

«ራሄልና ድልነሳ ትምህርታቸውን አቋርጠው ከአንቺ ጋር መሆናቸውን አትርሺ። ትምህርት ቤቶች ሁሉ እንዲዘጉ ያደረገችው ደግሞ 'ትምህርት ከድል በኋላ' በሚለው መሪ መፈክሯ ኢሕአፓ ናት። ለአሁኑ እንኳን ተፈታችሁ አንጂ ወንጀለኛ ለማድረግ ከተፈለገ አንኳን ይኸ ራሱ በቂ ምክንያት ሊሆን ይችላል።»

«እጢቃላይ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ተዘጉ፡፡ አንድም ተማሪ በሌለበት ብቻቸውን አይማሩ ነገር ምን ይሁኑ ይባላል አበራሽ?»

«ሁሉም ቤተሰብ ቢጠየቅ የሚሰጠው መልስ ይህንኑ ነው፡፡ ሀላፊነት የሚወስድ አንድም ወላጅ አታገኝም፡፡ ሁሉም ወላጅ የራሱን ልጅ ንጹህ ያደርጋል፡፡ አንችም ይህንኑ ነው የምትነግሪኝ፡፡ እኔን ሊገባኝ ይችል ይሆናል፡፡ አብዮቱ ግን አይገባውም» አለችና ለጥቂት ጊዜ ዝም አለች፡፡ «አብዮቱ የሚገባው ነገር ቢኖር ያለምንም ችግር ሶሻሊዝም በኢትዮጵያ ምድር ማበቡና ግብ መምታቱ ብቻ ነው፡፡ ያለፈውን እንተወውና መጭውን እናስብ በቅርቡ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ሊከፈቱ ነው፡፡

«እውነትሽን ነው አበራሽ ትምህርት ቤቶች ሊከፈቱ ነው?» አለች ትሩፋት የመገረምና የመደንገጥ ስሜት እየታየባት፡፡

«አዎ! ምነው? የትምህርት ቤቶች መከፈት የገረመሽ ተመስያለሽስ፡፡»

«አንዴ አበራሽ! የሚማሩት እኮ እህቶቼና ወንድሞቼ ናቸው፡፡ አሁንም አላመኘሽኝም አይደል?»

«እንጃ! ምን አውቃለሁ ትሩፋ? ሳይሽ የትምህርት ቤቶች መከፈት ያስደሰተሽ አትመስይም፡፡»

«አበራሽ በቆየው ጓደኝነታችን ስም ልለምንሽ ካልሆነ ጥርጣሬ ውስጥ አትግቢ፡፡»

«እሱን እየቆየን የምናየው ይሆናል፡፡ ይልቅስ ከፍተኛ ምሥጢር ነው የምነግርሽ፡፡ በትምህርት ገበታ ላይ ያልተገኘ ተማሪ ሁሉ እንደ ፀረ- አብዮተኛ ተቆጥሮ በተገኘበት ቦታ እንዲረሸን ተወስኗል፡፡ ለየአውራጃዎችና ወረዳዎች ለገበሬ ቀበሌ ማህበራት ሁሉ ሳይቀር መመሪያ ተላልፏል፡፡ ትምህርት ቤት እንደ ተከፈተ ድሌና ራሔል ወዲያውኑ እንዲጀምሩ አድርጊ፡፡»

«ራሔል ቁስሏ እስኪድንላት እንኳ አብራኝ ብትቆይ ጥሩ ነበር፡፡ የኔን የቶርቸር ሒሳብ ሁሉ ያወራረዱት በእሷ ላይ ነው፡፡»

«የነገርኩሽ ከፍተኛ ምሥጢር ዋዛ መስሎሽ እንዳትሞኚ፡፡ በሚደርሰው ነገር ሁሉ ኋላ እንዳታዝኚ፡፡ ኢሕአፓ የሚሏት ፀረ-ሕዝብ ድርጅት በምትነፋው የውሸት ፕሮፓጋንዳ ተታለሽ ወንድምና እህቶችሽን እንዳታጭ» አለች አበራሽ ጠንከር አድርጋ፡፡

«ምነው አበራሽ በኔ ላይ ከፉ እንዳይደርስ አይደል እንዴ ይህ ሁሉ ጥረትሽ? ከልቤ አመሰግንሻለሁ፡፡»

«ምስጋናውን እዚያው ቀቅለሽ ብይው፡፡ ድሌና ራሔል ለእኔም እህትና ወንድም ናቸው፡፡ በዚያ አድካሚ የመምህርነት ሥራ ለአንዳንድ ጉዳይ ከደልጊ ጎንደር ከተማ ስመጣ የማርፈው ከነሱ ጋር ነበር፡፡ አቶባርኮ በተከራየሽላቸው በዚያች ትንሽ ከፍል ውስጥ፡፡ ዘመድ ጠፍቶ አይደለም፡፡ የራሔልና የድሌ ፍቅር ልዩ ነበር፡፡ ላንቺ ከሚያደርጉት በላይ እንዴት ይንከባከቡኝ እንደ ነበር አልረሳውም» አለች አበራሽ ከልቧ፡፡

«አውቃለሁ አበራሽ፡፡ ለእኔ መንገር አይጠበቅብሽም፡፡ ራሔል ግን ትንሽ የመንፈስና የአካል እረፍት ያስፈልጋት ነበር»

«'ያልገደለ በሽታ ሁልጊዜ ሲወቀስ ይኖራል' አሉ፡፡ በዚህ ቀውጢ ሰዓት ነብሳችሁ በሰላም መውጣቱ ራሱ ተመስገን ነው፡፡ በግርፋቱም ልታማርሪ ታስቢያለሽ ትሩፋት? ሆሆይ! ምን እንዲያደርጉላችሁ ጠብቀሽ ነበር? ጊዜው የአብዮት ወቅት ነው ውዷ ጓደኛዬ፡፡ ስንት ጊዜ ላስታውስሽ? ቅቤ ቀብተው እንደ ለቀቋችሁ ቁጠሪው፡፡»

«እሱስ እውነትሽን ነው፡፡ በስም ስህተት እንኳ ስንቱ አልቋል፡፡»

«ይሄ ነጭ ወሬ ነው!» ቱግ አለች አበራሽ፡፡ «ዘመኑ የጥድፊያ ቢሆንም ያን ያህል ስህተት ይሰራል ብዬ አላምንም፡፡ የጎንደር ሕዝብ ጤነኛ አይደለም፡፡ አብዛኛው ወጣት የቅጥረኛው የኢሕአፓ አባል ነው፡፡ አዛውንቱ እንኳን ገና ልቡ አልሞተም፡፡ መንፋሱ እንደ ሸፈተ ነው፡፡ አሁንም ዘውድ ናፋቂ ሕዝብ ነው፡፡ ውስጥ ውስጡን ኢድዩን እንደ ሚደግፍም ይታወቃል፡፡» ትሩፋት እስኪገርማት ድረስ ደነፋች አበራሽ፡፡

«ደግነቱ ለኃይለኛውም ኃይለኛ አዘበታል፡፡ ደህና አድርጎ አናት አናቱን እየተቀጠቀጠ የሚገዛው ገዢ ጥሎበታል፡፡ ያ ባይሆን ኖሮ የጎንደር ሕዝብ የሚቻል አይደለም» አለች አበራሽ፡፡ የምር ተናዳ ነበር፡፡

«እሱስ እውነትሽ ነው፡፡ ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው' ይባል የለ» አለች ትሩፋት ነገር እንደ አመለጣት ስታውቅ ደንገጥ ብላ፡፡ አበራሽ እንዲህ እሳት የላሰች ካድሬ ትሆናለች ብላ አልጠበቀችም ነበር፡፡

«ደርግን አገለብጣለሁ ማለት የራስ ዳሸንን ተራራ ከቦታዉ አነሳዋለሁ እንደ ማለት ይቆጠራል፡፡ ጠሩ በሙሉ ደግፎታል፡፡ የመሬት ላራሹን ጥያቄ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በማያዳግም መልኩ መልሷል፡፡ በዚህም ምክንያት ገበሬው ሙሉ ለሙሉ ድጋፉን ሰጥቶታል፡፡ የከተማው ቤት አጥ ድሀ የአከራይና የተከራይ ግንኙነት ተቋርጦለታል፡፡ ነጋ ጠባ በቤት ኪራይ ስም መጨቅጨቁ ቀርቶለት እፎይ ብሏል፡፡ እስቲ አስቢው ምን ቀረኝ ብሎ ሌላ መንግስት ይፈልጋል? ከአንግዲህ ፈውዳል ሁሉ እርሙን ያውጣ! አናርኪስቷ ኢሕአፓ ደግሞ 'ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ምናምን' እያለች ኩታራ ሰብስባ እንደ ተልባ ብትንጫጫ ትርፉ አንድ ሙቀጫ ነው፡፡ ይልቅስ የጓደኝነቴን ልምከርሽ፡፡ በእጉል ቅስቀሳ

ደርግ ይወድቃል ብለሽ እንዳትታለይ:: መስመርሽን በጊዜ ብታስተካክይ ይሻልሻል:: ደርግ የተማረ የሰው ኃይል ይፈልጋል:: አንቺም ከዚያ ከገጠር አንድትወጭ ነው የምመክርሽ» አለች አበራሽ ቀዝቀዝ ለማለት እየጣረችና የትሩፋትን ስሜት ለማጤን እየሞከረች::

«እስቲ ለማንኛውም ልረጋጋ:: ከተመሰቃቀለው ሐሳቤ ገና አላገገምኩም:: መውለጃዬም የደረሰ ይመስለኛል» አለች:: ለምትናገረው ነገር ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባት ገብቷታል:: ምንም እንኳ አበራሽ ጥብቅ ጓደኛዋ ብትሆንም ጊዜው የአብዮት ነው:: ስንቱ ጓደኛ በመስመር ልዩነት ተለያይቷል:: መሳሪያ ተማዞ ነፍስ ጠፍቷል:: ትሩፋት አበራሽን ብትፈራት አይፈረድባትም::

«የማለተማር ሥራ ትርፉ ድካም ነው ትሩፋት:: ገጠር ለገጠር መንከራተት:: ከማንም ኩታራ ጋር መዳረቅ:: ምን በወጣሽ!? አብዮቱን ተቀላቀይና ጎንደር ከተማ ግቢ:: አንቺማ ስነ-ጽሑፍም ትሞካከሪያለሽ አይደል:: አብዮቱን የሚያወድሱ አንዳንድ መጣጥፎች በጋዜጣና በመጽሔቶች ላይ እንዲወጣ ብታደርጊ ደርግን አለደለተሽ ወድያውም ችሎታሽን ታሻሽያለሽ::»

«ኧረ በእናትሽ አበራሽ! እንዲህ ከፍ ከፍ ታደርጊኝ:: የትኛው የስነ- ጽሑፍ ችሎታዬ ነው ደግሞ ከሰው ፊት የሚያቀርበኝ? መሳቂያ መሳለቂያ ልታደርጊኝ አሰበሽ ካልሆነ በስተቀር» አለች የአበራሽን የተቆጣ ስሜት ለማለሳለስ ጭምር::

«ዋናው ቁም ነገር ቤት መትቶ አብዮቱን ማሞጋገስ ብቻ ነው:: ጊዜ ወስዶ በጥልቀት እንብቦ ይዘቱን ማን ሲመረምር ይገኝ መስለሽ? ደርግ በተለይ የተማሩ ሴቶችን በመብራት እየፈለገ ነው:: አባላቱን ሲንከባከብ ደግሞ ያውቅበታል:: ይልቅስ አብዮቱን ተቀላቀይና ዘ--ና ብለሽ ኑሪ:: መኖር ዛሬን ነው::»

ትሩፋት አበራሽ የወታደራዊው መንግሥት ሙሉ ደጋፊ መሆኗን አውቃለች:: እሷም አልደበቀቻትም:: ግን የየትኛው ድርጅት አባል እንደሆነች ለይታ ማወቅ አልቻለችም:: የመኢሶን፤ የሰደድ፤ የማልሬድ፤ የወዝሊግ፤ የኢማሌድህ፤...? እንደው ለትገምት ግን የመኢሶን አባል ሳትሆን አትቀርም ብላ ታስባለች:: ለጥርጣሬዋ መነሾ የሆናት ደግሞ ሰለ ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽፈት ቤት ተግባርና እንቅስቃሴ አሞግሳ አይበቃትም:: የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽህፈት ቤት በአብዛኛው በመኢሶን አባላት የተያዘ ነው::

«ዛሬ ማታ ፎገራ ሆቴል የከፍለ ሀገሩና የየአውራጃው ትላልቅ ባለስልጣናት ከስብሰባ መልስ የመልካም ግንኙነት የራት ግብዣ አላቸው:: እኔም እገኛለሁ:: የፈለግሁትን አንድ ሰው መጋበዝ እንደምችል ተነግሮኛል:: አብረን እንሄዳለን::»

«ኧ---ረ! እየቀለድሽ መሆን አለበት አበራሽ:: እንዲህ ሆዴን የአቦ ተራራን አሳከዬማ ከሰው ፊት ቅረቢ ባላልሽኝ:: ለዚያውም ባለለልጣን በሞላበት::»

«የሴት አርግዝና የታወቀ የተፈጥሮ ሕግ ነው:: እነሱም ሳይንሱ ይገባቸዋል አባከሽ! አዲስ ነገር የለም:: ባንቺ አልተጀመረ ባንቺ አያቆም፤ ያለ– የነበረ-- የሚኖር ነው:: ይልቅስ ተዘጋጂ::»

«አበራሽ!---በፈጠረሽ ይቅርብኝ!»

«ሞኝ አትሁኝ ትሩፋት:: በዚህ ጥድፊያ በበዛበት የአብዮት ወቅት ትላልቅ ባለስልጣናትን ማወቅ የኑሮ ዋሰትና ኢንሹራንስ እንደ መግባት ይቆጠራል:: ቀደም ብለሽ ከባለስልጣናቱ አንዱን ተዋውቀሽ ቢሆን ኖሮ እንኳን አልሰራሁትም በምትይው ወንጀል ይቀርና ለርተሽውም ቢሆን እንኳ እንዲህ ሆነሽ ባልታሰርሽም ነበር::» አለች አበራሽ ወደ ሆዷ እየጠቆመች::

« ው--- ይ ኧረ ያሳፍራል! አባከሽ ለሌላ ጊዜ ይተላለፍልኝ::»

«ጊዜ ሲኖር አይደል:: ነገ እንደ ገና ታስረሽ ብትመጭስ?»

«ምነው አበራሽ!? በጎ በጎውን አትመኝልኝም ይልቅ::»

«አልሰማ አልሽኝ እንጂ እኔማ የሰላሙን መንገድ ነበር እየነገርኩሽ ያለሁ:: ልጅሽን በሰላም ወልደሽ በሰላም ለመኖር ከፈለግሽ የአብዮቱን ካምፕ መቀላቀል-- ያለዚያም የትላልቅ ባለስልጣናት ጥግ መያዝ ነው ዘዴው እያልኩሽ እኮ ነው ትሩፌ ቢገባሽ:: ያለዝያ ትንንሽዬ የወረዳና የቀበሌ ባለስልጣናት ሁሉ መጫወቻ ያደርጉሻል:: ሁሉም እንዳሻው እየተነሳ ይዘፍንብሻል:: ሊያስር-- ሊፋታሽ ካሰፈለገም ሊረሽንሽ ሁሉ ይችላል::» አለችና ትንሽ ዝም ብላ ቆይታ

«ትሩፌ ጊዜው የመቅደም ጉዳይ ነው:: እከሌ የተባለውን ባለስልጣን ታውቀዋለች ከተባለ ግን ካድሬ ሁሉ እጁንና እፉን ይሰበስባል:: እንደውም በግልባጩ የምትፈሪው አንቺ ትሆኛለሽ:: በዚች ዓለም ላይ ደልቷቸው የሚኖሩት ብልጣ ብልጦች ናቸው:: እንደ አንቺ እውነቷን ይዘው ስራቸውን ብቻ እየሰሩ ለመኖር ደፋ ቀና የሚሉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ሲጎዱ ነው የሚታየው:: ድርቅ ያለ እውነት ምን አልባት በሰማይ ቤት ያፀድቅ ይሆናል:: ያን የሰማይ ቤት ደግሞ ከሰሙ በስተቀር አየሁት የሚል አንድም ሰው በዚች ምድር ላይ አልተገኘም:: መኖር በእጅ የያዙትን ነው:: ዛሬን--ዛሬን!» አለች አበራሽ እንገቷን አሰግጋ ወደ ፊቷ ቀረብ እያለች::

ትሩፋት ከዚህ በላይ መከራከር በደርግ መንግስት ላይ ያላትን አቋም ዐይን ባፈጠጠ መልኩ ማሳወቅ እንደደማይኖርባት ቀድሞውኑ መምጣት እንዳልነበረባት እያሰበች ቅፍፍ እያላት ለመሄድ ተስማማችላት::

ፎገራ ሆቴልን ደጋግማ አይታዋለች ትሩፋት:: ሁመራ ትሰራ በነበረበት ጊዜ ለእረፍት ስትመጣ አበራሽና እሷ ቡና የሚጠጡት እዚሁ ፎግራ ሆቴል ነበር:: የዛሬን እያድርገውና ጸጥታውን ትወደው ነበር:: በመሳሪያ ብቻ የተቀነበበረ ለሰለስ ብሎ የሚንቆረቆረውን ሙዚቃ ማዳመጥ ከሁሉም በላይ ያስደስታት ነበር:: አሁን ግን እንደምናምን ቀፈፋት::

ከሆቴል ሲደርሱ አዳራሹ በባለስልጣናቱ ግጥም ብሷል:: ትሩፋት አበራሽን ተከትላ እየተደነባበረች ወደ ውስጥ ዘለቁ:: የሰው ሁሉ ዐይን ከገፋ ሆዷ ላይ ያረፈ መሰላት:: ሁሉም በቡድን በቡድን ቆሞ ይዝናናል:: እግሯ ተጠላልፎ እንዳትወድቅ ፈራች:: ራሷን ያዞራት ልቧን ያጥወሰወላት መሰላት:: ቶሎ ብላ ጥግ ላይ ያለ አንድ ወንበር ባትይዝ ኖሮ መውደቋ አይቀሬ ነበር::

አበራሽ የማታውቀው ባለስልጣን የለም:: የከፍለ ሀገሩ የርዕዮተ-ዓለም ተጠሪ—የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ--የወጣቶች---የሴቶች--ተጠሪ-- የሊቦ--- የወገራ---የደብረታቦር----የጋይንት--የጭልጋ አውራጃ አስተዳዳሪ ሁሉም ጋር ሰላምታ ትሰዋወጣለች::ትሩፋትንም "እህቴ ናት" እያለች ታስተዋውቃታለች:: በጠያቂ ዓይን እያስተዋሏት ይሄዳሉ:: ባደራሹ ውስጥ ብዙ ሰው ቢኖርም ባይተዋርነት ተሰማ ትሩፋት::

የፎገራ ሆቴል አስተናጋጆች ምግብና መጠጥ ያዞራሉ:: ቅልጥፍናቸው ለጉድ ነው:: ከወዲያ ወዲህ ሽርጉድ--ሽርብትን ይላሉ:: መጠጥ በያይነቱ እንደ ውሃ ይቀዳል:: እንደ ጉድ ይበላል:: የተለመደው የፎገራ ሆቴል በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ ቀሰሰስ እያለ ይወርዳል:: የፍየል ወጠጤ ቀረርቶ የሚያስፈልገው ለሕዝቡ ነው:: ደረቅ ሽሮ የበላ ሆዱ ደግሞ በቀረርቶና ፉከራ መደንገጥና መደንዘዝ ይኖርበታል:: ሕዝቡ ይህን ሁሉ ግፍ ችሎ አንገቱን ደፍቶ ዝም ብሎ ይኖራል::

«ግን እስከ መቼ?» አለች ትሩፋት በሆዷ:: «የደርግ ባለስልጣን ቀን ቀን ካኪ---ማታ ማታ ውስኪ» ብሎ ሕዝቡ ትዝብቱን ነግሯቸዋል:: ማንነታቸውና ግብራቸው አብሮ እንደማይሄድ በውብ ስነቃል ገልጾታል:::: ትሩፋት የሕዝቡን ትዝብት ከፎገራ ሆቴል ግብዣ ጋር አገናዝባ ብቻዋን ፈገግ አለች:: አበራሽ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ነው ካለችው ባለስልጣን ጋር አፍ ለአፍ ገጥማ ታወራለች:: መለኪያውንም ታወራርደዋለች:: ስታውቃት የአልኮል መጠጥ አትጠጣም ነበር:: ከመቼው እንዲህ እንደ ተካነችው ገረማት:: እንዳትስከር ሲጋቻላት::

«ለምን ሌላ መጠጥ አትቀምሽም?» አላት አንድ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ነው ብላ ያስተዋወቀቻት ሰው:: አጠገቧ ካለው ባዶ ወንበር ላይ እየተቀመጠ::

«ብዙ ልምድ የለኝም:: ራሴንም እንዳያመኝ ብዬ ነው» አለች ሆድ ሆዷን እያየች:: እሱም ዐይኗን ተከተለ:: ውስጧ ሽምቅቅ ሲል ታወቃት:: ሁሉም ነገር አልጣማትም---ሁሉም ነገር ከሷ ስብዕና ጋር አብሮ አይሄድም:: የግብዣው ማለቂያ ሰዓት ናፈቃት::

«ሳይበዛ ምንም አይልም:: ሳይንሱም ያዘዋል» አላት ዐይኑን ከገፋ ሆዷ ላይ ሳይነቅል::

«ከአሁን ቀደም አልኮል ነክ መጠጥ ቀምሼ አላውቅም:: ልምዱ የለኝም» አለች እንደ አፋራም ልጃገረድ አንገቷን ደፍታ::

«አንድ ቀን ይቀመሰና ቀስ በቀስ ይለመዳል» አላት ሊያግባባት እየሞከረ::

«እንግዲህ ሌላ ጊዜ እቀምስዋለሁ:: ለአሁኑ እንኳን አምቦ ውሃው ይሻለኛል» አለች ትሩፋት ወደ አበራሽ እየተመለከተች:: አበራሽ አብራው ካለችው ሰው ጋር ትምሰል እንጂ ጆሮዋ እነትሩፋት ጋር ነበር::

«ሥራሽ ምንድን ነው? እዚህ ጎንደር ከተማ ወስጥ ነው የምትኖሪው?» ጠየቃት የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው::

«እም!-- የፈራሁት አልቀረም:: እዚሁ ሰላይ መጣብኝ» አለች ትሩፋት በሆዷ:: ቅድሙንም ከአበራሽ ጋር እዚህ ቦታ መምጣቱን የጠላችው እንድም ለዚሁ ነበር:: ታስራ መፈታቷን እንኳን የደርግ ባለስልጣን የሆነ ሰው ይቅርና ማንም እንዲያውቅባት አትፈልግም:: ወሬ ከበዛ ደግሞ ሌላ ችግር ሊያስከትል ይችላል:: ተጠንቅቃ መልሷን ስታንሰላስል

«ጓድ ወንድሙን በደንብ አወቂው እንዴት ያለ ጠንካራ ጓዳችን መሰለሽ:: አብዮቱ ካፈራቸው ጠንካራ ጓዶቻችን አንዱ እሱ ነው» የአበራሽ ንግግር ነበር:: ባለስልጣኑ በአበራሽ ውደሳ ትከሻ የጨመረ መሰለ:: ወሬው በመቀየሩ ደግሞ ትሩፋት ከጥያቄው ተገላገለች:: ሁለቱ እርስ በእርስ ወደ መሞጋገሱ ገቡ::

ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ቆምን የሚሉት ደርጎች በጭቁኑ ሕዝብ ገንዘብ ይምነሸነሻሉ:: ከአበሻ እስከ ፈረንጅ የምግብ ዓይነት እያማረጡ ይመገባሉ:: በውስኪ ይራጫሉ:: ጊዜው ገፍቶ አኩለ ሌሊት ሆነ:: የሰዓት እላፊ ገደቡ እነሱን አይነካም::ከግብዣው በኋላ ሁሉም በተመደበላቸው የመንግሥት መኪና ወደ ሚፈልጉበት ቦታ ተሸኙ::

«እንዲህ እርጎም ለጭቁን ሕዝብ መቆም የለ!» አለች ትሩፋት ለራሷ:: ከአበራሽ ጋር ፎገራ ሆቴልን ለቀው ሊወጡ::

******

ይነበብ የነትሩፋት ከእስር መለቀቅ ከምንም በላይ አስደስቶታል:: የትሩፋት የመውለጃ ቦታ አለመመቻቸት ደግሞ ሌላ ራስ ምታት ሆኖ ከፊቱ ተጋርጧል:: የመጀመርያ ልጃችውን የት ሆና ትውለድ? በእንዲህ ያለ ጊዜ ሁለቱም ያለመጠለያ ቀርተዋል:: ትሩፋት ድንገት ታስራ ከወጣችበት እንበሳሜ አትሄድም:: ከቤቷ ተመልሳ መግባት አትችልም:: የወታደራዊው መንግሥት ደርግ የኢሕአፓን መረብ ከሚበጣጥስበት አንዱ ስልቱ ታስረው የተፈቱ የመንግስት ሠራተኞችን ወደ ቀድሞ የሥራ ቦታቸው አይመልሳቸውም::

ትሩፋት ከእንግዲህ አዲስ የሥራ ቦታ ይጠብቃታል:: ምድቧን አስከታውቅ ደግሞ ሌላ ቦታ ሆና መጠበቅ ይኖርባታል:: ይነበብ ራሱ እንደአባወራነቱ የባለቤቱን የመውለጃ መሰናዶ ለማድረግ የሚያመች ሁኔታ ላይ አልነበረም:: ነገሩ ሁሉ ለእሱም በጣም አሳሳቢና አስጊ እየሆነበት ነው:: የሚወዳት ባለቤቱ ታስራ ጎንደር ባታ ወህኒ ቤት ተመላልሶ እንደ ልቡ የመጠየቅ እድል እንኳን አላገኘም:: በደርግ ዐይነ--መረብ ውስጥ ገብቷል:: ሌላ መጠለያ እስኪያገኝ ድረስ ለጊዜው ምድብ የስራ ቦታው ወረታ እንዲሆን ውስጥ ለውስጥ በጓዶች ተመቻችቶለት እንበሳሜን ለቋል:: እንደ ቆቅ ራሱን አንቅቶ በተጠንቀቅ ላይ ነው ያለው:: ለጊዜው የምታርፍበት ቦታ ሊያገኝላት አልቻለም:: በካር እንደ መሆኗ መጠን ሐኪም በምታገኝበት አካባቢ መሆን ይኖርባታል:: ሁኔታዎች ግን ለዚህ የተመቻቹ አልሆኑም:: ይነበብ ጭንቅ ያለ ነገር ሆኖበታል::

ትሩፋት ምርጫ ስታጣ ወደ እናቷ ሲፋጥራ ማርያም ወርዳለች:: ከተፈታች በኋላም ቢሆን የተረጋጋ ሁኔታ አላጋጠማትም:: የባታ ወህኒ ቤት ክፉ ትዝታ ገና ከአዕምሮዋ አልወጣም:: ጸጥታውና መረጋጋቱ ገጠር የሚሻል መስሏት ነበር ግን እዚያም ያው ነው:: ሕዝቡ የደርግ መንግሥትን እንደ ፈራ ውሎ እንደፈራ ያድራል:: ከተማ ያለው ሽብር በገጠሩም ብሷል:: የባላገር ወጣት ሁሉ አዳኙን እንደአየ እንስሳ የመንግሥት ታጣቂዎችን ባየ ቁጥር ይበረግጋል:: የወታደር ምልመላ ለየገበሬ ቀበሌ ማኅበሩ ኮታ ተጥሎ የገጠሩን ኗሪ ሁሉ እያመሰው ይገኛል:: ለትጥቅና ሰንቅ የሚሆን ገንዘብና እህል በየጊዜው አዋጡ መባሉ ገበሬውን ሁሉ አስመርሮ ካገር ሊያስወጣው ደርሷል:: የሞፈር ዘመት አድሎ የተሞላበት የመሬት ድልደላ አብዛኛውን ገበሬ በደርግ መንግሥት ላይ አዝኖ ቂም እንዲቋጥር አድርጎታል::

«በገጠር በከተማ በሕዝብ እንዲህ የተጠላ መንግሥት እስከ መቼ ይገዛን ይሆን?» አለች ትሩፋት:: የደርግ መንግሥት ቶሎ ወድቆ ሕዝባዊ መንግሥት የሚቋቋምበት ጊዜ ቅርብ እንዲሆን ተመኘች::

የትሩፋት እናት ቤት እንደ አብዛኛው የገጠር ቤት የሳር ክዳን አይደለችም:: ቆርቆሮ ናት:: ውስጧ በሦስት ክፍል የተከፋፈለ ነው:: መኝታ ቤት፣ እቃ ቤትና ሳሎን:: የቤቱን ጥግ--ጥግ ይዘው የተቀመጡ ከጠፍር የተሰሩ ሦስት መቀመጫዎች ይገኛሉ:: እያንዳንዳቸው

ሦስት ሦስት ሰው ማስቀመጥ ይችላሉ:: ቤቷ እንዳቅሟ ከተማ ከተማ ትሸታለች:: ትሩፋት ከአንደኛው መቀመጫ ላይ ጋደም ብላ ሐሳብ ይዞ እንደ ጉርና ይንጣታል::

በእሷ መታሰርና በይነበብ አለመረጋጋት ምክንያት ቤተሰቧ ተበትኗል:: ራሔልና ድልነሳ የትምህርት ቤቱን መከፈት እየተጠባበቁ ጎንደር ናችው:: ሌሎቹ እህቶቿ እዚያው እንበሳሜ ናቸው:: የአመቱን ትምህርት መጨረስ ስለ ነበረባቸው ይነበብ ብርሀኑ ለሚባል ጓደኛቸው እንደ እቃ አደራ ሰጥቷቸው ነው ወረታ ወደ ምድብ ሥራው የሄደው:: ትሩፋት የታናናሾቿ ሁኔታ ያሳስባታል:: የመጀመርያ ልጇን ለመውለድ በአካባቢው ሐኪም ቤት በማይገኝበት እዚህ ገጠር ውስጥ መሆኗ ሌላው የሚያስጨንቃት ጉዳይ ሆኗል:: እናቷ መተከዟን አይተው ሊያረሳሷት ፈለጉና

«አሁንስ ይርብሻል ልጄ:: እስቲ በዚች በትኩሷ ወጥ ትንሽ ቅመሽ» እያሉ ሆዷን የጎንዮሽ ስረቅ አድርገው ሲያይዋት ያዘቻቸው:: ይህ የስርቆት አስተያየታቸው ሀፍረት እንዲሰማት ያደርጋታል:: ቢሞቱ ዐይናቸውን ሞልተው ሆዷን አያዩም:: እንደዚህ ባደረጉ ቁጥር ደግሞ ገፍቶ ያፈጠጠ ሆዷን መደበቂያ ታጣለች::

«ለምን ግን አፍራ ታሳፍረኛለች?» አለች ትሩፋት ተሳቃ::

******

«ወር ያልሞላት የማርያም አራስ ወንዝ ተሻግራ አትኸድም:: ከርስትና ሳታስነሳ ጠበል ሳትረጭ ከቤት አትወጣም:: ምናምኑ ይተናኮላታል:: በኋላ ጤና ታጫለሽ ትሩፋቴ:: የወረታው መንገድ እንኳን ላልጠናች አራስ ለወንድም ይፈታተናል:: የምልሽን ሰሚኝ አባከሽ ልጄ» አሉ እናቷ የጎንደር ጉዞዋን እያከላከሉ:: ትሩፋት ምንም እንኳ አስጨናቂ ጊዜ ቢገጥማትም በመንደር እዋላጅ እዚሁ እናቷ ቤት ወንድ ልጅ ተገላግላለች::

«የወደቀበትን ሳላውቅ ብቀመጥ አሁንስ ጤና የማገኝ ይመስልሻል ታትዬ?»::

«የወደቀበትን ማፈላለግሽ ባልከፋም ነበር ግን የት ብለሽ ትፈልጊዋለሽ? የት እንደ ገባ ያልታወቀን ሰው መፈለግ ከንቱ መባዘን ነው የሚሆነው እኮ ልጄ! ኧረ እባከሽ ለዚህ አርጥብ ጨቅላ ብለሽ ተለመኚኝ» አሉ የትሩፋት እናት ጭንቅ ብሏቸው::

«ልጁ እንቹ እያለሽለት ምን ይሆናል ታትዬ? እኔም ጠንክሬያለሁ:: ግድ የለሽም አገኘሁትም አጣሁትም ጎንደር ደርሼ ቶሎ እመለሳለሁ::» ትሩፋት ዝም ብላ ለመሄድ አስበች እንጂ ይነበብን የት ብላ እንደ ምትፈልገው አታውቅም:: ታስሮ ይሆናል የሚል ግምት ነው የያዘችው:: እርምጃ ተወስዶበት ላለመሆኑም እርግጠኛ አይደለችም:: ታስራ ከተፈታች ወዲህ ድርጅታዊ ስራዋ ስለተቋረጠ ምንም ነገር መስማት አልቻለችም:: እንደ ዱሮው የግንኙነት መስመርን ቶሎ መቀጠል አስቸጋሪ እየሆነ በመምጣቱ ኢንፎርሜሽን

ማግኘት ከባድ ሆኗል፡፡ በተስፋ ስትጠባበቅ የነበረው በይነበብ በኩል ነበር፡፡ ይነበብ ራሱ አሁን የት እንደገባ አይታወቅም፡፡ ሁሉም ነገር ጉም እንደመጨበጥ ሆኖባታል፡፡ ተስፋዋ ሁሉ ባዶ!---ሕይወት ራሷ ባዶ!---አገሪቱ ራሷ ባዶ! ባ---ዶ ብቻ!

«ተስፋ መቁረጥ ግማሽ ሞት ነው፡፡ እንዲህማ በቀላሉ ተስፋ ልቆርጥ አይገባም አለች» ለራሷ፡፡ ይህን ትበል እንጂ ምንም ተስፋ --ምንም ጥንካሬ በውስጧ አልነበረም፡፡

ይነበብ በደራ ወረዳና በፎገራ ወረዳ የሚገኙ የኢሕአፓ መሰረታዊ ድርጅቶችን ያጠናክራል፡፡ አዳዲስ አባላትን ይመለምላል፡፡ በርዕዮተ--- ዓለም የበሰለ አቋም እንዲይዙ አባላቱን የማስተማር ሥራ ሁሉ የወደቀው በእሱ ላይ ነው፡፡ በገበሬው ውስጥ የፕሮፓጋንዳ ሥራ መሥራት ሳይቀር ይጠበቅበታል፡፡ ብዙ ገበሬዎች በኢሕአፓ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ አድርጓል፡፡ ከተቀጠረበት የመንግሥት ሥራ ይልቅ ወደ ድርጅታዊ ሥራው አያዘነበለ በመምጣቱ ምክንያት ዘግይቶም ቢሆን ጥርጣሬ ውስጥ መውደቁ አልቀረም፡፡ ወታደራዊው የደርግ መንግሥት እግር በእግር እየተከታተለው ነው፡፡ ጅግና ኪዳነምሕረት ገበሬ ማህበር ለነበረው ሰብስባ በጧት ነበር የደረሰው፡፡ ወደ ሰብሰባዉ ቦታ ለመሄድ ገና ጉዞ ከመጀመሩ

«ጋሼ ይነበብ --ጋሼ ይነበብ» አለ አንድ ወጣት ገበሬ ከኋላው ሲሮጥ ደርሶ፡፡ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል፡፡

«ከጎንደር ከመጣው አውቶብስ ውስጥ አንድ ሰው ይፈልግሀል፡፡ ከመንቀሳቀሱ በፊት በፍጥነት ሊያገኝህ ይፈልጋል» አለ፡፡ ጉማራ ድልድዩን አልፍ ብሎ ወደ ቆመው አውቶብስ እያመለከተው፡፡ «ቶሎ በል ጋሼ ይነበብ አውቶብሱ ሊንቀሳቀስ ነው፡፡» ይነበብ ተመለሰ፡፡ አውቶብሱ ሊንቀሳቀስ ሲል ደረሰበት፡፡ አንድ ሰው በመስኮት በኩል እጁን ልኮ አንድ ፖስታ አቀበለው፡፡ አድራሻ የለውም፡፡ እየተጠራጠረም ቢሆን ከፍቶ አነበበው፡፡ አጭርና ግልጽ መልዕክት ነበር፡፡

«ለወረዳው የወጣት ገበሬዎች የስፖርት ከበብ እንዲገዛልህ የጠየከውን የስፖርት ትጥቅና ጫማ በአፋጣኝ ጎንደር መጥተህ እንድትወስድ፡፡ ገበሬዎችን ለማሰልጠን የግድ ለአንተም ጫማ ያስፈልግሀል፡፡ የጫማ ቁጥርህ ስንት ነበር? 42 ነው አይደል? ትክክል ነው 42 ነው፡፡ እሱም ተዘጋጅቶልሃል» ይላል፡፡ ይህ መልዕክት ከየት እንደሚላከለት--ማን ሊልከለት እንደሚችል ያውቃል፡፡ ይነበብ መፍጠን ቶሎ ጎንደር ከተማ ገብቶ ማደር ይጠበቅበታል፡፡ ጊዜ አላጠፋም፡፡ ለገበሬዎቹ ወረታ ግብርና መስሪያ ቤት ለአስቸኳይ ሥራ የተፈለገ መሆኑን ነግሮ በጥድፊያ አካባቢውን ጥሎ ተሰወረ፡፡

ገበሬዎቹ ሰብሰባው አለመኖሩን ሲያውቁ ወደ የግል ጉዳያቸው ለመሄድ መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡ ድንገት ግን የጥይት ድምጽ ተሰማ፡፡ ድንጋጤ ተፈጠረ፡፡ ወዲያው ወታደር የጫነ

መኪና ሲበር መጥቶ ከትርምሱ መሀል ቆመ፡፡ ወታደሮቹ መኪናው ላይ ወርደው መሳሪያቸውን እየደገኑ አካባቢውን በፍጥነት ተቆጣጠሩት፡፡

«እጅ ወደ ላይ!» አለ ጥይት የተኮሰው ወታደር፡፡ ሁሉም ገበሬ ድንገት በተከሰተው ሆኔታ ተደናግጦ እንደታዘዘው ሁለት እጁን ችቦ አሰመስሎ ወደላይ ሰቀለ፡፡

«እጃችሁን ወደ ላይ እንደ ዘረጋችሁ በያላችሁበት ተንበርከኩ!» ወታደሩ ጠንከር ያለ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ እንደ ታዘዙት አደረጉ፡፡

«የታለ? በዚህ ፍጥነት የት ሊሄድ ይችላል? የት ደበቃችሁት?» አለ ዐይኑን እያጉረጠረጠ፡፡ ገበሬዎቹ ስለማን እንደሚያወራ እንኳን አልገባቸውም፡፡ የባሰ ተደናገጡ፡፡

«የገበሬ ማኅበሩ ሊቀመንበር ማን ነው?» ሲል በጩኸት ጠየቀ ተኳሹ ወታደር፡፡

«እኔ ነኝ» አለ ምናለ የሚባለው ገበሬ እጁን ሰቅሎ እንደ ተንበረከከ፡፡

«ኮሚቴዎቹን በሙሉ ይዘህ ና ወደ እዚህ ውጣ!» አለ አሁንም በቁጣ፡፡ ምናለ የገበሬ ማኅበሩን አስራ አምስት ኮሚቴዎች ይዞ ወደ ፊት ቀረበ፡፡

«ሁላችሁም ከመነዳታችሁ በፊት ከደበቃችሁበት አውጥታችሁ ብታስረክቡን ይሻላችኋል፡፡ ያለዚያ በእሱ ጦስ ሁላችሁም ታልቃላችሁ!!» አለ ወታደሩ ኮሚቴዎች ላይ አፍጥጦ፡፡

«ማንን ነው አውጥተን የምንሰጠው ጌታዬ? ጉዳዩ ምን እንደ ሆነ ሳይነግሩን? የነገሩ ውል አልገባንም እኮ!» አለ ምናለ ወታደሩን በመገረም እየተመለከተ፡፡

«ሙች አጣኸው አንተ አወናባጅ!» ብሎ በሰደፍ ደረቱ ላይ መታው፡፡ ምናለ ወደ ኋላው ሊወድቅ ለጥቂት ተንገዳግዶ ቆመ፡፡ «ዛሬ ለሰብሰባ የጠራችሁ የግብርና ሰራተኛ የታለ? በዚህ ፍጥነት የት ሊሄድ ይችላል? ከየትም ጎርጉራችሁ አውጥታችሁ ካላስረከባችሁን ሁላችሁም ታልቃላችሁ!» በንዴት ተንቀራጠጠ ወታደሩ፡፡

«አቶ ይነበብን ማለትም ተሆነ 'ወረታ የወረዳው ግብርና መሥሪያ ቤት ለአስቸኳይ ሥራ ፈልጎኝ መሄዴ ነው' ብሎን ሰብሰባውን ትቶ አሁን ወደ ወረታ ተመለሰ እኮ፡፡ መንገድ ላይ ተላልፋችሁ ይሆናል» አሉ አንድ አዛውንት፡፡ እጃቸውን ራሳቸው ላይ አድርገው በተንበረከኩበት እየተንቀጠቀጡ፡፡

«ይች ማደናገሪያ ናት፡፡ አሁን እዚህ አንደ ነበር ጥቆማ ደርሶናል፡፡ አንዳችሁ ቤት ደብቃችሁት ካልሆነ በስተቀር በዚህ ፍጥነት የትም ሊሄድ አይችልም፡፡ አምጥታችሁ እጁን ካልሰጣችሁን በአንድ ሰው ጦስ ሁላችሁም ወደ ጎንደር ትነዷታላችሁ» አለ ወታደሩ

በዛቻ:: ገበሬዎቹ የማያውቁት ነገር ስለ ሆነባቸው እርስ በርስ ተያዩ:: እውነቱን ተናግረዋል:: የሚያምናቸው ጠፋ:: ሁሉም አንገታቸውን ደፍተው ዝም አሉ:: በዝምታቸው የጠፉት ወታደሮች አርሶ አደሮችን በሰደፍ እያዳፉ ያዋከቧቸው ጀመር:: ደጋግመው ወረታ ግብርና መስሪያ ቤት ተጠርቶ መሄዱን እየማሉ እየተገዘቱ ነገሩ:: ሊቀበሏቸው አልቻሉም:: አንድ ከባህርዳር የመጣ መለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብስ አስቆሙ:: ተሳፋሪውን በሙሉ አስወርደው ከስልሳ የማያንሱ ገበሬዎችን ጠቅጥቀው ጫኗቸው:: የአገሬው ሰው ግልብጥ ብሎ ከመድረሱ በፊት ቶሎ ጉዞ እንዲጀምር ሹፌሩ ኃይለኛ ትዛዝ ተሰጠው:: ሹፌሩ መኪናውን አስጓርቶ እንደ ጥይት ተወረወረ:: ወረታ ከመድረሱ በፊት ወደ ቀኝ ታጥፎ በጠባቧ ኮረኮንች መንገድ እንዲገባ አሁንም ከባድ ትዕዛዝ ተሰጠው:: ከወረታ ከተማ ትንሽ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው ብሔራዊ የጦር ማሰልጠኛ ተቋም ካስገቧቸው በኋላ ገበሬዎቹን ቁም ስቅላቸውን ያሳዩዋቸው ጀመር::

ይነበብ ወሬው የደረሰው ራሱን ደብቆ ጉዞ በጀመረበት ለዓት ነበር:: መንገድ መሪ አንድ ጓድ ተሰማ የተባለ ገበሬ አብሮት አለ:: እንዳንድ ጊዜ ዋናውን መንገድ እያሳበሩ በእሳቻ መንገድ ወደ ጎንደር እየገሰገሱ ነበር:: አቅጣጫ እንዳይስቱም አልፎ አልፎ ዋናውን መንገድ መያዛቸው አልቀረም:: ከገቡበት አሳባሪ መንገድ ወጣ ሲሉ አንድ ባላገር የሩጫ ያህል እየገሰገሰ ከወደ ጉማራ ሲመጣ ተመከቱ:: እነሱ ላይ ከመድረሱ በፊት ከመንገድ ወጣ ብለው ጉድባ ውስጥ ገቡ:: ጉድባው አጠገብ አጅብ ብለው የበቀሉ ዛፎች አሉ:: እየቀረበ ሲመጣ ማንነቱ ተለየ:: የሸኘው ገበሬ የተሰማ ቅርብ ዘመድ ነው:: አጠገባቸው ሲደርስ ተሰማ ሦስት ጊዜ የፉጨት ድምጽ አሰማ:: ያ ሲሮጥ የመጣ ገበሬ ቀጥ ብሎ ቆመ:: ፉጨት ወደ ለማበት አቅጣጫ ሲዞር ተሰማ ከጉድባው ብቅ ሲል ተመለከተው:: ተገናኙ:: በገበሬዎች ላይ የደረሰውን ሁሉ ሲነግረው ጭንቀትና ድንጋጤ ውጦት ይንቀጠቀጣል:: ይነበብ ዛፉን ተጠልሎ በደንብ እስተውሎታል:: መልካም ወሬ ይዞ እንዳልመጣ ካኳኋኑ ገብቶታል:: ቀጥታውን ወደእነሱ ሄዶ ተቀላቀላቸው:: ይነበብ በገበሬዎች ላይ የሆነውን ሲሰማ እላመነታም:: ተመልሶ ሄዶ እጁን ለፖሊስ ሊሰጥ ቆረጠ::

«እንኳንም እርቄ ከሄድኩ አልሆነ:: በእኔ ምክንያት ገበሬዎቹ እንግልትና ስቃይ ሊቀበሉ አይገባም:: አሁኑኑ በዚሁ ሄጄ ለወረታ ፖሊስ ጣቢያ እጄን እሰጣለሁ» አለ ይነበብ ፊቱን ወደ ወረታ መንገድ መልሶ::

«ቆ---ይ! ቆይማ ጋሼ ይነበብ:: ስከን ብሎ ያሰቡበት ነገር ይበጃል» አለ ተሰማ::

«ገበሬዎቹ በማያውቁት ነገር እየተሰቃዩ ነው:: ጊዜ ማጥፋት አይኖርብኝም ተሰማ:: በእኔ ምክንያት ከሰልሳ በላይ ሰው ይሰቃይና ይሙት ብዬ አልፈርድም» አለ ይነበብ:: እጅ በመስጠቱ ቆርጦ::

«ሌላ መላ ከታጣ እጅ መስጠቱን ማን ይነሳሀል ጋሼ ይነበብ? ቆይማ ግድ የለህም፤ አቅልን ሰብሰብ አድርጎ መመካከሩ አይከፋም» አለ ተሰማ ደገመና:: ምን ቢደረግ እንደሚሻል የአዕምሮውን ጓዳ እየፈተሸ::

«እዚያ ያሉት የገበሬ ማኅበር ጓዶቻችን እንድ ሲመካከሩበት የነበረ ሐሳብ ነበር ድንገት የሚጠቅም ተሆነ» አለ መላኩተኛው ገበሬ ዝም ብሎ ቆይቶ::

«ሰትሮጥ የመጣህበትን መልዕከት ቅድሙኑ እሚጠህ አትነግረንም ኑሯል ዛዲያ! ተጨንቀን እያየኸን! የምን ቆንጥሮ ማስቀረት ነው? እንዴት ያለኸው ዋዘኛ ሰው ነህ እያ! በል አሁንም ፈጠን በል አጠር አድርገህ ንገረን» አለ ተሰማ ተቆጥቶ::

«ኧረገኝ! ኧረ እትቆጣ እየዋ ተሰማ! ድንጋጤዬ መች ገና ለቀቀኝ ብለህ ነው:: ድንገት ሳያችሁ እኮ አንዳች ነገር ነው ክው ያደረገኝ:: እሁን ገና ነው እቅሌን መሰብሰብ የጀመርኩት» አለ መላከተኛው ገበሬ::

«ኧረ ወዲያልህ እያ! በል ከርከሩን ተወውና የሰማኸውን ሁሉ አንድ ሳታስቀር ንገረን:: ምን ይታወቃል የሚበጅ ነገር እናገኝበት ይሆናል» አለ ተሰማ እንደ ተቆጣ::

«በዚህ አካባቢ ከሚገኙት ገበሬ ማኅበራት ውስጥ የሚለራ ሁነኛ ጓድ ከተገኘ በዚያ በኩል ምህረት ጠይቆ እጁን ቢሰጥ ይሻላል:: ከተቻለ የምህረት ደብዳቤ እጥፎ በእጁ ቢይዝ ጉዳዩን ያቀልለት ይሆናል:: ሆነም ቀረ ዝም ብሎ እጁን ለቦሊስ ከሚሰጥ ምህረት መጠየቁ አይከፋም' እያሉ እነእየዋ ምናለ ሲመካከሩ ሰምቼ ነበር:: የሚሆን ተሆነ እንግዴህ» ብሎ ዝም አለ::

«ዛዲያ ከዚህ የበለጠ ምን መልካም ሐሳብ አለ? በል ጋሼ ይነበብ ለቦሊስ ዝም ብሎ እጅ ከመስጠት በገበሬ ማኅበር ጥፈት ቤት በኩል ምሕረት ጠይቆ መግባቱ የተሻለ ዘዴ ሳይሆን አይቀርም:: ለመሆኑ በዚህ በቅርብ የሚገኙ ገበሬ ቀበሌዎች ውስጥ እነማነን እናውቃለን?» ብሎ የራሱ የሆኑ ሁነኛ ሰዎችን ማሰብ ጀመረ ተሰማ::

«የናበጋ ጌዎርጊስ ገበሬ ቀበሌ ማኅበር ሊቀመንበር የትሩፋት ማለት የባለቤቴ እኅት እኮ ነው» አለ ይነበብ ትንሽ የተሰፋ ጭላንጭል እየታየው::

«ኧረግ እግዚሀር ይስጥህ! እንዲያማ ተሆነ ናበጋ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ውስጥ እኮ ነው ያለነው:: እሱ የሚታየው ቆርቆሮ ጊዎርጊስ ቤተክርስቲያን እንጂ ነው:: በል እኔና ጋሼ ይነበብ ወደ እዚያው በፍጥነት እንገስግለ:: አንተ በመጣህበት ሳይሆን በሌላ መንገድ አድርገህ ወደ ጉማራ ተመለስ» አለው ተሰማ መላከተኛውን::

******

የናበጋ ጊዮርጊስ ገበሬ ማኅበር ሊቀመንበር ይነበብንና የምህረት ደብዳቤውን ይዞ ለወረታ ወረዳ አስተዳደር አስረከበ። ይነበብ ለጊዜው ፖሊስ ጣቢያ እንዲያርፍ ተደረገ። የወረታ አስተዳደር «ምህረቱን ተቀብያለሁ» ቢልም ቃሉን አጠፈ። ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንኳን አላሳደረውም። ሌሊቱን አሸሽቶት አደረ።

ይነበብ የልጁ ክርስትና መነሻ ቀን ቢደርስም ደብዛው ጠፍቶ የትሩፋት እናት ሰድግሱ ሽር-ጉድ በሚሉበት ወቅት ነበር ይህ ዱብዳ የደረሰው። ትሩፋትን እንቅልፍ ነሳት። ሌላው ቢቀር የሆነውን ነገር እንኳ ማወቅ ይኖርባታል። በወታደራዊው የደርግ መንግሥት "ምህረት ሰጥተናችኋል" ከተባሉ በኋላ የት እንደ ገቡ የማይታወቁ ብዙ ሰዎች መኖራቸውን ታውቃለች። እንኳን አሁን በዚህ የአብዮት ቀውጢ ሰዓት ይቅርና አንጻራዊ መረጋጋት በነበረበት በኃይለሥላሴ ዘመን መንግሥትም ሰዎች ይሰወራሉ። የገቡበት ሳይታወቅ እንደ ወጡ ይቀራሉ። የደርግ አምባገነን መንግሥት ምህረት ከሰጠ በኋላ ቃሉን ለማጠፍ የሚያግደው የሕግም ሆነ የሞራል ዳኝነት የለውም። በስልጣኑ የመጣ የመሰለውን ሁሉ ከማጥፋት አይመለስም። ትሩፋትን የጨነቃት የሆነውን አለማወቋ ነው። ቁርጡን እስከታውቅ ሞቱን ወይ ሽረቱን እስከትለይ ድረስ የፍሊጋ ጉዞዋ አይቆምም..... እናቷ በበኩላቸው ተጨንቀዋል። እራስ ልጃቸው ከቤት ወጥታ እንዳትሄድ እየወተወቱ ነው። ክርስትና ሳታስነሳ ጸበል ሳትረጭ ከቤት ብትወጣ ለከፉ መንፈስ ትጋለጣለች ብለው ሰግተዋል።

«ትሩፋቴ አንቺ ከምትኸጂ ከተማው እንዳያደናግራቸው እንጂ ተዘመዶቻችን አንድ ሁለቱን ለምኜ ኸደው በየስር ቤቱ እንዲያጠያይቁት ባደርግ ይሻላል ልጄ አባከሽ። በዜት--በዜት እንደ ሚሄዱ ብቻ አስጠንቶ መላክ ነው» አሉ የትሩፋት እናት። የተሻለ የመሰላቸውን አማራጭ እያቀረቡ ።

«የቀይ ኮከብ ዘመቻ የሚባል አዋጅ መጥቷል ታትዬ። ወጣት ሁሉ ለወታደርነት እየታፈሰ ነው። የሰው ሰው ሰድጄ እሳት ውስጥ አልጨምርም። አንቺንም ከዘመድ ጋር አላቆራርጥሽም። ወረታ ከሄዱ ወዲያው ነው ካምፕ የሚያስገቧቸው።»

«ወይ እበሳዬ! ኧረ እንዴት ካለው እስጨናቂ ጊዜ ላይ አደረስከን ጌታዬ!!» አሉ ጭ--ንቅ ጥ--ብብ እያላቸው።

«አትጨነቂ ታትዬ ግድ የለሽም። እኔ ምንም አልሆንም። ብቻ ልጄን ብርድ እንዳይመታው ተጠንቅቀሽ ያዥልኝ። ባገኘውም– ባላገኘውም ጎንደር በየእስር ቤቱ ካፈላለግሁት በኋላ ቶሎ እመለሳለሁ።»

«ኧረገግኝ! ልጄማ ምን ይሆን ብለሽው? እናንተን ያሳደግሁ የእናንተ እናት አይደለሁ። ጡጦውን እያጠባሁ ከጉያዬም አላወጣው። የጨነቀኝ ያንቺ ነገር ነው እንጂ ልጄ።

የማርያም አራስ-- በወጉ ሳትታረሺ» እንደ ቆረጠች ሲያዉቁ «እስቲ ለነፍስ አባቴ ልላከባቸውና ባይሆን መልካ ሚካኤልን ደግመው ፀበል ይርጩሽ» አሉ እናቷ።

«ባታደከሚያቸው ደስ ይለኝ ነበር። ይምጡ ካልሽ ግን እሺ እስጠሪያቸው» አለች ትሩፋት። እናቷን ደስ እንዲላቸው።

ትሩፋት ጎንደር አለ የተባለ እስር ቤት ሁሉ አልቀራትም። ስንቅ ቋጥራ ስሙን ታስጠራለች። የምታገኘው መልስ ግን «ይነበብ መዝገቡ የሚባል እስረኛ እዚህ የለም» የሚል ነበር። ተስፋ ቆርጣ እርሟን ልታወጣ ስትል አንድ ወሬ ደረሳት። ወረታ ካለው ብሔራዊ ጦር ካምፕ ውስጥ መታየቱንና በሚቀጥለው ቀን ወደ ባህርዳር መወሰዱን ነገሯት። ባህርዳር ገብቶ አዳሪውን የመጨረሻ አውቶብስ ለመያዝ አራዳ አውቶብስ መናኸሪያ ለመድረስ ተጣደፈች።

******

እለተ እሁድ--- እስረኛ ጠያቂ ቤተሰብ ሁሉ ጣና ዳር የተንጣለለውን በዘመናዊ ሞድ የተገነባውን አዲሱን ጣና ሆቴል በርቀት ይመለከታል። የልጁን ወይ የአባቱን ወይ የእናቱን፣ የወንድሙን ወይ የእህቱን፣ የባሉን-ወይ የሚስቱን የዘመድ ወይ የጓደኛውን.... መምጣት በናፍቆት ይጠባበቃል። እንዳለመታደል ሆኖ ለመዝናኛነት የተገነባው ዘመናዊው ጣና ሆቴል የፖለቲካ እስረኞች ማጎሪያ ሆኖ አርፎታል። አንዳንድ ጊዜ የአርባ ቀን እድል ለሰው ብቻ የተሰጠች አይደለችም ያሰኛል የጣና ሆቴልን ነገር ሲመለከቱት።

እስረኞች ከታሰሩበት ክፍል ወጥተው ወደ መጠየቂያው ቦታ ሲመጡ ትሩፋት ይነበብን ገና ከርቀት ነበር የለየችው። የሰበሰው እሮጌ ጋቢ አላሳሳታትም። የታጠቀው ሽንሽን ቁምጣ ሱሪው ቋንጃውን ያስረዘመው መሰላት። አጭር ሽንሽን ቀሚስ የለበሰች ወንዳወንድ ሴት አስመስሎታል። ያኔ ወደ ጎንደር ሲሄድ ሲነሳ ገበሬ እንዲመስል ተሰማ የሰጠውን የገበሬ ቁምጣ ሱሪና ጋቢ እንደ ለበሰ ነበር ምህረት ጠይቆ እጁን የሰጠው።

«እንኳንም ሴት ያልሆነ። ሴት መሆን አያምርበትም ነበር» አለች ለራሷ። ፈገግ እንደ ማለት ብላ። ይነበብ በህልም ዓለም ያለ ይመስላል። በደመነፍስ ነው የሚራመደው። ስሙን ስትጠራው እንኳን የሰማት ዘግይቶ ነበር።

«እዚህ እንዳመጡኝ በምን አወቅሽ? እንዲህ በአጭር ጊዜ ውስጥ የምንገናኝ አልመሰለኝም ነበር» አላት። ከሄደበት የህልም አለም ሲመለስ።

«ጠፍተህ የምትቀር መስሎህ ነበር? እይጥ ጉድጓድ ውስጥ ብትገባ እንኳ አታመልጠኝም ነበር» አለችው የግድ ሳቅ ለመሳቅ እየሞከረች። አሳሪዎቹ ከጎንደር ከፍለ ሀገር እንዴት ጎጃም ከፍለ ሀገር እንዳመጡት እንኳን እሷ ይነበብ ራሱ የሚያውቀው ነገር የለም።

አጋጣሚውን ግን ወዳዋለች፡፡ በቀይ ሽብር የመመታት እድል ከጎንደር ከፍለ ሀገር ይልቅ ጎጃም ይቀላል ይባላል፡፡ የጎንደሩ የደርግ ተጠሪና ዋና አስተዳዳሪ በከፍለ ሀገሩ አንድ ወጣት አይቅር የተባሉ ይመስል እንደ ገብስ እያጨዱ ይከምሩት ይዘዋል፡፡ በለስ ቀንቶት ከመረሸን ወይ ከመታሰር የተረፈው ወጣት ደግሞ አገር ጥሎ ይሰደዳል፡፡ እድሜ ለጎረቤት አገር ሱዳን-- ወደ ዚያው ይጎርፋል፡፡

«ቴዎድሮስ እንዴት ነው?» አለ አይቶ ያልጠገበው የልጁ ናፍቆት ጥፍር አውጥቶ ውስጥ አንጀቱን ቡጥጥ እያደረገው፡፡ «የልጅ ፍቅር ለካ እንዲህ ልብን ያንሰፈስፋል?» አለ ሰራሱ፡፡ ወኔው ሁሉ ከዳው፡፡

«ደህና ነው፡፡ መቼም አራስ ልጅ አዚህ አምጥቼ እንዳላይህ እንዳማትጠብቅ ነው የሚገባኝ፡፡» ገና ነፍሰጡር እያለች በስም አውጣጥና በፆታ እንዴት ይጨቃጨቁ እንደ ነበር!

«ልጃችን ሴት ነው የምትሆነው፤ ደግሞ ቁርጥ እኔን፡፡ ስሟንም ነፃነት እላታለሁ፡፡» ትላለች ትሩፋት ሆዷን እየደባበሰች፡

«ይነበብ ም--ን አለ በይኝት ትሩፌ! ወንድ ነው የሚሆነው፡፡ ስሙንም ቴዎድሮስ እንለዋለን፡፡ ቴዎድሮስ ይነበብ ታሪኩ፡፡ ስም አወጣጥ ይሉሻል እንደዚህ ነው፡፡ ትርጉም የሚሰጥ፡፡ ታሪክ የሚዘከር-- ቅኔ እኮ ነው አባከሽ!» ይላታል ሆድ ሆዷን እያየና እሱም በእጁ እየደባበሰ፡፡ እንደ ተመኘው ወንድ ሆነለት፡፡ ስሙም ቴዎድሮስ ሆነ፡፡ በእስረኛና በጠያቂ መለያ ግንዱ በላይ እጆቻቸው እንደ ተጨባበጡ ትዝታው በሁለቱም ልብ ውስጥ ሽው ብሎ አለፈ፡፡

«ያንቺም መምጣት ገርሞኛል፡፡ እናትሽ እንዴት እሺ ብለው ለቀቁሽ?»

«ከርስትና ሳላሰነሳ ከቤት እንዳልወጣ ያላደረገችው ጥረት አልነበረም፡፡ መውደቂያህን ማወቅ ስለ ነበረብኝ እንቢ አልኳት» አለች ትሩፋት፡፡ የእናቷ ጭንቀት እየታሰባት፡፡

«አዚህ መሆኔን ማን ነገረሽ? በጨለማ ይዘውኝ ስለ መጡ ማንም አላየኝም ነበር፡፡ እንዲህ በቅርብ ጊዜ እንገናኛለን የሚል ተስፋ አልነበረኝም» አላት ደግሞ፡፡

«የጎንደር እስር ቤት አንድ አልቀረኝም፡፡ ተስፋዬ ሁሉ ተሟጦ አልቆ እርፌ ልቀመጥ ነበር፡፡ ኋላ ላይ ግን እዚህ ልትሆን እንደ ምትችል ወፍ ነገረችኝ» አለች ትሩፋት ሁኔታውን እያጤነች፡፡

«በእኔ ምክንያት ታስረው ከነበሩት አብዛኞቹ ገበሬዎች በመፈታታቸው ደስተኛ ነኝ፡፡ ሦስቱ ገበሬዎች ግን እንዳልተለቀቁ ሰምቻለሁ፡፡ ወደ ጎንደር ባታ ወህኒ ቤት ሳይነዷቸው አይቀሩም» አላት ሀዘን ልቡን እያደማው፡፡

እስረኞች ወደ ክፍላቸው እንዲመለሱ የማስጠንቀቂያ ፊሽካ ተነፋ፡፡ ጠያቂም-- እስረኛም ወደ ኋላው ማፈግፈግ ጀመረ፡፡ ቁርጥ አድርጎ የተለያየ ባለመኖሩ ድጋሚ ፊሽካ ተነፋ፡፡ እስረኛው ሁሉ ወደ ክፍሉ አዘገመ፡፡ ትሩፋት በቆመችበት ሆና ይነበብ ከከፍሉ እስኪገባ ድረስ ተመለከተችው፡፡ መለወጫ ልብስ ያስፈልገዋል፡፡ ወደ ከተማው አምብርት ገሰገሰች፡፡

******

ትሩፋት ወደ ሥራዋ ገና አልተመለሰችችም፡፡ ደመወዟን ግን በፎገራ ወረዳ በወረታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት በኩል በጊዜያዊነት እንዲከፈላት ተወስኖላታል፡፡ ከቦታ ቦታ ስትንቀሳቀስ የይለፍ ደብዳቤ የምታጽፈውም እዚሁ ወረታ ነው፡፡ የስራ ቦታዋና ቋሚ መኖሪያዋ የት እንደ ሆነ ገና ለለማታውቅ ለጊዜው ያለችው እዚያው ከእናቷ ጋር ነው፡፡ ድርጅታዊ ስራዋ ባታ ወህኒ ቤት ከወረደች ወዲህ ተቋርጧል፡፡ እንዲሁ ግራ ገብቷት ተቀምጣለች፡፡ እሁድ እሁድ ይነበብን ለመጠየቅ ባህርዳር መሄዷ ብቻ የማይቀር ዋና ተግባሯ ሆኗል፡፡

«ዛሬ የእስረኛ መጠየቂያ ቀን አይደለም፡፡ ላልተወሰነ ጊዜ መከልከሉን አልሰማሽም እንዴ ዝም ብለሽ ስትንተች የምትመጭው! ስታስቢው የእስረኛ መጠየቂያ ቀን ቢሆን ኖሮ አካባቢው እንደዚህ ፀጥ- ረጭ የሚል ይመስልሻል? ምን ነገር የማይገበዋ ናት እባካችሁ!» ጮኽባት በር ላይ ሰው ወታደር ፊቱን አኮሳትሮ፡፡ የንሰር አሞራ ዐይን በመሰሉ ዐይኖቹ አተኩሮ እየተመለከታት፡፡ ደነገጠች ትሩፋት፡፡

«ዛሬ ደግሞ አዴት ያለው ከፉ ለካፌ ወታደር ገጠመኝ እባካችሁ፡፡ ምን ይሻለኛል?» አለች በልቧ፡፡ ሦስት የፖለቲካ እስረኞች ጣና ሀይቅ ውስጥ ራሳቸውን ወርውረው ሕይወታቸውን ካጠፉ ወዲህ ሁሉም ነገር ጠብቋል፡፡ እነሱ ሰበብ ሆነው እስረኛው ሁሉ አዲስ ወደ ተገነባው ወህኒ ቤት ከተዛወረ ይኸው ድፍን አንድ ወሩ፡፡ ቢቸግር ነው እንጂ አዲሱን ወህኒ ቤትም በምዕራባዊ ሰሜን በኩል አብዛኛውን ጎኑን የሚያዋስነው ይኸው የጣና ሀይቅ ነው፡፡ ተወርውሮ ለመሞት የፈለገ እስረኛ-- አዚህም ሀይቁ አፉን በሰፊው ከፍቶ ይጠብቀዋል፡፡

«አንቺን እኮ ነው! ምን ይገትርሻል!? እስረኛ መጠየቂያ ቀን አይደለም እያልኩሽ አይደል!? በመጣ እግርሽ ተመልሰሽ አዚህ አካባቢ ጥፊ ብዬሻለሁ!!» ቁጣው! በዚያ ላይ ጩኸቱ! ሩቅ

ላለ ሰው የሚናገር ይመስላል:: በእርግጠኝነት ቢሮው በር ላይ የቆመው ሌላው ወታደር ይሰማዋል::

«ማየት ከተከለከለ የቆሸሸ ልብስና የምግብ ሳህንስ መውሰድ አይፈቀድልኝም? ከተቻለ ይህንን የያዝኩትን ምግብም ላቀብል ነበር:: ከጎንደር ከፍለ ሀገር ነው የመጣሁ:: የዛሬው እሁድ አሰረኛ የማይጠየቅበት መሆኑን አላወቅሁም ነበር» አለች ትሩፋት በተቻላት መጠን አለሳልሳና አስተዛዝና::

«ከጎንደር ከፍለ ሀገር ለመምጣትሽ መታወቂያና የይለፍ ደብዳቤ ይዘሻል?» አንደ ተቆጣ ነበር የጠየቃት::

«አዎ ይዣለሁ» አለች ቀልጠፍ ብላ:: መታወቂያና የይለፍ ደብዳቤ ቦርሳዋ ውስጥ አውጥታ ልትሰጠው ስትል

«አዚያው ቁሚ! አንዳትንቀሳቀሺ! አንቀሳቀሰለሁ ብትይ አንችም ገብተሽ ትቀፈደጃታለሽ! ለእለቱ ተረኛ ኃላፊ ላሳይልሽና ከፈቀደልሽ የያዝሽውን ስንቅ ታቀብያለሽ፤ ካልተፈቀደልሽ ደግሞ በመጣ እግርሽ ትመለሻታለሽ!» አያለ መታወቂያዋንና የይለፍ ደብዳቤዋን ሲቀበላት በዐይኑ ጠቀስ አድርጎ የሆነ ምልከት አሳያት ተግባቡ:: ተረጋጋች:: የይለፍ ደብዳቤዋንና መታወቂያዋን ለአለቃው አሳይቶ ተመለሰ::

«የያዝሽውን ምግብ አዚህ አስመርምሪና ቅመሽ!» አላት እሁንም በቁጣ:: አልደነገጠችም:: ምግቡን አድርሶ የቆሸሸ ልብስና ባዶ ሳህን ሲያቀብላት ሁሉ ግስላ እንደ መሰለ ነበር::

«ሰሞኑን ተዘዋዋሪ የደርግ መርማሪዎች ከአዲስ አበባ ይመጣሉ:: ከባድ ምርመራ ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል:: አሰረኛው ሁሉ ኢንፎርሜሽን ይቀባበላል ተብሎ ስለተፈራ ከቤተሰብ ጋር መገናኘት ተከልክሏል:: አንቺም ባትመጭና እዚህ ባትታይ ይሻላል:: ለሌላ ተልዕኮ የምትመጭ ስለሚመስላቸው አደጋ አለው:: አላስፈላጊ መስዋእትነ ደግሞ ተገቢ አይመስለኝም» አላት በሹክሹክታ:: አቃውን የሚፈትሽ መስሎ:: ልብሱን ሲፈትሽ ጎርበጥ ያለ ነገር ቢያገኝበትም ሌላው ተረኛ ዘብ ከመምጣቱ በፊት ጠቅለል አድርጎ ቶሎ አቀበላት::

ያን ቅፍፍ የሚል ጥላ የተጫነውን ወህኒ ቤት ለቃ ከአካባቢው ለመጥፋት ተጣደፈች:: ባለ በሌለ ኃይሏ ነጠቅ--ነጠቅ እያለች ተራመደች:: መናኸሪያ ስትደርስ ጎንደር ገብቶ አዳሪው አውቶብስ ሊወጣ ሲል ደረሰችበት:: ስትገባ ቦታ የለም:: ወደ መጨረሻው ወንበር ሄዳ ተጣባ ለሰባት ተቀመጠች:: መንገዱን ሁሉ በሐሳብ ስትናውዝ ወረታ መድረሷን እንኳ አላወቀችውም ነበር:: ረዳቱ «የወረታ ተሳፋሪዎች ትኬቱን መልሱና ቶሎ ውረዱ» ሲል ባና ወንበሩ ላይ ተነሳች:: ከአናቷ መንደር የደረሰችው ከመሽ ነበር:: አቤት እንደ ገባች እረፍት ልውሰድ እንኳ አላለችም:: ልብሱን ከወታደሩ ስትቀበል እጇን የሆነ ዳጎስ ያለ ነገር

ተሰምቷት ነበር:: በጥንቃቄ ተጣጥፎ የተደበቀ ወረቀት አገኘች:: ትንፋሿን ውጣ ተደላድላ ተቀመጠች:: ረጅሙን ደብዳቤ በጽሞና ለማንበብ----

«ትሩፋት ምን ብዬ ልጀምር:: ለካ የውስጥን ስሜት ግልጥልጥ አድርጎ ለሚወዱት ሰው ለማሳየትና ለመግለጽ ቃላት ማግኘት ይቸግራል:: ናፍቆቴ ፍንትው ብሎ እንዲታይሽና የሚለማኝ ሁሉ እንዲሰማሽ ለማድረግ አልቻልኩም:: እንዴት አድርጌ መጻፍ እንደምጀምር እንኳ አላውቅም:: ብቻ አዚች ላይ ታቿ የትኋንና የቁንጫ ሰራዊት በሚርመሰመስበት የምድር ላይ ሲዖል በሆነች ከፍል ውስጥ ነኝ:: ቀኑን ሙሉ--- ሌሊቱን ሙሉ ስለአንቺና ስለማላውቀው ልጃችን---- ስለ ድርጅታችን እንዲሁም የመከራ ጉዞዋ ገና ስላላቀው አገራችን ሳስብ ውዬ ሳስብ አድራለሁ::

አራት በሦስት በማትሆን ከፍል ውስጥ ሰልሳ ሰዎች ታጉረንባታል:: በወረፋ አንተኛለን--- በወረፋ እንቆማለን---በወረፋ አንቀመጣለን:: እስቢው--- በባህርዳር ቃጥሎ ፀሐይ በዚች በተዘጋች ከፍል ውስጥ ሙቀቱ ምን ያህል እንደ ንፍሮ እንደሚቀቅለን:: የራሳችን ትንፋሽ አንፋሎት ሆኖ ጣሪያው ላይ ጤዛ ይሰራል:: ጥቂት ቆይቶ ደግሞ የጣራውን ቆርቆሮ ቆሻሻ ሁሉ ይዞ ተመልሶ እኛው ላይ ይንጠባጠባል:: ልብሳችን ሁሉ ጀማሪ ሰዐሊ ሸራው ላይ የረጨው ቀለም ይመስላል:: ይገርምሻል ትሩፌ! በዚህ ጭንቅ የሕይወት ፈተና ውስጥ ሆኜ እንኳ አንችን ሳስብ የመኖር ፍላጎቴ ይጨምራል:: ባይገርምሽ አዲስ ጉልበት-- አዲስ ሞራል አገኛለሁ:: ፍቅር ኃያል ነው:: ፍቅር ጉልበት ነው:: እኔ ደግሞ በደርብርብ ፍቅር የተያዝኩ ሰው ነኝ:: ባንች ፍቅር---በድርጅቴ ፍቅር--- ባገሬ ፍቅር— አሁን ደግሞ አዲስ በተወለደው ልጃችን ፍቅር:: ዐይኑን አፍጦ---አፉን ከፍቶ ሊውጠኝ ከሚጠብቀኝ የሞት መንጋጋ በፍቅር ኃይል---በፍቅር ጉልበት ፈልቅቄ እንደምወጣ ለቅጽበት እንኳ ተጠራጥሬ አላውቅም::

ኢትዮጵያን በእውቀቱና በጉልበቱ ሊያሳድጋትና ሊያበለጽጋት የሚችለው ትኩስ የወጣት ጭንቅላትና ጉልበት በየስር ቤቱ ተቆልፎበት በከንቱ ማለፉን ሳስበው ቁጭት እንደ እግር እሳት ያንገበግበኛል:: ሰንት ታምር ሊፈጥር የሚችል አዕምሮ ከፍት የሆነ ምሁር ለዚች አገር በጎ አስቦ--- በጎ አልሞ ---- በጎ ተመኝቶ መነሳቱ የአስተሳሰብ ድህ በሆኑ የአገሪቱ አምባገነን መሪዎች እንደ ወንጀል ተቆጥሮበት በአንዲት ጠባብ ከፍል ውስጥ ተቆልፎበት እንዲሁ ተቀምጦ ቀን ሲቆጥር ይውላል:: ለዚያውም የመኖር ተስፋው ተሟጦ አልቆ በሞት መንጋጋ ስር በዋለበት እስር ቤት ውስጥ:: ያልታደለች አገር---! በልጆቿ ተጠቅማ ማደግ---- መበልጸግ---- መዘመን ያልቻለች የምታሳዝን አገር...!

ውዴ! ደግ ማሰብና መልካም መልካሙን መመኘት ጥሩ ነው:: በዚህ በከፋ ጊዜ ውስጥ ሆኜ ብሩህ ተስፋ አድማስ ሰር ጨረሯን እንደ ፋነጠቆች የማለዳ ጮራ በሩ---ቁ ይታየኛል:: ከድህነት ወለል በታች የዋለችው ኢትዮጵያ እንደ ድሮው የዳቦ ቅርጫት ስትሆን--- ሕዝብ ራሱ ይሁነኝ ብሎ በመረጠው ሕዝባዊ መንግስት ሲስተዳደር--- ሕዝብ

ያለ ይለፍ ወረቀት በየትኛውም የአገሪቱ ክልል በነፃነት እንደ ልቡ ሲዘዋወር--- በፈለገውና በወደደው ቦታ እየሠራ በነፃነት ሲኖር--- ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ የፈለገውን ሲደግፍና ያልፈለገውን ሲነቅፍ--- «በእናውቅልሃለን» ሳይሆን በሕግ የበላይነት ትክክለኛ ፍትህ ሲያገኝ--- እውነተኛ ነፃነቱን ተጎናፅፎ ያለስጋት በሰላምና በፍቅር አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራዋን በኩራት ከፍ አድርጎ ይዞ በአንድነት ሲያውለበልብና በሕዝባዊ መንግስት ሲመራ--- ይታየኛል:: ትሩፌ እውነት እልሻለሁ ሕዝብ በእኩልነትና በወንድማማችነት እጅ ለእጅ ተያይዞ የገነባት ያደገችና የበለጸገች ኢትዮጵያን የምናይበት ጊዜ አይቀርም--ይመጣል:: ያኔ እኛም ውብ በሆነች ኢትዮጵያ ለልጃችን እህትና ወንድም ወልደንለት በፍቅር የምንኖርበት ጊዜ ከዚህ የሞት ጥላ ካጠላበት እስር ቤት ባሻገር ይታየኛል...

ለእናቴ አንድ ነኝ ታውቂያለሽ:: ዳሩ ስለ እኔ ምን የማታውቂው ታሪክ ይኖራል? ያቺ መከረኛ እናቴ እላግባብ ስታስብልኝና ስትንገበገብልኝ በእኔ ብሶ እገሰጻት ነበር፤ በእኔ ብሶ እቆጣት ነበር:: ታድያ የዘወትር መልሷ ምን እንደ ነበር ታውቂያለሽ? 'ወልደህ እየው' ትለኝ ነበር:: የማላውቀው ልጄ ናፍቆቱ እንደ በረሀ ውሃ ጥም ሲያቃጥለኝ እርግማን መሆኑ የገባኝ አሁን ነው::

እድራሻዬን ለማግኘት ብዙ እንደ ባዘንሽ ገባኝ:: ከሳ ያለውና የእራስነት ወዝ የሌለው ፊትሽ ነገረኝ:: በግ እርጄ የእባወራነት ወግ ማዕረግ ሳላሳይሽ ይባስ አደከምኩሽ:: ሀዘኔ እጥንቴ ድረስ ዘልቆ ይሰማኛል:: ለከርስትናው ልመጣ እንዴት ጓጉቼ እንደ ነበር ከቶ ስሜቴን ትረጅልኝ ይሆን? እንጃ! እኔም እንኳ የደረሰብኝን የልብ ቁስለት ልገልጽልሽ አቅም አጥቻለሁ::

አሁን ይህ ሁሉ ማለቃቀስ ምን ይባላል? አትታዘቢኝ ትሩፋት:: ታውቂያለሽ ላንቺ የሚሰማኝን የውስጥ ስሜቴን መደበቅ አይሆንልኝም:: እውነት ነው የወገን ጥሪ አለብን---ከምጧ እንገላግላት ዘንድ አገራችን ትፈልገናለች:: ዘመድኩን የተናገረው ትክክል ነበር:: '....ይህ ትውልድ የራሱን ትዳር መስርቶ የራሱን ልጅ ሲወልድ አልተፈጠረም:: የታሪክ ጥሪና አደራ አለበት...' ነበር ያለው::

ጠያቂ ዘመድ እንደሚፈልገኝ ተነግሮኝ ተጠርቼ ስወጣ በሩቁ ነበር ያየሁሽ:: ይገርምሻል! ወደ መጠየቂያው እየቀረብኩ ስመጣ ከሰው ሁሉ ተለይተሽ እንደ መላዕክ በጉም ውስጥ የምትንሳፈፊ ሆነሽ ታየሽኝ:: ከእስረኛና ከጠያቂ መለያ ግንዱ አጠገብ ቆመሽ እጅሽን እያውለበለብሽ ስትጠሪኝ ሁሉ የሰማሁሽ ዘግይቼ ነበር:: ሁሌም ሞቅ የሚያደርገኝ ፈገግታሽ በእነዚያ ምንጊዜም ልቤን ስንጥቅ በሚያደርጉት ውብ ጥርሶችሽ ታጅቦ ተቀበለኝ:: እውነቱን ልንገርሽ አይደል ትሩፌ-- የጠበኩት ግን ሌላ ነበር:: ልክ አብዛኛው ቤተሰብ እንደሚያደረው ስንገናኝ ታለቅሻለሽ ብዬ:: አላደረግሽውም:: ልውረድ አልውረድ እያለ ዐይኔን ሲቆጠቁጠኝ የነበረው የእራሴ እንባ መንተፍረቱን ወደ ውስጥ

ዘቀጠ:: በአንቺ ጽናት ራሴን እስኪታዘብ ድረስ ኮራሁ:: አላማ ቢስ ተልካሻ! ብዬ እኔኑ ወቀስኩት:: ልጃችን እናትም–አባትም ልትሆነው የምትችል ጠንካራ እናት ስላለችው ኮራሁ---- ተጽናናሁ::

ትሩፌ 'ሰው ሰው የሚሆነው ለሌላው ማሰብ ሲጀምር ነው' የሚለው የግጥም ቋጠሮሽ ዛሬ ነፍስ ዘርቶ በአንቺነትሽ ውስጥ ሲንቀሳቀስ እየሁት:: ድርጅቱ ያስታጠቀኝ ዲሲፕሊን ላልቶ---ለዓላማየ የማልቆም ልፍስፍስ ከሆንኩ----ድርጅቴንና ጓዶቼን ብቻ ሳይሆን እንቺንም እንደማጣ በትክክል የተረዳሁት ዛሬ ነው:: በጎንጮሽስ ላይ ጠብታ እንባ አለመውረዱ መንፈሴና ልቤ እንዲጠነከሩ ብርታት ሆነኝ::

የኔ ውድ በመጨረሻ ሁለት ነገር ላሳሰብሽ እወዳለሁ:: አንድ ውጊያ ሜዳ ላይ ተማርኮ የተያዘ ጓዳችን ከምትገምቺው በላይ በድብደባ ብዛት ተጎድቷል:: አንድም እንኳን ጠያቂ ዘመድ የለውም:: እስረኛው ሁሉ እንክብካቤ ቢያደርግለትም ሊያገግም አልቻለም:: ልብሱም እላዩ ላይ ተቦጫጭቋል:: ብታይው ታዝኚለታለሽ:: እባክሽ የኔ ፍቅር ላስቸግርሽ:: ከእኔ ልብሶች የተወሰኑትን አስጠብበሽና አሳጥረሽ ይዘሽለት ነይ:: የብዙ ቤተሰብ ሃላፊ--- አሁን ደግሞ ብቸኛ ልጅ አሳዳጊ መሆንሽን አውቃለሁ:: ስትመጪ---ስትመጪ እንዳንድ ፓኮ ሲጋራ እንድትቸገሪለት ብጠይቅሽ ይሉኝታ እንዳጣሁ አድርገሽ እትውሰጅብኝ-- ሌላ ማንን ላስቸግር እችላለሁ? ሁለተኛው ማሳሰቢያ ነው:: ለኔ ማሳወቅ የምትፈልጊው ነገር ሲኖርሽ መስጠት ያለብሽ ይህንን የእኔን መልዕክት ይዞልሽ ለመጣው ወታደር ብቻ ነው:: ከሌሎቹ ተጠንቀቂ:: ታውቂያለሽ ትሩፌ? ጧትና ማታ እንደ ዳዊት የማነበንበው

በሀዘኑ ሲያዝን ደስታው ሲያስደስተው፣

ረሀቡ ሲርበዉ ጭንቁ ሲያስጨንቀው፣

ያኔ ነው-----ያኔ ነው---

ሰው መሆን-------ሰው «ሰው» የሚሆነው::

የምትለዋን የስንኝ ቋጠሮሽን ነው:: እዚህ እስር ቤት ውስጥ ሆኜ ሳስባት ደግሞ ይበልጥ ልዩ ትርጉም እየሰጠችኝ መጣች:: ሰው ሆኖ ተፈጥሮ የራሱ እምሳያ ለሆነው ሰው ማሰብ ካልቻለ ምኑን ሰው ሆነው? ለነገሩ 'ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ' የሚል ትዕዛዝ እኮ ከላይም ተሰጥቶን ነበር::

ውዴ! ምነው ችሎታሽ ለእኔ እንደ ታየኝ ሁሉ ላንቺም በታየሽ:: 'ለስሜቴ እንጂ እኔ ገጣሚ አይደለሁም' የሚል አጉል ፈሊጥ አለሽ:: በልምምድ ጥሩ ገጣሚነቱን ታገኝዋለሽ:: ግድ

የለሽም የኔ ፍቅር-- የግድ ጸጋዬ ገብረመድህንን መሆን አይጠበቅብሽም:: ከበረታሽ ግን ራስሽን የሆንሽ ጥሩ ጸሐፊ ይወጣሻል:: በርቺልኝ የእኔ ውድ:: አሁንስ አሰለቸሁሽ:: ፊት ለፊት ሆነን የማወራሽ እየመሰለኝ ማቆም አቃተኝ፤ ግን ግድ ነው ብዕሬን ልገታው ይገባል:: ሰላሙን ሁሉ እመኝልሻለሁ::

የኔ ነገር! አሰሩን ነገር እያነሳሁ ሰቀባጣጥር ለካ ዋና ቁምነገር ረሰቻለሁ:: ያን አረንጓዴ ፊልድ ጃኬቴን ወረታ ሹፌሮች ቡና ቤት ውስጥ ረሰቼው መጥቻለሁ:: ሰኞ ማለዳ ሄደሽ ጠይቂያቸው እዚያ ታገኚዋለሽ:: ያ የምወደው «ብዕሬ» ደግሞ ከጃኬቱ ኪስ ውስጥ ታገኚዋለሽ:: ድንገት ሰው አግኝቶ ወስዶት ከሆነ ግን መጠየቅ አያስፈልግሽም:: ውዴ! የምለናበትሽ የትዝታ ደም በሚተፋው «ብዕሬ» እና ---- «ልቤ» ነው»::

ያንቺው--- ይነበብ ታሪኩ:: ይላል ደብዳቤው::

ደብዳቤውን አንብባ ስትጨርስ በረጅሙ ተንፍሳ በተመሰጠ ማሰብ ጀመረች:: ደብዳቤው ውስጥ የሆነ መልዕክት ያለው መሆኑ ገብቷታል:: የፍሬ ነገሩን ጭብጥ መለየት አቅቷት ዐይኗን ግድግዳው ላይ ሰኪታ ባለችበት ብዙ ቆየች:: ደብዳቤውን መላልሳ አነበበችው:: ቁም ነገሩ የተገለጸላት መሰላትና ፈገግ አለች::

******

በወቅቱ ወረታ አሉ ከሚባሉት ቡና ቤቶች አንዱ ሹፌሮች ቡና ቤት ነበር:: ትሩፋትና ይነበብ ብዙ ጊዜ ተሰተናግደውበታል:: ሠራተኞቹ ሁሉ ያውቋቸዋል:: ትሩፋት ሰኞ እለት ለማይና ምድር ገና በወጉ ሳይላቀቅ ከሲፋጥራ በእግሯ ተጉዛ ወረታ ስትደርስ የቡና ቤቱ ሠራተኞች ቤት ያፀዳሉ:: ገብታ አንድ ጥግ ላይ ተቀመጠች::

«እትዬ ምን ይምጣልሽ» አለች ልጅ እግሯ ሠራተኛ በትህትና::

«ሻይ ከደረሰ ሻይ ይምጣልኝ አለች» ትሩፋት ለመጠጣት ሳይሆን በባዶው ወንበር ይዛ ቁጭ ላለማለት:: በአካባቢው ሴት ልጅ ብቻዋን ቡና ቤት መግባት ብዙ የተለመደ አይደለም:: የደርግ ሰላዮች ጣጣቸው አያልቅም ሌላ ጥርጣሬ ውስጥ እንዳትገባ ሰግታለች-- ግን ምንም ምርጫ የላትም:: ሰኞ ቧት ማለት ዛሬ ነው-- አሁን:: እዚሁ ተቀምጣ ካልጠበቀችው የተባለውን ሰው ላታገኘው ትችላለች::

«የሚበላስ ምን ይምጣልሽ እትዬ? በዚህ በጧት ባዶ ሻይ ልብሽን ይልጥሻል ኧረ! » አለች ያቺው ልጅ እግር አስተናጋጅ ::

«አይ ግድ የለም:: ስመጣ ቁርስ በልቻለሁ:: ሻይ ብቻ ይምጣልኝ» አለች ትሩፋት:: አንድ ሰው ገባ የትሩፋት ዐይኖች ሰውየው ላይ አነጣጠሩ:: እሷ የምትፈልገው ሰው ግን

አይደልም:: አረንጓዴ ፊልድ ጃኬት አለበሰም:: ዐይኗን ቶሎ መለሰች:: ከቡና ቤቱ-- ሰው ይገባል--- ይወጣል:: ትሩፋት ብቻ እንደ ተቀመጠች አለች:: የምትፈልገው ሰው እስካሁን ብቅ አላለም :: ተሰፋ ቆርጣ በመሄድና ባለመሄድ መካከል እየዋለለች ሰዓቷን ተመለከተች:: ብዙ የተቀመጠች መሰሏት ነበር:: ወደ በሩ ቀና ስትልና ሰው ሲገባ አንድ ሆነ:: መካከለኛ ቁመት አለው:: ባለ ዞማ ጸጉር የቀይ ዳማ መልከ መልካም የሚባል ሰው ነው:: ረዘም ያለ አረንጓዴ ፊልድ ጃኬት ለብሷል:: አንደ ገባ ቡና ቤቱን ጫፍ እስከ ጫፍ በዐይኑ ማማተር ያዘ:: ትሩፋት የምትፈልገው ሰው እሱ ለመሆኑ ገና ሲገባ ነበር እግርጠኛ የሆነችው:: ቢሆንም መጠንቀቅ ራሱ መጥቶ እስኪያናግራት ድረስ መጠበቅ እንዳለባት ተሰማት:: እንደ ጠበቀችው በዝግታ ወደሷ መጣና እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ

«ብዕሬ» አላት:: «ልቤ ነው» ብላ የተዘረጋ እጁን ጨበጠችው:: ለእሱም ሻይ እንዲመጣ አዘዘች:: ሻዩን እየጠጡ በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለባት ሲነግራት የተጨነቀ ይመስላል:: የመረጋጋት ሁኔታ ፈጽሞ አላየችበትም:: ምንም ይሁን ምን ግን ድርጅታዊ ስራዋን እንዴት መቀጠል እንዳለባት ሊነግራት ይገባል:: እሱ ግን የሥራ ምድቧን እስከታውቅ ድረስ ለጊዜው መታገስ እንደሚኖርባት እያግባባት ነው::

«በአሁኑ ሰዓት የኢሕአፓ የበላይ አመራሮች ችግር ውስጥ ናቸው:: ጉዳዩ በውይይት እርምት ተወስዶበት ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ መጠበቅ ግድ ነው::» ብሎ አዝማሚያው ጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳልሆነ ጠቆሚታል:: በአሁኑ ጊዜ የከተማውም ሆነ የገጠሩ የዕዝ ሰንሰለቶች እየተበጣጠሱ መገናኘት አዳጋች እየሆነ መምጣቱን ሲያስረዳት ፊቱ በሀዘን እየተኮማተረ ነበር:: ዝም ብላ በተሰበረ ልብ አዳመጠችው:: ለቀጣይ ግንኙነት ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ:: ወደ እናቷ ቤት ስትመለስ መንፈሷ ድቅቅ ብሎ ነበር:: በዚያ ላይ ፀሐይ ሙቀቷን ያለገደብ ለቃ የበለጠ አደከመቻት:: ለኮሳሳ ተጓዥ ከሦስት ሰዓት በላይ የማይወስደው የእግር መንገድ አራት ሰዓት ወሰዶ እንኳ ገና ከእናቷ ሰፈር አልደረሰችም::

******

ሰሞኑን ደግሞ ባህርዳር ወህኒ ቤት አጥር ጥሰው በጠፉት እሰረኞች ምክንያት ከዘመድ አዝማድ ጋር መገናኘት ተከልክሏ:: ይነበብ የትሩፋትና የልጁ ናፍቆት እንደ ውሃ ጥም እያንገበገበው ውስጡ ሰላም አጥቷል:: አድርጎት የማያውቀውን ሌሊት መቃዠት ሁሉ ጀምሯል:: የመተኛት ተራ አግኝቶ ፊቱን ለግድግዳው ሰጥቶ ጋደም ቢልም ሐሳብ ከውስጥ እየወዘወዘው ናላው ዞሮ መተኛት አቅቶታል:: ዐይኑ ፈጦ በሐሳብ ተዘፍቆ ሲባዝን ከጎኑ ያሉት የሁለት አስረኞች የጦፈ ክርክር ሳበውና ጆሮ ሰጥቶ ማዳመጥ ቀጠለ::

«እነዚህ የተረገሙ ራስ ወዳድ እሰረኞች ባያመልጡ ኖሮ ወጥተን የፀሐይን ብርሃን እንኳ እናገኝ ነበር:: አምልጠው ሳያመልጡ እንደ ሰርዲን ታጭቀን እንድንውል ፈረዱብን::

እግዜር ይይላቸውና:: በእንዱ ገበሬ ማኅበር ታጣቂ ተይዘው የመጡ ጊዜ ግን እነሱን እያድርገኝ!» አለ አንደኛው እስራኛ::

«ጀግኖች ናቸው አባከህ! በወታደር መልካም ፈቃድ ሳይሆን ፀሐይን እንደ ልብ ሊሞቋት--ሊያደንቋት ሲመኙስ:: ይልቅስ ነፃነት የምትናፍቅ ስስ ነፍሳቸውን አድንቅ!» አለው ሁለተኛው ተናጋሪ እስረኛ ፈገግ ብሎ እየተመለከተው::

«የማይረቡ ጀብደኞች ናቸው እባከህ! ዝም ብለህ የማይገባቸውን አድናቆት አትቸራቸው:: በእነሱ የተነሳ እኛ እሳር መከራችን ማየታችንን አጥተውት አይደለም:: ሆን ብለው ነው ስቃያችንን ያበዙት:: ሰልፈሾች ናቸው እሺ! ሰልፈሾች!»

«የምርህን ነው ግን? የግድ እኛን መሆን አለባቸው እያልክ ነው? የምትገርም ነህ ጃል! ለምን እነሱን ትኮንናለህ? በሌሎቻችን ውስጥ የሌለ ቆራጥነት በእነሱ ነብስ ውስጥ ስትገኝስ:: ይልቁንስ መውቀስ ያለብህ የራስህን ፍርሀት ነው:: እኛ ነን ልብ የሌለን ፈሪ እስረኞች!--ህሞት ያልፈጠረብን ልፍስፍስ ፍጥረቶች!— እንደ ደነገጥን ውለን እንደ ባነን መሽቶ የሚነጋልን ቡከኖች!- የወታደር ጥላ ባየን ቁጥር የምንደነብር ደንባሮች! መኖር እንደዚህ ከሆነ ባፍጢሙ ይደፋ! ነፃነትን ለሰዓታት አይቶ አይቀሬውን ሞት መጎንጨት ጽድቅ ነው:: እየህ! ጀግኖቹ የመረጡት ይህን ነው:: እኛ የፈራነውን! እኛ ያልሆነውን!»

«ቀን እስኪያልፍ እንገትን ድፍቶ ማሳለፍ ብልህነት ነው:: እጉል ድፍረት ድንቁርና ነው---ድንቁርና! የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ እንጂ ሲሸሹ ቢገኙ ኖሮ ዐይናቸው እያየ ነበር ቆዳቸውን የሚገፉት::»

«እየህ ወንድሜ! ከእኛ ከፈሪዎች ልዩ የሚያደርጋቸው እኮ ታድያ ይሄ ነው:: ለነፃነት ሲሉ የመጣውን ችግርና ስቃይ ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸው:: የሚገርመኝ ፈሪዎች ስንባል ራሳችንን ማጽናኛ-- ፍርሀታችንን መደበቂያ ሰበብ አለማጣታችን ነው:: 'ቀን እስኪያልፍ' ትላለህ እንዴ! ያ ቀን መቼ ነው የሚያልፈው? የዛሬ ወር?-- የዛሬ ዓመት?-- የዛሬ እስር ዓመት? ምናልባት የዛሬ ሃያና እምሳ ዓመት....? መቼ ነው የሚያልፈው? እንዴት ነው የሚያልፈው? ያ ቀን ከመምጣቱ በፊት እኛ በፍርሀት እየራድን ንጹህ እየር እየተመኘን--ፀሀይ ጠግበን መሞቅ እየፈለግን እዚህ ተቆራምደን እንደ ታሰርን ማለፋችንስ አይታይህም!?» እለው በትዝብት እያስተዋለው::

«'መቃብር በር የለውም:: እስር ቤት ግን በር አለው..' የሚል ከእንድ ልብወለድ መጽሐፍ ላይ ማንበቤ ትዝ ይለኛል:: እትሞኝ በሕይወት ካለን እንድ ቀን ከዚህ ሲኦል ከሆነ እስር ቤት ውስጥ መውጣታችን አይቀርም::»

«እኮ መቼ!? እታውቀውም-- እላውቀውም:: ቆራጦቹ ያ ያልታወቀውን ቀን ባልታወቀ ተስፋ መጠበቅ አልፈለጉም:: ለዚያውም ያ ያልታወቀው ቀን ይዞት የሚመጣው

የጓጓንለትን መፈታት ሳይሆን የፈራነውን ሞት ሊሆን እንደማይችል ማናችንም እናውቅም:: እነዚህ ልጆች በድፍረት በስንት ጠባቂ ጦር የተከበበን እጥር ጥሰው የነፃነታቸውን ቀን አቀረቡ:: እየህ ማድነቅ ያለብህ ለነፃነታቸው የሰጡትን ይህን ትልቅ መስዋዕትነት ነው! ለነፃነታቸው ሊከፍሉት የተነሱለትን ዋጋ ነው!» እለ ሁለተኛው ተናጋሪ እሰረኛ አድናቆቱን ሳይደብቅ::

«የእነሱ መጥፋት ይኸው ከዘመዶቻችን ጋር እንኳ እንዳንገናኝ አድርጎናል:: የተረገሙ እርጉሞች! የት እንዳልደረሱ ነው? ይሄኔ እዚሁ ባህርዳር ከተማ በእንዱ ቤት ውስጥ ዘግተው ተቀምጠው ይሆናል:: እነሱም ከእኛ አይሻሉ ይሆናል:: እንደውም ይበልጥ ስጋት ላይ ሊሆኑ ይችላሉ:: ተያዝኩ እልተያዝኩ እያሉ ነብሳቸው እየባነነች ይሆናል:: እነዚህ ጦሰኞች!»

«ኧረ ቀስ በል በእናትህ! ምን ያናዳድሀል? ከተናደድክም መናደድ ያለብህ በገዛ ፍርሀትህ ነው:: ማወቅ ያለብህ የሚያደርጉትን ሁሉ የሚፈጽሙት በራሳቸው ፍላጎትና እካሄድ ነው:: ይህን ጊዜ በር ተዘግቶባቸውም ቢሆን እንኳ በሌላ ሰው እጅ አልተከረቸመባቸውም:: በሩን በራሳቸው ላይ የዘጉት ራሳቸው ናቸው:: የእኛና የእነሱ ልዩነት እዚህ ላይ ነው:: ሰው ሆነህ ሳለ በሌላ ሰው ይሁንታ ሥር መዋል:: ታዲያ ከዚህ የከፋ ውርደት አለ? ከዚህ የከፋ የቁም ሞት አለ? ይበልጥ የሚያናድደውና የሚገርመው ደግሞ ጀግኖቹ ባመለጡ--- እየተቀጣን ያለነው እኛ ፈሪዎቹ ነን:: ስለዚህ መኮነን ያለብህ ያመለጡትን ጀግና ልጆች ሳይሆን የገዛ ፍርሃትህን ነው ወዳጄ:: ሳታጠፋ የሚያስቀጣህን! ሳትሞት የገደለህን» አለ ሁለተኛው ተናጋሪ እስረኛ የምጸት ሳቅ እየሳቀ:: እስረኞቹ ይህን እየተነጋገሩ ለሽንት እንዲወጡ ታዘዙ::

«እየህ ውርደት ማለት ይሄ ነው:: ሽንትህን እንኳ የምትሸናው በሌላ ሰው ይሁንታ ነው:: ፊት ለፊትህ መሳሪያ ተደግኖ» አለው ሁለተኛው ተናጋሪ:: ያኛው እስረኛ ምንም ሳይመልስለት ገላምጦት ወደበሩ ተራመደ:: ከሽንት ቤት መልስ ወደ ከፍላቸው ገቡ:: ረጅሙን ሌሊት እያሰቡ የነገዋን ንጋት እየናፈቁ:: ይነበብ የሁለተኛው እስረኛ ንግግር ከልቡ ገብቷል:: ከሽንት ቤት መልስ ወደ መኝታ ቦታው ሲሄድ ሁሉ የሚያስበው የሁለቱን ክርክር ነበር::

«እውነትም የሰው ልጅ ከሞት በፊት ደጋግሞ የሚገድለው ፍርሀት ነው:: ለሰው ልጅ ከፍርሀት የከፋ ምንም ጠላት የለውም» አለ ለራሱ:: ለጊዜውም ቢሆን ስለትሩፋትና ስለልጁ ማሰቡን ትቶ::

እነዚያ እጥር ጥሰው የጠፉ እስረኞች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሌሉበት ሞት ተፈረደባቸው:: በተገኙበት እንዲገደሉ ፎቷቸው ሁሉ ተባዝቶ በየቦታተው ተበተነ:: በየገበሬ ማህበሩ ሳይቀር ማደኛ ወጥቶ ቢፈለጉም ደብዛቸው ጠፍቶ ቀረ:: ቀስ በቀስ

መንግሥትም ተስፋ ቆርጦ እስሳው ቀዘቀዘ:: ከወራት በኋላ ጨርሶ እየተረሳ ሄደ:: እነዚህ ሦስት ቆራጥ የባህርዳር እስረኞች በዚያ ሁሉ ጥበቃ ስር ያለን እስርቤት ሰብሮ መጥፋት የአንድ ሰሞን የጀግንነት ወሬ ሆኖ ከረመ::

******

በጠፋት እስረኞች ምክንያት ታግዶ የነበረው የቤተሰብ ግንኙነት እንደ ገና ተፈቀደ:: እለተ-እሁድ የእስረኛ ቤተሰብ ሁሉ ቤት ያፈራውን ስንቅ ቋጥሮ የወህኒ ቤቱን አካባቢ በጧት ገበያ አስመስሎታል:: ከመለያ ግንዱ አጠገብ ቦታ ያላገኘው አንዱ ባንዱ ላይ እየተንጠራራ መንገድ መንገዱን ዐይኑን ሳያራግብ ይመለከታል::

ትሩፋት እሁድ እሁድ ባህርዳር ወህኒ ቤት መገኘት ሌላው መደበኛ ሥራዋ ነው:: ዛሬም ይነበብን በሩቅ ነበር ያየችው:: ስለከሳ ረጅም ቁመቱ የበለጠ ረዝሞ ታያት:: ከመለያ ግንዱ ደርሶ እብሮት የቆመውን ሰው ስታይ ግን ያየችውን ማመን አቃታት:: ሁለቱንም ዐይኖቿን ጨፍና አሻሽታ እንደገና ገለጠቻቸው:: ያየችው ግን እውነት ነው:: ፍቅሩ ጠና!! ከስቷል--ጸጉሩ አድጎ አጭር ቁመቱን ሊውጠው ደርሷል:: የፂሙ አድገት አዲስ ባህታዊ አስመስሎታል:: ያነከሳል:: ቶሎ ግንዱን ባይዝ ኑሮ ይወድቅ ነበር:: ትሩፋት አፏ ተከፍቶ ዐይኗ ፈጦ ባለችበት ድርቅ ብላ ቀረች:: በዘንቢል ይዛው የነበረው ስንቅና ቅያሬ ልብስ እጇ ላይ ተንሸራቶ ሲወድቅ እንኳ አልሰማችውም::

«ስንቅ የምታስመረምሩ ቤተሰቦች ሳህኖቻችሁን ወረፋ አስይዙ!» የሚለው የዘብ ወታደሩ ኃይለኛ ትዕዛዛዊ ጩኸት ነበር ከድንጋጤዋ አባኖ የመለሳት:: ከእጇ ተንሸራቶ የወደቀውን ዘንቢል በዳበሳ እንስታ ስንቅ የያዘ ሳህኑን ስታወጣ ሁሉ ገና ራሷን በሚገባ አልገዛችም ነበር:: ከዘንቢሉ ውስጥ ሳህኑን ስታወጣው የተቋጠረበት ጨርቅ በወጥ ርሷል:: እስሩን ፈትታ ሳህኑን አስተካከላ ከደነች:: እላዩ ላይ የተደፋውን ወጥ አስራበት በነበረው ጨርቅ ጠራርጋ ከተደረደሩት ሳህኖች ጋር ወስዳ ወረፋ ስታስይዝ ሁሉ እጇ እየተንቀጠቀጠ ነበር:: የሆነውን ሁሉ የምታደርገው በደመነፍስ ነው:: ከወደቀችበት ከፍተኛ ድንጋጤ ነፍሷ ገና አልተመለሰችም::

በግንድ አጥር ተለይተው የቆሙት እስረኛና ጠያቂ ቤተሰቦች ሰላምታ ይለዋወጣሉ:: ናፍቆታቸውን-- ፍቅራቸውን-- ብሶታቸውን-- ችግሮቻቸውን ይገላለጻሉ:: ሁሉም የየራሱን ስለሚጮህ መደማመጥ ያለ አይመስልም:: ዳር ሆኖ ለሚያዳምጠው ሰው ገበያ መሀል ያለ ይመስለዋል:: ለስንት ደቂቃ ያህል ደንዝዛ እንደ ቆየች አላወቀችውም:: ለመናገር ፈልጋ ቃላቶች ከአፏ አልወጣልሽ አሏት :: እንደ ምንም የሞት ሞቷን ታግላ

«ፍቅሩ በየት በየት ዞረህ እዚህ ተገኘህ!?» አለችው:: ድምጿ ከሩ--ቅ የሚመጣ ይመስል ነበር:: ከግንዱ በላይ እጇን ለሰላምታ ልካ ስትጨብጠው ሁሉ እሷ ራሷ የምታደርገው

አልመሰላትም:: በስመመን ዓለም ውስጥ ነበረች:: እየሆነ ያለው ሁሉ በህልም ዓለም እንጂ በውኑ ዓለም ለዚያውም እዚህ ባህርዳር ወህኒ ቤት ግቢ ውስጥ የሆነ በጭራሽ አልመሰላትም::

«እሱን በድል ስንገናኝ በሰፊው ሌላ ጊዜ አወራልሻለሁ:: እንዲህ በአጭር ጊዜ ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም:: ረጅም ታሪክ አለው» አላት ከግንዱ በላይ የጨበጠውን እጇን እንደ ያዘና በናፍቆት ትኩር ብሎ ዐይን ዐይኗን እየተመለከተ:: ቀስ እያለች ወደ ልቦናዋ መመለስ ጀመረች:: ከባዱ ድንጋጤ እየለቀቃት ሰውነቷ እየተረጋጋ መጣ:: ከፍቅሩ ጋር ስለ ደህንነታቸው ሲጠያየቁ ይነበብ በዝምታ እያዳመጣቸው ነበር::

«ይነበብ አንተስ እንዴት ነህ? የከሳህ ትመስላለህ» አለች ዐይኗን ከፍቅሩ አሸሽታ ወደ ይነብበ እየመለሰች:: ድምጿ አሁንም ድክም እንዳለ ነው::

«ከስቻለሁ እንጂ? መስሎሽ ነው እንጂ እኔስ ቁጭ ብዬ ሳልሠራ እየተቀለብኩ ጠብድያለሁ:: አልከሳሁም እንጂ ብከሳም አያስገርምም:: የቴዎድሮስ ናፍቆት ከእንቺ ላይ ታክሎ ከፍላችን ውስጥ እንደሚርመሰመሰው ትኋን ሲበጠቡጠኝ እያደረ ምን እንድሆን ጠብቀሽ ነበር?» አላት ዓይኑን በዘዝ አድርጎ በስስት እየተመለከታት «ይልቁንስ አንቺ ከስተሻል--ጠቁረሻል::»

«ምን ይደረግ? በየቀኑ የሚያሳስበን ነገር እየበዛ መጥቷል» አለችው ከድርጅቷ ጋር ያላት ግንኙነት እንዲህ እንደ ዋዛ ተቋርጦ መቅረቱ በእጅጉ እየቆጫት::

«ያ ተጎዳ ያልኩሽ ጓዳችን ይኸ ነው ትሩፌ:: በኋላ ስንጨዋወት አዲስ ዘመን አብራችሁ የተማራችሁ መሆኑንና እንደምትተዋወቁ ነገረኝ:: እየውልሽ እንግዲህ የአጋጣሚ ነገር» አላት::

«እውነት ነው አብረን ተምረናል» አለችው በአጭሩ:: «በእኔና በፍቅሩ መካከል ስንት የልጅነት ታሪክ እንደ አለፈ ብነግርህና ብታውቅ ምን ይሰማህ ይሆን?» አለች በውስጧ:: «ጤንነትህ እንዴት ነው? የኛ ጤንነት እንኳ ይህን ያህል አስተማማኝ አልሆነም» አለች ትከዝ ብላ:: ፍቅሩ አሁንም ዐይኑን ከላዩዋ ላይ አልነቀለም::

«ቴዎድሮስ አደገ? ጠነከረ? ወፍራም ነው ቀጭን? ትሩፌ በሞቴ ንገሪኝ ማንን ይመስላል? ሳስበዉ-- ሳስበዉ እኔን የሚመስል ይመስለኛል» ጥያቄ በጥያቄ ላይ አደራረበው::

«አባቴን አሳዩኝ እያለ እያስቸገረ ነው» ብላ ቀለደችበትና «ይልቅስ የማስጠንቀቂያ ፊሽካ ከመነፋቱ በፊት ቁም ነገር---ቁም ነገሩን እናውራ:: ድርቁ በረታ፤ የዘመዶቻችን አዝመራ በዋግ እየተመታ ነው:: ከብቶችም በድርቁ ምክንያት ከቦታ ቦታ እየተንከራተቱ ይገኛሉ:: ከተማም ለሽያጭ እየገቡ ነው:: በበለሳና በተቀሩት ቆላማ ቦታዎች ሁሉ የሚያስፈራ ድርቅ

ገብቷል» አለችው ከፍት እንደ አሳት፡፡ ይነበብ ምን ልትነግረው እንደ ፈለገች ገብቶታል፡፡ ኢሕአፓ በራሷ የውስጥ ችግር ተመትታ አባላቱ በምህረት ስም እየገቡ ለመንግሥት እጅ እየሰጡ መሆናቸውንና መዋቅሩ ከፉኛ እየፈራረሰ መሆኑን ነው የገለጸችለት፡፡ ሰሞኑን አሰረኛው ሁሉ በቁጭትና በንዴት የሚያወራው ይህንኑ ነበር፡፡

«ተስፋ መቁረጥ እያስፈልግም፡፡ ድርቁ ለጊዜው ነው ዘመዶቻችን የሚጎዳቸው፡፡ ሁልጊዜ ዝናብ አይሆንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድርቅ እንደሚከሰት መታወቅ አለበት፡፡ ተስፋ እናድርግ ይዘንባል» ፊሽካ ተነፋ፡፡ እስረኛው ሁሉ ወደ ክፍሉ ተመሰሰ፡፡ የቀሩት ይነበብና ፍቅሩ ብቻ ነበሩ፡፡ በወታደር እየተገፈታተሩ ሲሄዱ ሰጥቂት ጊዜ ባስችበት ቆማ እየቻቸው፡፡ ፊቷን መልሳ ወደ አረፈችበት የዘመድ ቤት ስትሄድ ሁሉ የፍቅሩና የይነበብ መገናኘት ኢጋጣሚው ድንቅ! ግርም! እያላት ነበር፡፡

******

«አበራሽ ልጅ ለመውሰድ ስትይ እንኳን ምን እለበት በጊዜ ብታገቢ እንዲህ ልጅ እንደ ሆኑና እንደ አማሩ ዘላለም መኖር ይገኝ መስሎሻል» አሰች ትሩፋት፡፡ ስትበር ወደ ጎንደር የመጣችው የአበራሽ ትዳር እሰመያዝ እስጨንቋት አይደለም፡፡ ሌላ የምታማክራት ብርቱ ጉዳይ ኖሯት ነው፡፡ እብዮት የቆዩ ጓደኝነትን ብቻ ሳይሆን የቅርብ ዝምድናን ሁሉ እርመጥምጦ በልቷል፡፡ እርስ በእርስ በጥርጣሬ መተያየት ከተጀመረ ውሎ አድሯል፡፡ ባልና ሚስት አለያይቷል፡፡ እህትና ወንድም---አባትና ልጅ---እናትና ልጅ ሳይቀር ጎራ አለያይቶ አፋጅቷል፡፡ ትሩፋት አበራሽ ሰደርግ መንግሥት ያላት አቋም ጠንካራ እንደ ሆነ አሳምራ ታውቃለች፡፡ እሷንም ቢሆን አታምናትም፡፡ ይነበብ በፀረ አብዮት ካምፕ ተሰልፎ አብዮቱን የወጋ ለመሆኑ አምኖ ምህረት መጠየቁ ለአበራሽ ጥርጣሬ አንድ ማጠናከሪያ ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ ትሩፋት እንድ ነገር ቸግሯታል፡፡ ይህን ችግሯን ከአበራሽ የቀረበ ልታማክረው የምትችለው የመንግሥት ሰው እላገኘችም፡፡ ዋናውን ቁምነገር ትታ ዳር ድር የምትሰው ለወሬ ማሟሟቂያ መሆኑ ነው፡፡ አበራሽ ደግሞ ጥሎባት ልጅና ባል ብሎ ነገር አይጥማትም፡፡ ትሩፋት ደግሞ የማትወደውን ነገር አንስታ ውጥር እድርጋ ይዛታለች፡፡

«እውነት ትሩፌ አብዮት በአገሪቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በአንቺም ላይ ነው የተካሄደው፡፡ ወይ ዘመን! ጉድ እኮ ነው! ጉድ ተወርቶ አያልቅም፡፡ ታድያ እናትዬ አግብተሽ ልጅ መውሰድሽ ካልቀረ ፍቅሩ ላይ ምነው እንዲያ ጨከንሽበት? ዳግም እንዳይነሳ እድርገሽ በፍቅር ዱላ ተቀጥቅጦ እንዲቀበር ፈረድሽበት፡፡ ምስኪን ፍቅሩ! ከልቤ ነው የሚያሳዝነኝ፡፡ በዓለም ላይ በሕይወት እየኖረ የአንቺ ነገር እስችሎት ይቀመጣል ብዬ አላስብም» አሰች አበራሽ፡፡

«ከእንግዲህ የእኔና የፍቅሩ ጉዳይ ፋይሉ ተዘግቷል፡፡ ይልቅ 'አምና ብለምንሽ ልጅ ነው ብለሽኛል፣ ዘንድሮ ተራዬን እርጅተሽብኛል' እንዳይሆንብሽ ለራስሽ እስቢ፡፡ ጊዜሽ ካለፈ ደግሞ ብትሳይም መውሰድ ላይገኝ ይችላል፡፡ ከልቤ ነው አበራሽ፡፡» ፍቅሩን ባህርዳር

ያገኘችው መሆኑን አሁን መንገር አልፈለገችም፡፡ የበለጠ ነገር ማራዘም መስሎ ታይቷታል፡፡

«የጎንደር ድሀ እናት በድባብ ትሂድ፡፡ ሳይፈልጉ የተፈለፈሉ ሕፃናት በየደጀ ሰላሙና በየጎዳናው እየተንከላወሱ ምድሪቱን ሞልተዋታል፡፡ ደስ ያለኝን እንዱን መርጬ በጉዲፈቻ ባሳድግ በሰማይ ቤትም ጽድቅን ሳያጎናጽፈኝ አይቀርም፡፡ በምድር ደግሞ አንድ ጎስቋላ ነፍስ በመታደጌ የሕሊና እርካታ አተርፍበታለሁ፡፡ አባከሽን ተይኝ ትሩፋት አታስቸግሪኝ፡፡ እኔ ተጨማሪ ሐሳብ ፈጥሬ መንገላታት አልፈልግም፡፡ ምን አሳጣኝ ብዬ? ለዚያውም እንችን እያየሁ!» እለች እበራሽ፡፡

አበራሽ የልጅነት ውበቷ እንደ ነበር አለ፡፡ ቼኮሌት የሚመስለው ገጽታዋ ገና ፍልቅልቅ እንዳለ ነው፡፡ ትላልቅ ዐይኗ የዘመኑ ጭንቀትና ትካዜ እይነበብባቸውም--- አልደበዘዙም፡፡ እንደ ፓውዛ ከሩቅ ያበራሉ፡፡

«ይልቅስ ጎንደር ድረስ ሲያከንፍ ያመጣሽን ዋና ጉዳይ ምንድን ነው? በእሱ ላይ ብንወያይ ይሻላል፡፡ ምን ጥብ--ቅ ያለ ጉዳይ ቢገጥምሽ ነው ግን እርጥብ እራስ ልጅ አስትቶ ያስመጣሽ?» እስች አበራሽ እያዘነችላት፡፡

«ምን አባከሽ አበራሽ እስቸጋሪ ዘመን ላይ ነው ይለው» ብላ ዝም አለች ትሩፋት፡፡ እንዴት እንደምትጀምርላት ጨንቋት፡፡

«እስቸጋሪ የሰውጥ ዘመን ላይ መሆናችን የገባሽ እሁን ነው? ቆየ እኮ!»

«ይነበብ ባህርዳር ወህኒ ቤት መታሰሩን ታውቂያለሽ እይደል?» አለች ትሩፋት ስትፈራ ስትቸር፡፡

«በፀረ-አብዮተኛነት» አለች አበራሽ፡፡

«እሱ ምን ጥያቄ አለው፡፡ ምህረት ጠይቆ አይደል እጁን የሰጠው፡፡»

«ትሩፋት ዛሬም ጓደኛዬ ነሽ፡፡ የተሰማኝን አልደብቅሽም፡፡ ይነበብ ጸረ አብዮተኛ ይሆናል ብዬ የጠረጠርኩት የሰርጋችሁ ጊዜ ነበር፡፡ ጥርጣሬዬ ደግሞ አንቺንም ያካትታል፡፡ ለዚህም በቂ ምክንያት አለኝ ብዬ አምናለሁ፡፡ ያኔ የሰርጋችሁ እለት ዘመድ አዝማድ ሁሉ እኔን ጨምሮ ቅዳሜ እለት መጥተን ስናድር-- የተገላቢጦሽ ሙሽራይቱ ግን በእለቱ እለት እንኳ በሰዓቱ አልተገኘሽም፡፡ ወንዱ ሙሽራም ቢሆን እርፍዶ ነበር የመጣው፡፡» ትንሽ ፈገግ አለችና «የሰርግሽን ቀን ፈጽሞ አልረሳትም፡፡ ዘመድ አዝማድሽ ሁሉ ቀረች---ኧረ ቀረች! እያለ በጭንቀት ተውጦ እኛ ሚዜዎችሽ ግን ሙሽራዋ በሌለሽበት አገር ምድሩን በዘፈን ቀውጢ አድርገነው ነበር» አለች አበራሽ እየሳቀች፡፡

«ጉረኛ! ታድያ አብሮ አደግ ጓደኞቼ በዚያ ላይ ሚዜዎቼ ሆናችሁ ለሰርጌ ቀን ካልዘፈናችሁ ለመቼ ልትዘፍኑልኝ ነበር?» አለች ትሩፋት ነገሩን ለማለሳለስ አብራት እየሳቀች፡፡

«አንቺ በጊዜውና በሰዓቱ ባትገኝም አላሳፈርንሽም፡፡ በርግጥ ኢሕአፓ አባሎቿ ከሚከፍሉት መስዋእትነት አንጻር ሲታይ ይኸ በጣም ትንሹ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ይሁንና በወቅቱ ሰርጉ ላይ የተፈጠረውን ሁኔታ አስታኮ ወዲያውኑ ሁላችሁንም ማሳፈስ ይቻል ነበር» አለች አበራሽ፡፡ የትሩፋትን ስሜት ለመመርመር እየሞከረች፡፡

«ሆኖም ግን ለአብዮታችን ከሚለጠው ጥቅም አኳያ ሰመዘነው የሰርጉ ታዳሚና የአካባቢው ሕዝብ በሙሉ በመንግሥት ላይ የሚፈጥረው ጥላቻ የበለጠ ሊሆን እንደሚችል ተሰማኝ፡፡ ፖሊስ የኃይል እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ጣልቃ ገባሁ፡፡ አቅሜ የቻለውን ሁሉ አደረኩ፡፡ ሰርጋችሁም በሰላም ተከናወነ፡፡ ሁለተኛው ምክንያቴ ደግሞ ለቆየው ጓደኝነታችን ስል የከፈልኩት መስዋእትነት መሆኑ ነው» ትሩፋት ዝም ብላ አዳመጠቻት፡፡ አራስ ልጇን ጥላ የመጣችው አንዳንድ ነገሮችን ልታማክራት ነበር፡፡ የአበራሽ ሁኔታ ግን አስፈራት፡፡ ባልመጣ ይሻለን ነበር ግን መጥቻለው፡፡ የጉዳዩን ጫፍ አለጨብጫታለው ጨርሳ ሳትሰማኝ አለቃትም አለች ለራሷ፡፡

«ባለፈ ታሪክ ላይ አሁን መወቃቀሱ ምን ይጠቅማል አበራሽ? እሱን በቃ እርሺው» አለች ትሩፋት ተለላችታ፡፡

«ትክክል ብለሻል፡፡ ያለፈው ታሪክ ሆኖ አልፏል፡፡ የአንቺን አቋም በእርግጠኝነት ባልናገርም የባለቤትሽ አቋም ታውቋል፡፡ ፀረ-አብዮተኛነቱን አምኖ በምህረት እጁን ለመንግሥት ሰጥቷል፡፡ አመጣጥሽ ይህንን በተመለከተ ከሆነ ግልጽ ሆነሽ እንነጋገር» አለች አበራሽ፡፡

«የይነበብን ሁኔታ ካወቅሽ ግልጽ እንድሆን የምትፈልጊው የእኔን አቋም ከሆነ ከአሁን በፊት ነግሬሻለሁ፡፡ የተሰጠኝን ሥራዬን ሰርቼ ከመኖር በስተቀር ዛሬም-- ነገም-- ወደፊትም የተለየ ዓላማ አይኖረኝም፡፡ በቃ! ይኸው ነው» አለች ትሩፋት ኮስተር ብላ፡፡ እናትና ልጅን በለያየ በዚህ የአብዮት ወቅት የድሮ ጓደኝነታቸው እንደ ነበር ይቆያል ብላ አምና ልታማክራት በመምጣቷ ተቆጨች፡፡ ራሷን እንደ ቂል ቆጠረች፡፡

«ግድ የለም ውዷ ጓደኛዬ አትኮሳተሪ! እንደ ባለቤትሽ ያንችም አቋም አያደር ይለያል፡፡ አራስ ልጅ ትተሽ ስትበሪ የመጣሽው ምን ልታማክሪኝ ፈልገሽ ነው?»

«እንደ ፖሊስ ለምርመራ ስታቀርቢኝ ፈራሁሽ እኮ አበራሽ!»

«በጥንቱ ጓደኝነታችን ስም አምልልሻለሁ፡፡ መቼም ቢሆን ከፉሽን አልሻም» አለች አበራሽ ከልቧ

ያልተቋጨ ጉዞ

«ይገባኛል አበራሽ፡፡ አንቺም ትረጅኛለሽ ብዬ አስባለሁ» አለች ትሩፋት፡፡

«'ስለማይጥማቸው የፍቅር ድግሱ!» ስትል አበራሽ

«ውሾች ብቻ ናቸው የሚነካከሱ፡፡'» አለች ትሩፋት--- ተሳሳቁ፡፡

«እሺ ቀጥይ ወደ ዋናው ፍሬ ነገር እንግባ፡፡»

«ይነበብ እጁን የሰጠው በምህረት አዋጁ መሰረት ነው፡፡ የአዋጁ ተፈጻሚነት በራዲዮና በቴሌቪዥን እንደሚነገረው ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ እንደማንኛውም የፖለቲካ እስረኛ ታስሮ እሳር መከራውን እያየ ነው፡፡ በምህረት መግባቱ አዋጁ ሊያስገኝለት የሚችለው ጥቅም እንዳለ ላማከርሽ ነበር አመጣጤ አበራሽ፡፡ እኔ ብቻዬን ወስኜ ከመንቀሳቀሴ በፊት ከሕግ አንጻር ያለውን ጠቀሜታ እንድታስረጅኝ ፈልጌ ነበር፡፡ ይህን ስልሽ ግን ለእኔ ብለሽ የተለየ ውለታ እንድትውይልኝ አይደለም፡፡ አንቺንም ካልሆነ ጥርጣሬ ውስጥ ልከትሽ አልፈልግም፡፡ የምህረት አዋጁን ጥቅምና አካሄዱን ብቻ ነው ማወቅ የፈለጉት» አለች ትፋት፡፡

«እንደ እውነቱ ከሆነ ይነበብ ምህረት የጠየቀው ከልቡ ነው ብዬ አላምንም፡፡ ይህ ጥርጣሬዬ እንዳለ ሆኖ የበደለውን አብዮት ለመካስ ዝግጁ ከሆነ የቻልኩትን ሁሉ እሞክራለሁ፡፡ ትሩፋት እኔ መቼም ቢሆን ጓደኛሽ ነኝ፡፡ የአመለካከት ልዩነት እንዳለን አውቃለሁ፡፡ እውነታው ሲገባሽና ሲገለጽልሽ በሂደት አንድ ቀን በአንድ መስመር ላይ መሰለፋችን አይቀርም፡፡ ከአብዮታችን ጎን እስከትሰለፊ ድረስ ግን ልዩነታችን የቆየ ጓደኝነታችንን ጨርሶ ይንደዋል ብዬ አላስብም፡፡»

«ይነበብ በገጠመው ችግር የመንግስት አዋጅ ምን የመስላል? ተፈጻሚነቱ እንዴት ነው? የሚለውን ለማወቅ እንጂ አንቺን በጓደኝነት ስም ላስቸግርሽ ፈጽሞ አልፈልግም፡፡ የወቅቱ ፖለቲካ ሁኔታ ለጓደኝነት አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል፡፡ የማትችይው ነገር ከሆነ ይህን ሳታደርግልኝ ብዬ ቅሬታ አይሰማኝም፡፡ ጓደኝነታችን መልኩን ሳይቀይር እንደ ነበረ ይቀጥላል» አለች ትሩፋት፡፡

«ስለ አሰብሽልኝ አመሰግናለሁ የጥንት-- የጠዋቷ ጓደኛዬ፡፡ ለማንኛውም ውዱ ባለቤትሽ ፀረ-አብዮተኛ ሆኖ ለመሸፈት ሙከራ አድርጎ ነበር፡፡ ሆኖም ትክክል ያለመሆኑን አውቆ ተፀፅቶ ምህረት ጠይቆ ገብቷል፡፡ የሚታመን መሰሎ ካልታያቸው የከፋ እርምጃ ከመውሰድ አይመለሱም፡፡ በእርግጠኝነት እንዲህ ነው ብሎ መናገር ያስቸግራል፡፡»

«ምህረት መጠየቁና የምህረት አዋጁ ምንም አይጠቅመውም እያልሽኝ ነው አበራሽ?»

«እንደ እሱ ማለቴ እንኳን አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ይህን አይለቁትም ከፍተኛ ወንጀል በአብዮቱ ላይ የፈፀመ ነው ያልሽውን ፀረ-አብዮተኛ በነፃ ሲያሰናብቱት ታያለሽ። በምህረት ለቀነዋል ያሉትን ደግሞ አሰረው አሰቃይተው እርምጃ ሊወስዱበት ይገኛሉ። እንዳልሽው የፖለቲካው ነገር አስቸጋሪ ሆኗል። እንዲህ ይሆናል ብሎ መገመት ይከብዳል።»

«ለባህርዳር አውራጃ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በምህረት አዋጁ መሰረት መፈታት የሚገባው መሆኑን ማመልከቻ ጽፌ ባቀርብ ምን ይመስልሻል?»

«ትሩፋት ቀስ በይ። በችኮላ አንድ ነገር ከማድረግሽ በፊት ግራና ቀኙን ማስተዋል ይኖርብሻል። ሥራው ሁሉ የሚሰራው በኮሚቴ ነው። ዝም ብለሽ ሄደሽ ለአስተዳዳሪው ብታመለክች አሰተዳዳሪው እንደ ግለ-ሰብ ቀና አመለካከት ቢኖረው እንኳ ብቻውን ምንም የሚፈጽመው ነገር አይኖርም። ጉዳዩን ለኮሚቴ ያቀርበዋል። ከዚያ በኋላ ውሳኔው እንደ ኮሚቴው አመለካከት ይሆናል» አለች አበራሽ።

«ታድያ ምን ይሻለኛል አበራሽ? ዝም ብለሽ እጅሽን አጣጥፈሽ ተቀመጭ ነው የምትይኝ? ምንም ሙከራ ሳላደርግ አንድ ነገር የሆነ እንደሆነ ኋላ ጸጸቱን የምችለው አይሆንም» አለች ትሩፋት ጭንቅ እያላት ።

«በቅድሚያ ባህርዳር አውራጃ አስተዳደር ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች እናፈላልግ። ሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ውስጥ ከሚሠሩ ጓዶች ጋር እስከመካከር ድረስ ጊዜ ስጭኝ» አለች አበራሽ። ባሕርዳር ውስጥ ከምታውቃቸው ሰዎች ደህና ተሰሚነት አላቸው የምትላቸውን ባለስልጣናት በልቧ እያሰበች።

«ጊዜ በሄደ ቁጥር አንድ ነገር እንዳያደርጉት ብዬ ፈራሁ» አለች ትሩፋት ስጋት አፈቷ ላይ እየተነበበ።

«ታድያ በችኮላስ ምን ማድረግ ትችያለሽ? ኮሚቴው ውስጥ የሚሰሩ ጥቂት የምናውቃቸው ሰዎችን ማፈላለግና መያዝ ይኖርብናል። ያለ ሰው ማመልከቻ ብቻውን ወስደሽ ለአስተዳዳሪው ብትሰጭ ይልቁንም ልዩ ትኩረት እንዲያደርጉበት መጋበዝ ነው የሚሆነው። ከትትሉ ደግሞ ባንቺም ላይ ሊያነጣጥር ይችላል። ታስረሽ የተፈታሽ መሆንሽን አትርሺ። ይህንን ካወቁ ደግሞ ነገሩ ይብልጥ ተወሳሰበ ማለት ነው። ጥሩ ተሰሚነት ያለው ሁነኛ ሰው እስከምናመቻች ድረስ እርፈሽ መቀመጡና ማድፈጡ የሚሻል ይመስለኛል» አለች አበራሽ። በዚሁ ሀሳብ ተሰማምተው ትሩፋት ለመሄድ ተነሳች።

ትሩፋት ወደ አውቶብስ መናኸሪያ ለመሄድ ጋሪ ስትጠብቅ ፒያሳ አደባባዩ ውስጥ ዋጋን አየቻት። ሁለት እግሯን ኳ እድርጋ ዘርግታ የከሰአቱ ፀሀይ ያለከለላ ይለበልባታል። እሷ ግን ለኃይለኛው ሙቀት ደንታ አልነበራትም። ትኩረቷን በቁምነገር የሳበው የሰበሰበችው

የወዳደቀ ወረቀትና የአስከርቢቶ ቀፎ ነበር። አንዱን ታነሳለች ሌላውን ትጥላለች። ትሩፋት እሷ ለመሆኗ ተጠራጥራ ትኩር ብላ ተመለከተቻት። ዛሬስ በዚያ በሚያሳዝን ድምጿ ሙሾ አታወርድም፤ አትዘፍንም። አፉን እንደ ተለጎመ ሰው ዝ—ም! ጭ—ጭ! ብላለች። ዝምታዋ ገርሟታል። ያቺ የባህር ዳር ላይ ቁጠማ የመሰለች ቀንበጥ ልጅ በሚያሳዝን ሁኔታ ተለዋውጣለች። ጥቁረቷ የተለበለበ ግንድ ይመስላል። ያ ሀር መስሎ ጀርባዋ ላይ ይገማሸር የነበረ ጸጉሯ ምን እንደ በላው አይታወቅም። የሆነ የተድበለበለ አመዳም ጥቁር አጎዛ የመሰለ ጸጉር ራሷ ላይ ተቆልሎ ይበልጥ አከፍቷታል። ምንም-- ምኗም ያችን ለግላጋዋን ዋጋን አይመስልም።

«ምስኪን! እድሜ ለአብዮት ፍቅሯን በልቶባታል--- ድርጅቷን ነጥቋታል---- እሷ ራሷን ለዚህ አብቅቷታል። ከእንግዲህ ምን ቀራት? አሁንማ ሰውም ለምዷት ማዘኑንና ከንፈር መምጠጡን ትቶ ረስቷታል።» ብላ ወደ አራዳ የሚሄድ ጋሪ ሲመጣላት ተሳፍራ ሄደች ትሩፋት። አውቶብስ መናህሪያ ሲደርሱ ሒሳቡን ለባለ ጋሪው ከፍላ እየተጣደፈች ጋሪው ላይ ወረደች። ባህርዳር ገብቶ አዳሪውን የመጨረሻ አውቶብስ ለማግኘት በማሰብ አበራሽ እየተጫወቱ አብረው እንዲያድሩ አጥብቃ ያቀረበችላትን ልመና አይሆንም ብላ የመጣችው ላራስ ልጇ መድረስ እንዳለባት በመወሰኗ ነው። ባጠጋቧ ውልብ ብሎ ያለፈው ሰው ግን ሳታስበው ልቧን አስደነገጠው። ዘወር አለች። አዳፋ ጋቢ ለብሶ በባዶ እግሩ የሚገሰግሰው ሰውም ዞር አለ። ዐይን ለዐይን ተጋጩ። ሁለቱም ባሉበት ቆሙ። ትሩፋት ወደ ኋላ ተመለሰች። ሰውየው ወደ ፊትም ወደ ኋላም አልተነቃነቀም። አካባቢውን በንቃት እየተቆጣጠረ ባለበት ቆሞ ጠበቃት።

«እያዩ ነህ አይደል?»

«ትሩፋት እንደ ምን አለሽ?» አላትና በናፍቆት ተቃቀፉ። አዳፋ ጋቢው፣ አጭር ሽንሽን ቀሚስ የመሰለ ቆምጣ ሱሪውና ወዝ የጠገበ ዱላው ፍጹም የአገር ቤት ሰው አስመስሎታል። እሷ እንኳን የወንድሟን ያህል የምታውቀውን እያዩን ልትስተው ምንም ያህል አልቀራትም ነበር።

«ተወልደህ ካደግህበት•ከተማ እንዲህ ሆነህ አያሰጋህም እያዩ? አብዛኛው ወጣት በግድም ይሁን በውድ የደርግ ደጋፊና የሰደድ አባል ሆኗል። አንዱ የሚያውቅህ ሰው ቢያይህ ሊጠቁምብህ ይችላል። በማትታወቅበት አገር ቢሆን አይሻልም ነበር» አለችው ትሩፋት ጭንቅ እያላት።

«ስጋትሽ ይገባኛል ትሩፋት ነገር ግን አካባቢውን ከሌሎቹ ጓዶች የተሻለ የማውቀው እኔ ሰለሆንኩና እኔ የበለጠ ልሠራው የምችለው ሥራ በመሆኑ ነው የተመረጥኩት። በተቻለ መጠን እጠነቀቃለሁ።   ከተያዝኩም አትሰጊ— ለመሰዋእትነት ተዘጋጅቻለሁ— ከኒን ይዣለሁ» አላት በልበ ሙሉነት። ለመሞት ቁርጥ ያለው ውሳኔውና ወኔው አንጀቷን

እንሰፍሰፎ በእጥፉ ቁርጥ አደረገው፡፡ ሆኖም ሀዘናን ወደ ውስጥ ዋጥ አደረገችው፡፡ የተናነቃትን እንባ አላፈሰሰችውም፡፡

«ድልነሳ ጋር ተገናኝታችሁ ታውቃላችሁ?» ውስጧን ፍርሃት-ፍርሃት እያላት ነበር የጠየቀችው፡፡ እጥብቆ ጠያቂ የእናቱን ሞት ይረዳል እንዳይሆንባት ከአፏ ከወጣ በኋላ ቆጫት፡፡ «በትግል ሜዳ እገሌ በተባለው ቦታ ላይ ተሰውቷል ቢለኝ አሁን እዚህ መንገድ ላይ ምን ልሆን ነው?» አለች በውስጧ፡፡

«እንደምታውቂው አቶባከኮ መብራት ኃይሉ እጠገብ በሞተው የደርግ ካድሬ ምክንያት የአካባቢው ወጣቶች በሙሉ ማለት ይቻላል የዚያኑ ቀን ነበር ጎንደር ከተማን ለቀን ያደርነው» ብሎ ትንሽ ተከዝ አለ፡፡ ትሩፋት ንግግሩን ለማስጨረስ የምትጠብቀው በሲቃ ሆነ፡፡ እሱ የዚያን ቀኑን ትረካ ቀጠለ፡፡

«ጎንደር ከተማን ለቀን ስንወጣ ከደርግ አፈናና ግድያ ለመዳን እንጂ በድርጅታችን የተጠና እካሄድ አልነበረም፡፡ ቁጥራችንም በርከት ስለሚል ሁላችንም በአንድ ጊዜ ለመቀበል ድርጅቱ ችግር ሳይሆንበት አልቀረም፡፡ ያለን አማራጭ ለጊዜውም ቢሆን ገጠር ውስጥ ከምናውቃቸው ዘመዶቻችን መጠለያ ማፈላለግ ነበር፡፡ በአጋጣሚ የእናቴ ታላቅ ወንድም የሚኖርበትን አካባቢ አውቅ ስለነበር እኔና ድሌ ወደዚያው አመራን፡፡ በደስታና በፍቅር ተቀበለን፡፡ የገበሬ ታጣቂዎችና ሰላዮች እንዳያገኙን ደብቆ አሰነበተን፡፡ ይኸው እንደምታይው ዓይነት የባላገር አልባሳት ሰጥቶ ሸኘኝ» አላት የባላገር እጎቱ ባለውለታነት እየተሰማው፡፡‹

«ይህን ሁሉ ጊዜ ከድሌ ጋር አብራችሁ ነበራችሁ ማለት ነው?» አለች ድልነሳ ያለበትን የአሁን ሁኔታ የማወቅ ጉጉቷ አይሎ፡፡

«ሜዳ- ስልጠና ላይ አብረን ነበርን፡፡ ከስልጠና በኋላ ግን ድሌ ኢሕአሠን ተቀላቅሎ በተዋጊው መስመር ተመደበ፡፡ እኔ በእርእዮተ-ዓለም ክፍል ውስጥ የፕሮፓጋንዳ ሥራ እንድሰራ ተደረገ፡፡ የሥራ ድልድላችን በመለያየቱ የተለያየ ቦታ መሄድ ነበረብን፡፡ አሁን እዚህ ከተማ የመጣሁት ግን ለተለየ ተግባር ነው» አላት፡፡ ትሩፋት ሳይቸግራት የወንድሟን ነገር ጠይቃ ይባስ ጭንቅ ውስጥ ገባች፡፡

«አሁን ሰሞኑን ግን ስንቅና ትጥቅ ወደ እርማጭሆ ቤዛችን ለማድረስ የሄዱ ጓዶቻችን እንደ ነገሩኝ ከሆነ ድሌ የአንድ ጋንታ መሪ ሆኗል እሉ፡፡ ጥሩ የጦር መሪና ተዋጊ እንደ ሆነ አጫውተውኛል፡፡ አይዞሽ! ተመችቶት ቁመት ሁሉ ጨምሯል እሉ» አላት ፈገግ ብሎ፡፡

«አንተም እኮ አድገሀል እያዩ» አለችውና በዐይኗ የምትለካው ይመስል ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ጸጉሩ ተመለከተችው፡፡ የወንድሟን በሕይወት መኖር ስትሰማ እፎይታ ተሰማት፡፡

«ለመሆኑ የበረሀው ኑሮ እንዴት ይዟችኋል? ርሀብና ጥሙ እንዴት እያደረጋችሁ ነው?»

«አታስቢ ትሩፋት፡፡ የወጣነው ብሩህ ዓላማ ይዘን ነው፡፡ የማይቀረውን የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ነፃነትና ድል እያሰብን ስለምንታገል ርሀብና ጥም--ሀሩርና ቁር አይፈቱንም፡፡ ዓላማና ግቡን ያወቀ ሰው እንኳን ጊዜያዊ ችግር ሞት እንኳ አያስፈራውም» አላት ፈገግ ብሎ፡፡

«በየእስር ቤቱ በደርግ ፋሽስታዊ ቶርቸር የሚሰቃየው ወጣት-- ሬሳው በየአስፓልቱ እንደ ሰጦ የተሰጣው ወጣት--- እስከ አፍጢሙ ከታጠቀ የደርግ ወታደር ጋር በየበረሀው ግንባር ለግንባር ገጥሞ የሚዋደቀው ለውጥ ናፋቂ ወጣት ሁሉ የተሰዋለት ዓላማ ግቡን መትቶ እውነት የተናፈቀው ፍትህ-- ነፃነትና ዲሞክራሲ ይገኝ ይሆን? ሕዝብ ራሱ በመረጠው መሪ በሕዝባዊ መንግስት ይተዳደር ይሆን?» ውስጧን ጠየቀች ትሩፋት፡፡ የሚሆን የሚሆን አልመሰላት እለ፡፡ በኢሕአፓ ውስጥ ተፈጠረ ስለሚባለው መከፋፈልና እዚህ እያዩ አፈቷ ቆሞ በቆራጥነት ስለ መጭው ብሩህ ጊዜ የሚነግራት ነገር አብሮ እልሄድልሽ አላት፡፡ የትግሉ ነገር ገና ጉዞው ረጅ--ምና አድካሚ ሆኖ ታያት፡፡ ነፍሷ ከውስጥ ትክት አለች፡፡ ድርጅታዊ ግንኙነቷ የተቋረጠባት መሆኑን ነግራው ሌላ የግንኙነት መስመር በእሱ በኩል ታገኝ እንደሆን ልትጠይቀው አሰባ ተወችው፡፡ ከድርጅቱ የስነ-ስርዓትና ደንብ ውጭ ይሆናል ብላ፡፡

«ብል እያዩ ድሌን ካገኘኸው ጠንካራ ታጋይ እንዲሆንና ከእጉል መስዋዕአትነት ራሱን እንዲጠብቅ ንገርልኝ» አለችው እንዳይታዘባት ናፍቆቷንና ስጋቷን ለመደበቅ እየሞከረች፡፡ እያዩ ግን አውቆባታል፡፡

«አይዞሽ ትሩፋት ከድል በኋላ ሕዝባዊ መንግሥት ተመስርቶ የወይራ ዝንጣፊ ይዘን ነጭ እርግቦች ሰማዩን በክንፋቸው እየቀዘፉ ነጻነታችንን የምናከብርበት ቀን እሩቅ አይሆንም» አለ እያዩ እሻ--ግሮ ማዶ--- ማዶውን ሩ-- ቅ እየተመለከተ፡፡ ሲናገር ፊቱ የተሰፋ ፀዳል አርብቦበት ነበር፡፡

«እስኪ እንደ አፍህ ያድርግልን» አለች ትሩፋት በሞተ ተስፋ፡፡ ቦርሳዋ ውስጥ የሆነ ነገር የምትፋልግ ይመስል እጎንብሳ ውስጡን መጎርጎር ያዘች፡፡ የተወሰነ ገንዘብ እውጥታ ልትሰጠው ስትል

«አትቸገሪ ትሩፋት፡፡ እድሜ ለኢትዮጵያ ሰፊ ገበሬ! ሳይማር እንደ አስተማረን ሁሉ ዛሬም ሳይበላ እያበላን--- ሳይጠጣ እያጠጣን-- ሳይለብስ እያለበሰን-- እቅፍ ድግፍ አድርጎ ይዞናል፡፡ ውለታውን በአምባገነኖች የተነጠቀውን ሰው በመሆኑ ብቻ ሊኖረው የሚገባውን ነጻነቱን በማስመለስ የሕይወት መስዋእትነት በመክፈል እንኳ እንጨርሰውም» እለ ትክዝ ብሎ አሁንም ሩ---ቅ እየተመለከተ፡፡

«እያዩ እሱን አጥቸው አይደለም:: ከአንዱ ቡና ቤት ገብተን ብንጨዋወት ደስ ባለኝ ነበር:: ግን ከደርግ ሰላዮች አይታ ውስጥ መግባት ይሆናል ብዬ ነው:: አባከህ ተቀበለኝ:: እኔን ደስ እንዲለኝ:: ያን ያክል ጠቃሚ ገንዘብ ሆኖ አይደለም» አለች እጇን ዘርግታ:: ደስ እንዲላት--- ደስ ሳይለው ተቀበላት::

ተሰነባብተው ሲለያዩ ሆዷን ከፉኛ ባር ባር እያለው ነበር:: የሞት ጥላ ከአንዣበበበት የጎንደር ከተማ በሰላም እንዲወጣ ተመኘችለት:: ከእይታዋ እስኪሰወር ድረስ እንደ ሀውልት ባለችበት ድርቅ ብላ እንባ ባቆረዘዙ ዐይኖቿ ሸኘችው:: ከዚያን ቀን በኋላ ከእያዩ ጋር ተገናኝታ አታውቅም:: እንግዲያው ለአንዳንድ ጉዳይ ጎንደር ከተማ መመላለሷ አልቀረም ነበር::

******

የደርግ መንግሥት የኢሕአፓን መዋቅር ከሚበጣጥስበት አንዱ ስልቱ እስሮ የፈታውን ተጠርጣሪ ሁሉ ከዱሮ ምድብ ቦታው ላይ ማንሳት ነበር:: ትሩፋት ከአንበሳሜ ተነስታ አዲስ ዘመን ገብታለች:: አልከፋትም:: በዶቅማ ዛፍ በተከበበችው ሽኒ ወንዝ ዛሬም እንደ ልጅነቷ መዋኘት ትችላለች:: የተራራ ሰንሰለት ዙርያዋን ያጠራት የአዲስ ዘመን ከተማን አስከ አሮጌ ቤቶቿ ዛሬም ትወዳታለች:: አዲስ ዘመን አልተለወጠችም--አላደገችም በልጅነቷ እንደምታውቃት እንደ ነበረች አለች::

ድሮ የተማረችበት--- አሁን የምታስተምርበት የአዲስ ዘመን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አርጅና ጨምሮ አገኘችው:: ለከተማዋ አንደ ትልቅ ለውጥ ሆኖ የሚታየው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሽኒ ማዶ ተሰርቷል:: አጋጣሚውም ለትሩፋት ጥሩ ሆኖላታል:: አህቶቿን አንድ ላይ አድርጋ ለማስተማር አመቻት:: እስረኛ ባሏን ለመጠየቅ ትራንስፖርት አልተቸገረችም:: ቧት ሄዳ ማታ መመለስ ትመለሳለች:: ለትሩፋት ከፉ ራስ ምታት የሆነባት ከድርጅቷ ጋር የነበራት ግንኙነት እንደ ዋዛ ተቋርጦ መቅረቱ ብቻ ነው:: በይነበብ በኩል ወረታ አግኝታው የነበረው ሰው ያን አካባቢ ለቆ ሲሰወር ከተገናኙ የሳምንት እድሜ እንኳን አልቆየም:: አያደር የሚሰማውና የሚታየው ነገር ደግሞ ጨርሶ ተስፋ አስቆራጭ ሆነ:: ሰንት መስዋዕትነት የተከፈለላት ኢሕአፓ--- ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ የነበራት ኢሕአፓ-- የበሰሉና የሰከኑ የአመራር ሰዎችን እጥታ ከላይ ጀምራ ተናደች::

አዲስ ዘመን ለበለሳና ለቆላ መቀጣዋ ቅርብ በመሆኗ በየቀኑ የደርግ መንግሥትን ምህረት እየጠየቀ የሚገባው የኢሕአፓ አባል ወጣት ቁጥር ከግምት በላይ ነበር:: የትሩፋትን ተስፋ ጨርሶ የገደለው ደግሞ በየቀበሌው «የማጋለጥ ዘመቻ» ብሎ የኢሕአፓን የማፈራረስ አዲሱን ስልቱን ከተመለከተች በኋላ ነበር:: ይህ በየቀበሌው ያካሄደው የማጋለጥ ዘመቻ ደርግ ራሱን በበላይነት አጠናክሮ እንዲወጣ በእጅጉ ጠቅሞታል::

«ሀሎ ሀሎ በቀበሌያችን ኗሪ ለሆናችሁ በሙሉ!! ዛሬ አጠቃላይ የቀበሌ ነዋሪዎች ሰብሰባ ለለሚካሄድ እድሜው ከአስራ አምስት ዓመት በላይ የሆነ ሁሉ በየቀበሌው ጽሕፈት ቤት እንዲገኝ በጥብቅ እናሳታውቃለን!! በማይገኙ ነዋሪዎች ላይ አብዮታዊ እርምጃ የምንወስድ መሆናችንን ከወዲሁ እናስታውቃለን! የቀበሌው አስተዳደር!» ይህ ለፈፋ በተለይ አሁድ አሁድ የማይቀር ዕዳ ሆነ::

«አድሀሪው ፊውዳሊዝም --ቢሮከራቱ ካፒታሊዝም ይውደም!!» ካድሬው ማይክራፎኑን ይዞ ከወዲያ ወዲህ እየተንቆራጠጠ የአንገቱ ስር እስኪገታተር ድረስ መፈክር ያሰማል:: ግራ እጁን ጨብጦ ወደ ላይ ይሰቅላል---በርግማን ያወርዳል:: እንደ ዘፈን አውራጅና ተቀባይ ሕዝብ ካድሬውን ተከትሎ ይጮሃል::

«ዝርዝር እውጥተን ስማችሁን ከምንጠራውና ከመታሰራችሁ በፊት ራሳችሁን አጋልጡ!» አለ የቀበሌው ካድሬ:: ሰም ዝርዝር የያዘ ነው የሚለውን የውሸት ወረቀት እያገላበጠ:: የተሰበሰበው ሕዝብ ምጥ ይዞት ጸጥ! ረጭ! ብሎ ያዳምጣል::

«ተፀፅቶ ያለማንም ጠቋሚ በራሱ ፈቃድ ወደ አብዮቱ ካምፕ የሚቀላቀለውን ሁሉ በአብዮት እቅፍ እንቀበላለን:: እልተነቃብንም ብለው የሚያደፍጡ ፀረ- አብዮተኞችን ግን ልንታገላቸው እንችልም:: የሊታሊን ሰይፍ ልንመዝባቸው አንገደዳለን:: በተሰጣችሁ አድል ተጠቀሙ! አያምልጣችሁ!» ይላል ካድሬዉ ለጨረታ እንደ ቀረበ እቃ እየደጋገመ:: ከብዙ ልፍለፋና ማስፈራራት በኋላ የሆነውን ማየት ግን ያሳዝናል:: ወጣት ሁሉ ለማእድ እንደ ተጠራ ሰርገኛ አንዱ አንዱን እያየና እየተከተለ ወደ መድረኩ ተግተለተለ::

በፍርሃትና በደመነፍስ ወደ መድረክ የሚወጡትን ወጣቶች በትዝብት ነበር የተመለከተቻቸው ትሩፋት:: የፈለገው ቢሆን እዚህ ሕዝብ መሀል ራሷን እንደማታጋልጥ ለውስጧ ነግራ ወጣቶችን በግርምት እየተመለከተች ተቀምጣለች:: ጭብጨባውና ቅስቀሳው ቢሞቅም አሷን ግን መንፈሷ ቀዝቅዞ ብርድ ብርድ እያላት ነበር:: ይህን ያላሰበችውን አሳዛኝ ትዕይንት ዓይታ ወደ ቤቷ ስትመለስ ሁሉ ሰለ ኢሕአፓ የትግል ጊዜ እያሰበች ነበር::

******

ትሩፋት ለንቅ ቋጥራ-- የታጠበ ልብስ ይዛ እስረኛ ባሏን ለመጠየቅ እሁድ እሁድ ባህርዳር መሄዷ የማይቀር ነው:: ለፍቅሩም ቢሆን ለሳምንት ቆጥቦም ቢሆን የሚጠቀምበት ሁለት ፓኮ ሲጋራ አትነሳውም:: በጨካኙ የደርግ መንግሥት እጅ ወድቆ ባታገኘው ምርጫዋ ነበር:: እንዲህ ተንገላቶና ተጎድቶ ባታየው ምኞቷ ነበር:: ግን ሆኗል:: የአጋጣሚ ነገር ሆኖ በተጎዳበት ጊዜ ስለ ደረሰችለት ደግሞ በጣም ደስ ብሏታል:: ሳደረሰችበት የፍቅር በደል ሁሉ መጠነኛ ማካካሻ የሆነላት ይመስላታል:: ሁለቱን ጠይቃ አየባከነች እውቶብስ ተራ

ትሄዳለች:: አዲስ ዘመን ጉብታ ለማደር:: ዛሬ ደግሞ ቴዎድሮስንም ይዛዋለች:: ይነበብ እንዲያየው እልፎ እልፎ ታመጣለታለች:: ልጅ ይዛ መናኸሪያው ድረስ ከመሄድ ይልቅ አባይ ድልድዩ ላይ መላፈር ይቀርባታል:: እውቶብሱ ምንጊዜም አባይ ላይ ለፍተሻ መቆሙ የማይቀር ነው::

«ሞልቶ ይመጣና አላሳፍር ይለኝ ይሆን?» እያለች ወደ እውቶብስ መናኸሪያው በመሄድና ባለመሄድ መሀከል ሆና ገና ሀሳቧን ሳትቆርጥ:: «ትሩፋት» የሚል ድምጽ ሰምታ ዞር አለች:: ወታደር ታከለ ነበር::

«አዲስ ዘመን ፖሊስ በእግር በፈረስ እየፈለግሽ ነው:: መሄጃ--መሸሸጊያ--ማምለጫ ካለሽ ጥፊ!--እምልጪ!» አላት:: ወታደር ታከለ አብሮ አደግ ጓደኛዋ ነው:: አዲስ ዘመን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት አብረው ተምረዋል:: እሁንም ቢሆን በፖለቲካው በኩል የመሰመር ልዩነት ያላቸው አይመስላትም:: ከንግግሩና ከተግባሩ ትገምታለች::

«ዛሬ ደግሞ ምን ወንጀል ተገኝቶብኝ ይሆን ፖሊስ የሚፈልገኝ?» አለች ትሩፋት ደንግጣና ግራ ተጋብታ::

«ሥራሽን የምታውቂውማ አንቺ ነሽ:: በፖሊስ መፈለግሽን ብቻ ነው እኔ የማውቀው:: ምን እልባት መንግሥት ለመገልበጥ አሲረሽ ሳይሆን አይቀርም:: እናንተ ምናችሁ ይታመናል» ብሎ ፈገግ አለ::

«እኛ ደግሞ አነማን እንሆን?» አለች እሷም ፈገግ ለማለት እየሞከረች:: ውስጧ ግን ተጨንቋል::

«ለጊዜው እሱን እርሺው:: እንደ አብሮ አደግነቴ ግን አደጋ ላይ መሆንሽን እየነከርኩሽ ነው::»

«አመሰግናለሁ ታከለ:: ምንም ቢሆን የሸኒን ውሃ አብረን ጠጥተናል፤ ዶቅማዋን ተሻምተን ለቅመናል፤ ዋሚትና አላብ አብረን ዋኝተኛል፤ ይህንን እንኳን እኛ የላበው ቆሌ አባ ወርቄም ያውቀዋል» አለችው እጁን ጭብጥ አድርጋ::

«የአብሮ ማደግ ገመድ ባይጎትተኝማ ኖሮ ሁለት እጅሽን ለኋሊት ጠፍሬ እየነዳሁ ነበር አዲስ ዘመን ፖሊስ ጣቢያ የማስረክብሽ:: ለእኔም እንደ አንድ የአብዮት ጀብዱ በተቆጠረልኝ ነበር ወይም የአብዮት ውለታ::»

«ደጋግሜ አመሰግናለሁ ብልህ ቃሉ ያንስሃል:: የአብሮ አደግ ጓደኝነት ግዴታህ ነው ብልህ ይሻለኛል:: ስሜቴን በትክክል ይገልጸው ይመስለኛል::»

«ማድረግ የሚገባኝን ነው ያደረግሁት:: ማመስገን አይጠበቅብሽም ትሩፊ:: ይልቅ ረስቼ ሳልነግርሽ ልሄድ ነበር:: በይ አጥብቄ የማስጠነቅቅሽ ነገር ቢኖር ፖሊስ እየፈለገሽ መሆኑን እኔ አልነገርኩሽም:: ባህርዳር በሚሉት ከተማ ውስጥ ፈጽሞ አልተገናኘንም--አልተያየንም--ልባድርጊ!»

«ኧረ በፍጹም! አለመገናኘት ብቻ ላይሆን አንተዋወቅም::»

«እሱ እንኳ እያዋጣም:: የሸኒን ውሃ ጠጥተንና አብረን ዋኝተን ማደጋችንን የላበው ቆሌ አባ ወርቄም ሊያጋልጠን ይችላል:: ይልቅ አሁን በዚች ሰዓት በዚች ቦታ አብረን አይደለንም:: በይ አንዱ እግር የጣለው እንዳያገኘንና እንዳይጠቁምብኝ ሳምልጥ:: መልካሙን ሁሉ እመኝልሻለሁ ትሩፋት--- ደህና ሁኚ::» ወታደር ታከለ ተሰናብቷት እየተጣደፈ ሄደ::

ትሩፋት በፖሊስ የምትፈለግበትን ጉዳይ ብታውጠነጥን--ብታነሳ ብትጥል ማወቅ ቀርቶ መገመት አልቻለችም:: የት ትሂድ? ምንስ መሸሻ አላት? እንዲያ የምታምናት ድርጅቷ በዚህ የጭንቅ ጊዜ ጥላ ከለላ ልትሆናት አልቻለችም:: የራሷ ህልውናም አልቆመም:: ነገሩ ሁሉ እንዳይሆን እንዳይሆን ሆኗል:: ቤተሰቧንና አስረኛ ባሏን አሰበች፤ ፍቅሩንም ጭምር:: ከእንግዲህ ለእነሱም ስንቅ አቀባይ ላይኖር ነው:: ብዙ አሰበች:: ብዙ ተጨነቀች:: ምንም መሸሻ አልነበራትም:: የመጣውን ለመቀበል ቀጥታውን አዲስ ዘመን ሄደች:: ከቤቷ አልገባችም:: መምጣቷን የሚጠባበቅ ወታደር ታዞ መናኸሪያ ውስጥ ይጠብቃት ነበር:: ገና ከእውቶቡሱ ውርድ ከማለቷ

«ትሩፋት ደህና ዋልሽ?» አላት አንድ ፊቱን ከፍት ያለው ወታደር::

«እንደ ምን ዋልክ? አሰር አለቃ» አለችው ከዚህ ወታደር ጋርም ይተዋወቃሉ:: የአባቷ ጎረቤት ነው::

«ፖሊስ ጣቢያ ትፈለጊያለሽ» አላት ጭንቅ እያለው::

«ለምን ጉዳይ ነው የተፈለግሁት?» አለች ምንም እንዳላወቀች ሆና::

«ለምን እንደ ተፈለግሽ የተነገረኝ ነገር የለም:: አቤትሽም ወታደር ተልኮ ነበር:: ባህርዳር መሄድሽ ታውቋል:: እኔ እዚህ መናኸሪያ ውስጥ እንድጠብቅሽ ታዝዤ ነው» አላት ቅር እያለው::

«ልጁን እቤት ላድርሰውና ልመለስ» አለችው::

«በዚሁ ነው እጅቤ እንዳመጣሽ የታዘዝኩት፡፡ ልጁን እቤቱ ማን ያድርስልሽ ይሆን?» አለ እሁንም እንደተጨነቀ፡፡ ቀጠሰና ጉዳይሽ ቀላል ይሆንና ወዲያው ትመለሽ ይሆናል፡፡ ይዘሽው ብትሄጅ ይሻላል ትሩፋት» ሲላት በውስጡ ደግሞ «ወንጀል ቢኖርባት እንኳ ልጅ መያዟ ያቀልላት ይሆናል» እያለ ነበር፡፡ በአጋጣሚ ግን ጎረቤቷ የሆነ ሰው አግኝታ የያዘችውን የምግብ ሳህን፣ ያልታጠበ ልብሰና ቴዎድሮስን እቤት እንዲያደርሱላት ላከች፡፡

ፖሊስ ጣቢያ ደርሳ ምርመራ ክፍል ስትገባ ግን ያየችውን ማመን አቃታት፡፡ መጀመሪያ የኢሕአፓ አባል እንድትሆን በሕዋስ ደረጃ የመለመላት ሙሉዓለም የተባለው ወጣት ቁጭ ብሏል፡፡ ሜዳ ከሄደ የቆየ መሆኑን ሰምታለች፡፡ እሱ በሄደ ሰሞን ኢሕአፓ በአንድ በኩል በኤርትራና በትግራይ ጎጠኛ ሽምቅ ተዋጊዎች በሌላ በኩል ደግሞ በደርግ ጦር እጣብቂኝ ወስጥ ገብታ ብዙ አባሎቿን እጥታ ነበር፡፡ በሕይወት ይኖራል ብላ በፍጹም እልጠረጠረችም ነበር፡፡ ሰታየው ደስ እሳት፡፡ የተጨበረረ ጸጉሩ የከሳ ፊቱን ውጦታል፡፡ ጠይምነቱ ቀርቶ ጠቁሯል፡፡ ብዙ መንገላታቱ ገፅታው ላይ ይነበባል፡፡ የሰየችው እስተውላ ዐይኑን ከተመለከተችው በኋላ ነበር፡፡ በፖሊስ ታጅባ ምርመራ ክፍል ግብት ስትል ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ብድግ እለ፡፡ መርማሪው ፖሊስ በመገረም እየተመለከተው መሆኑን ሲያውቅ ተመልሶ ቁጭ እለ፡፡

«እንኳንም በሕይወት ኖረ» አለች በውስጧ ትሩፋት፡፡ ቀጠል አደረገችና «ድሌ የት ደርሶ ይሆን? እንደ እያዩ...» ማሰቡ ራሱ እንቀጠቀጣት፡፡ እያዩ የድልነሳ ጓደኛ የተበጣጠሰውን የሜዳውንና የከተማውን የኢሕአፓ መዋቅር እንደ ገና በአዲስ መልኩ ለማዋቀር የተሰመደ ተግባሩን ሲያከናውን ለዚች የመከራ ጉዞዋ ገና ለአላለቀላት እገር.... እድገቷንና ለውጧን ተመኝቶ ሲታገል በደርግ እፋኝ ቡድኖች እጅ ይወድቃል፡፡ እንደ ፎከረው የያዛትን የሞት ክኒን ውጦ ገና በእፍላ የወጣትነት እድሜው ይሰዋል፡፡ የእያዩን ቆራጥ መስዋዕትነት የሰማች ጊዜ መሪር ሀዘን አዝና ነበር፡፡

«ግን ለምን በራስ ቤተሰብ ላይ ሲመጣ ያስጨንቃል? ስንቷ ኢትዮጵያዊ ወንድሟን፣ ልጇን፣ ባሏን... እጥታ የለ፡፡ ለምን ሁሌ ወንድሜን ድሌን ብቻ እስባለሁ?....» በውስጧ ራሷን በመውቀስ ላይ እያለች ጎርነን ያለው የመርማሪ ፖሊሱ ድምጽ ከሐሳባ መለሳት፡፡

«ትሩፋት እንኳን ደህና መጣሽ፡፡ እሱ ላይ ተቀመጭ» እላት ፊት ለፊቱ ያለውን ወንበር በእጁ እያመለከታት፡፡ ወንበሩ ጫፍ ላይ በተጠንቀቅ ቁጭ እለች፡፡

«ከዚህ ሰው ጋር ትተዋወቃላችሁ አይደል?» አላት፡፡ እተኩሮ ውስጥ ድረስ ዘልቆ እየመረመራት፡፡ እላመነታችም፡፡

«አዎ! እንተዋወቃለን» እለች፡፡ ይህን ስትል ምህረት ጠይቆ የገባው ሙሉዓለም የተረጋጋ መሰለ፡፡ በማጋለጡ ዘመቻ ሁሉም ሰው የሚያውቀውን ጓድ ሁሉ ያስመዘገበ መስሎት

የቀረው ሰው እልነበረም፡፡ እንደ ትሩፋት ያላጋለጠ መኖሩን ቢያውቅ ኖሮ ስሟን ባላነሳውም ነበር፡፡ በፖሊስ ታጅባ ስትመጣ ፀፀት ውስጥ ውስጡን እንደ እሳት እየለበለበው ነበር፡፡ እንደ ማታውቀው ትሆንና ደግሞ ሌላ ከባድ ችግር ይፈጠርባት ይሆን እያለ እቤት!! ነፍሱ ከውስጥ እንዴት ተጨንቃ እንደ ነበር ከራሱ በቀር ከቶ ማንም ሊረዳለት አይችልም፡፡ ስትገባ ብድግ ያለው የሚተዋወቁ መሆናቸውን እንዳትደብቅ ጥቆማ መሆኑ ነበር፡፡ እሷም ገብቷታል፡፡

ትሩፋት መንግሥት በሰጠው የማጋለጥ ዘመቻ እድል ሳትጠቀም በመቅረቷ ታሰረች፡፡ የእሷ መታሰር በስሯ የተሰባሰበውን ቤተሰብ ሕይወት የሚያናጋው መሆኑን ስታስብ ጭንቅ እላት፡፡ ለጊዜው እንኳ እደራ የምትለው ሁነኛ ሰው የላትም፡፡ የሥራ ባልደረቦቿና ጓደኞቿ የተረፋቸው አይደሉም፡፡ እንደ እሷው ወር ጠብቀው እዳሪዎች ናቸው፡፡ ሥራ በያዘችባቸው ዓመታት ውስጥ ለጊዜው ተሸጦ ቀን የሚያወጣ ጥሪት አልያዘችም፡፡

አባቷ አሁን ጡረታ ወጥተዋል፡፡ በፈረሰኛነት ይጫንላቸው የነበረው እህል በመሬት ላራሹ እዋጅ ምክንያት ቀርቷል፡፡ ከሌላ የወለዷቸውን እራት ልጆች ማሳደግ እንኳ ተስኗቸው በጭንቅ ነው ሕይወትን የሚመሯት፡፡ ትሩፋት ከእናቷ የወለዷቸውን እምስት ልጆች ተረከባ ማሳደጓ እንዴውም በጅቷቸዋል፡፡ በጡረታ ደመወዝ ዘጠኝ ልጅ ማሳደግ እንዴት ይችሉት ነበር? እንዳንድ ጊዜ ለኪሳቸዉ መጠበቂያ ትንሽ ብር ብትሰጣቸው እንኳ አይጠሉም፡፡ የእባቷ አቅም እስከዚህ ድረስ ነው፡፡ ምን እልባት እናቷ እህላ እህል በመላከ ለጊዜው ለሆድ የሚሆን ነገር ላይቸግር ይችል ይሆናል፡፡ እስረኛ ባሏ ይነበብና ፍቅሩም ያስእሷ ማንም ጠያቂ ዘመድ የላቸውም፡፡ ሐሳብ ብጥብጥ አደረጋት፡፡

ከፖሊስ ጣቢያው ማረፊያ ክፍል ስትገባ ቀድመዋት የመጡ ሁለት ሴት እስረኞች ነበሩ፡፡ በምን እንደ ታሰሩ ባታውቅም ማታውኑ ነው ተፈተው ወደየቤታቸው የሄዱት፡፡ የታሰረችባት ክፍል ጠባብ ናት፡፡ እንጨት በእንጨት የተሰራች ስትሆን አዲስ ጭቃ ልጥፍ ናት፡፡ በአግባቡ እንኳ አልተለሰነችም፡፡ ገለባና ሳር የተልከሰከሰበት የአፈር ወለል ገና እግር ሲያርፍበት የቁንጫ ሰራዊት ውርር ያደርጋል፡፡ የቁንጫውን መንጋ እንዲጋሯት የነዚያን ሴት እስረኞች መኖር ተመኘች፡፡ ከጎኗ ካለው ክፍል የታሰሩት ወንድ እስረኞች ቁጥራቸው በርከት እንደሚል ከድምጻቸው ገምታለች፡፡

ራሔል እቤት ድረስ ወታደር ተልኮ ትሩፋት ፖሊስ ጣቢያ እንደምትፈለግ የተነገራት ቢሆንም ለእስር እልመሰላትም ፡፡ ቴዎድሮስን ሌላ ሰው ይዞት ወደ ቤት ሲመጣ ግን ዋዛ ነገር እንዳልገጠማት እወቀች፡፡ የኢሕአፓ መዋቅር ከላይ እንደ እንቧይ ካብ ተንዶ---ነገር ዓለሙ ሁሉ ተለዋውጦ የተሰደደውም ተሰዶ— ወደ ከተማ የሚገባውም በምህረት ገብቶ እጅ በሰጠበት በዚህ በእበቃለት ሰዓት ዳግም እስር ይገጥማታል ብላ ፈጽሞ አልጠበቀችም፡፡ የተላከው ሰው የሆነውን ሁሉ ሲነግራት ለማመን ተቸግራ ነበር፡፡ የእስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ልትወስድ እየተዘጋጀች ነው፡፡ በዚህ ወሳኝ ወቅት ይሆናል

ብላ ያሳሰበችው ሁኔታ መከሰቱ መጣም እሰደነገጣት:: እራትና ለመኝታ የሚሆን ብርድልብስና እንሰላ ይዛ ፖሊስ ጣቢያ ስትደርስ ጓደኞቿ ትዛሉና እልፍነሽ ቀድመው ሄደው ኖሮ እዚያው አገኘቻቸው:: ሲታያት እንባዋን መቆጣጠር አልቻለችም:: ያመጡላትን እራት ሰጥተዋት ተመለሱ::

«ራሔል ለቅሶ ምንም የሚጠቅመው ነገር የለም:: ትንሽ ቀን እጉላላ ይሆናል እንጂ አይዞሽ ሌላ የከፋ ነገር አይደርስብኝም:: ይልቅስ የቤቱ ጣጣ ሁሉ ኃላፊነቱ አንቺ ላይ መውደቁ ነው ያሳዘነኝ:: መጠንከር አለብሽ:: ስለዚህ ምን ማድረግ እንዳለብን መመካከሩ ነው የሚሻለው» አለች ትሩፋት:: ራሔል እንባዋን ጠራርጋ የሚሆን የሚሆነውን ተመካከረው ተሰያዩ::

ትሩፋት ጓደኞቿና ራሔል ያመጡላትን ምግብ አልበላችውም:: በውስጧ ጠብታ ታከል የምግብ ፍላጎት አልነበረም:: ለወንዶቹ እስረኞች ላከችላቸው:: ፀሀይ ከማደሪያዋ ስትገባ መብራት የሌላት ከፍል ጭልምልሟ ወጣ:: ሻማ እንዳታስመጣ አይፈቀድም:: ብቻዋን በጨለማው ውስጥ አፍጣ ተቀመጠች:: ቁንጫ ከስር--ሀሳብ ከውስጥ እየበጠበጧት:: መንፋሷና አካሏ መቋጫ በሌለው ሐሳብ ናወዘ:: ድካም ተሰማት:: ትንሽ ጋደም አለች:: እንቅልፍ ሸለብለብ ሊያደርጋት ሲል በሯ ቀስ ብሎ ሲከፈት እንደ ህልም ሰማችው::

«ማነው!?» አለች በደመነፍስ:: ከመነሳቷ በፊት አንድ ወፍራምና ከባድ እጅ እላይዋ ላይ አረፈ:: አፏ ከመታፈኑ በፊት አንድ ጊዜ በኃይል ጮኸች:: ባለ በሌለ ኃይሏ ተፈራግጣ ከእንገቷ ቀና አለች:: በድንጋጤ ስትፈራገጥ እላይዋ ላይ ሊወጣ የነበረውን ሰው ጭኖቹ መሀል ጥሩ አድርጋ እግኝታው ኖሯል:: የማቃሰት ድምጽ አሰምቶ እላይዋ ላይ አርፎ የነበረው ከባድ እጅ ለቋት በጨለማው ውስጥ ወደኋላ ተፍገምግሞ ሊወድቅ ሰማችው:: የጠባቧ ከፍል ግድግዳ ሳያገኘው አልቀረም:: ቶሎ ብላ ራሷን ገዝታ ዐይን ቢወጉ በማይታየው ጨለማ ውስጥ ድምጿን አጥፍታ አደፈጠች:: ራሷን ለመከላከል ተዘጋጅታ መጠባበቅ ጀመረች:: ከወድያኛው ወንዶች ከታሰሩበት ከፍል

«ምንድነው!?-- ምን ሆንሽ!?--ማነው እሱ በዚህ በጨለማ ከፍልሽ ውስጥ የገባው!?» የሚል የብዙ እስረኞች ድምጽ ተሰማ:: ሁኔታው ያልቀናው ዘብ ወታደር ትሩፋት ደንግጣ በደመነፍስ ስትፈራገጥ ሳያስበው ባጋጠመው ምት ለቅጽበትም ቢሆን ይህ ነው ከማይለው ስቃይ ውስጥ ገብቶ ነፍስና ስጋው የተሰያዩ መስሎት ነበር:: የወንድ እስረኞችን ጩኸት የሚያዳምጥበት አቅልና ጆሮ አልነበረውም:: እጁን ጭኖቹ መሀል ወሽቆ ባሰበት ድርቅ ብሏል:: ነፍሱ ትንሽ መለስ ስትልለት የሀፍረት ብልኮውን ተከናንቦ ስቃዩን ጥርሱን ነክሶ ችሎ እያነከሰ ሹ---ከክ ብሎ ወጣ::

«ምንድነው ጩኸቱ? ዝም አትሉም? ፖሊስ ጣቢያውን ሰብራችሁ ለማምለጥ አስባችሁ ከሆነ ረብሻ የምትፈጥሩት እኔ መተኮሴ ነው» ብሎ መሳሪያውን እንገጫገጨ:: ልክ ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ሁሉ::

«እኛ ምንም አረብሻ አልፈጠርንም:: ከሴቷ ከፍል ምን ልታደርግ ገብተህ ነበር? ያለምክንያት አልጮኸችም::»

«እኩለ ሌሊት ላይ ምን ፈልገህ ሄድክባት?»

«እርኩስ ነህ! ጨካኝ! ቆይ ይኸ ቀን ያልፍና እንገኛለን!» ዛቻና ስድብ ከወንዶች ከፍል ጎረፈ::

«ማንም በእንቅልፍ ልቡ የቃዠ እንደ ሆነ እናንተ ዝም ብላችሁ መጮህ አለባችሁ? የባሰ ነገር ሳይከተላችሁ ዝም ብትሉ ይሻላችኋል» አለ ወታደሩ አሁንም መሳሪያውን እያንገጫገጨ:: በተፈጠረው ሁኔታ ግን ደንግጧል::

«ምን ልታደርጋት እንዳሰብክ ነቅተንብሃል::»

«እንደ ሌሎች ሴት እስረኞች ሞኝ መሰላህ ዛሬ ጉድህ ተጋለጠብህ! ጎሽ እበጀሽ የእኛ ጀግና!»

«እችም ስልጣን ሆነችና በሴት እስረኞች ላይ የምትፈጽመውን ግፍ ሁሉ የማናውቅ መስሎሃል አንተ ውሻ!»

ሁሉም እስረኛ በንዴት ይናገራል:: ይሳደባል:: የሁሉንም እስረኛ ጩኸት ግን የእኩለ ሌሊቱ ጨለማ ውጦ አስቀረው::

«እንደ ሌሎች ሴት እስረኞች መሰለሽው ሊጫወትብሽ ነበር:: አንቺ ግን ጀግና ነሽ:: እዚህ ከጎናችን ስንት ጉድ ሲሰራ ሰምተናል መሰለሽ:: ጩኸትሽን በማሰማትሽ ከእንግዲህ ይገርፍሽ እንደ ሆነ እንጂ እይደፍርሽም:: ይህ ነውረኛ ጉዱን ስለሰማንበት ዳግም አይሞከራትም» እያሉ በጨለማው ውስጥ ሊያጽናኗት ሞከሩ:: ትሩፋት ግን ንዴትና ጥቃት እንገበገባት:: መጽናናት አልቻለችም:: እንዲሁ ዐይኗ እንደ ፈጠጠ ያ አስፈሪ ጨለማ ተገፎ ፀሐይ ብርሀኗን መፈንጠቋ አልቀረም:: የትሩፋት ልብ ግን እንደ ጠቆረ ነው:: ጽልመት እንደ ዋጠው:: በነቃቃው የጭቃ ምርግ የገባው የፀሀይዋ ወርቃማ ጨረር እንደ ሁልጊዜው ልዩ ደስታ ፈጥሮላት መንፈሷን ዘና አላደረገውም:: እንግዲያው ለተፈጥሮ ስስ ልብ---ተመልካች ዐይን--- አድናቂ አዕምሮ ነበራት:: ይልቁንስ አልህ ተናነቃት--ንዴት አቃጠላት--ቁጭት እንገበገባት--ጥቃትና ውርደት ተሰማት:: ከውስጧ የሚወጣው የሚፋጅ ትንፋሿ ደረቷን--ጉረሮዋንና አፏን እንደ እሳት ይለበልባት

ጀመር፡፡ ምላሷ አረረ፡፡ ከንፈሯ እንደ ከብት ደረቀ፡፡ ጧት ራሔል ቁርስ ይዛላት መጣች፡፡ ሌሊት በአንድ ተራ ወታደር ሊደርስባት የነበረውን ውርደትና ግፍ ስትነግራት የሰራ አከላቷ በንዴት ይንቀጠቀጥ ነበር፡፡ የደርግ መንግሥት ወድቆ እንዲህ በብዙ ሴቶች ላይ የሚደርሰው መዋረድ በአደባባይ ተጋልጦ ትክክለኛ ፍርድ የሚገኝበትን ጊዜ በእጅጉ ተመኘች፡፡

ትሩፋት እስራቷ ብዙ አልቆየም፡፡ በወዳጅ ዘመድ ተሂዶ ሦስት ጠንካራ ዋሶችን አቅርባ ያደማችውን አብዮት ልትከስ ቃል ገብታ ተፈታች፡፡ ኢሕአፓ በራሷ የውስጥ ችግር ከላይ መፈራረስ ስትጀምር ለስልጣኑ እንደ ማታሲጋው የደርግ አምባገነናዊ መንግሥት በሚገባ ተረድቶታል፡፡ ለዚህ ይመስላል እስሩንም ግድያውንም ቀለል አድርጎት ነበር፡፡ ኢሕአፓ ከእንግዲህ እንዳትነሳ ሆና አከርካሪዋ ተመቷል ብሎ አምኗል፡፡ ኢሕአፓ ከራሷ ውስጣዊ ችግር በተጨማሪ ደርግ በወሰደው የማጋለጥ ዘመቻ የከተማውን መዋቅር ዳግም እንዳያንሰራራ አድርጎ አነኳኩቶታል፡፡ ዳግም ለድርጅታዊ ስራ የተረፈ ልብ እንዳይኖር አድርጎ የወጣቱን የትግል ወኔ ገሎታል፡፡

ኢሕአፓን የመሰሰች ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ የነበራት አገር አቀፋዊ ድርጅት እርስ በእርስ መቻቻልና መናበብ አቅቶ ከላይ ጀምሮ መሰረቷ ፈራርሷል፡፡ ከእንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር እንዴት እንደሚፈታ የሚያታየው በጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ለአሁኑ ዝም ብሎ ከመቀመጥ ሌላ አማራጭ አልነበረም፡፡ በተለይ እንደ ትሩፋት በኢሕአፓ ላይ ጽኑ እምነት ለነበራቸው ጓዶች በአንባገነኑ የደርግ መንግሥት መዳፍ ሥር በዚህ ሁኔታ መውደቅ የሞት ያህል ከባድ ነበር--- ግን ምንም ማድረግ ላይቻል ቀረ፡፡

******

ትሩፋት የማስተማር ስራዋን እየሰራች ቤተሰቧን ማስተዳደር ጀምራለች፡፡ ውስጧ ግን ርካታ አግኝቶ አያውቅም፡፡ ሁልጊዜ የማይጠቅም ባዶ ተራ ኑሮ እንደምትኖር ያህል ነበር የሚሰማት፡፡ ከሰኞ እስከ አርብ ታስተምራለች-— በማትፈልገው የደርግ ስብሰባ ላይ መገኘት ግዴታዋ ነው--- እሁድ እሁድ እስረኛ ባሏን ለመጠየቅ ባህርዳር ትመላለሳች፡፡ እስልቸው የሕይወቷ አዙሪት ይህንን ይመስላል፡፡ ይመሻል— ይነጋል፡፡ ትርጉም የሌው የኑሮ ጉዞ--- እንደ እንስሳ በልቶ መተኛት--ተኝቶ መነሳት በቃ ይኸው ሆነ!!

ከሁሉም የሚያናድዳትና ሰልችት የሚላት ደግሞ በየጊዜው ባልፈለገችው ስብሰባ ሁሉ የመገኘት ግዴታና መዋረጭ መኖሩ ነው፡፡ የቀበሌ የሴቶች ስብሰባ--- የወጣቶች ስብሰባ-- የአብዮታዊ ንቃት ስብሰባ-- የመምህራን ስብሰባ--የመንግሥት ሠራተኞች ስብሰባ-- አጠቃላይ የቀበሌ ኗሪዎች ስብሰባ.... የስብሰባው ብዛት፡፡ አንዱም አይጥማትም፡፡ አንዱም ላይ መገኘት አትፈልግም፡፡ ግን ከአንዱም መቅረት አትችልም፡፡ በስብሰባ ቦታዎች ሁሉ

ብትገኝም በአካል እንጂ ምንጊዜም በሐሳብም-- በመንፈስም የለችም፡፡ የምትወያየው ከውስጧ ጋር ነው፡፡

«እንዲህ በስብሰባ ብዛት ከሚያደክሙን የአዲስ ዘመንን ተራራዎች ሁሉ ሲያስቆፍሩን ቢውሉ ይሻል ነበር፡፡ ለእርሻ አመቺ የሆነ ሜዳና ለም መሬት በፈጠርን ነበር፡፡ ለዚህ ለተራበ ሕዝብ የሚታፈስ ምርት ባመረትን ነበር» ትላለች ለራሷ እዚያው ስብሰባው ቦታ ከተሰብሳቢዎች መካከል ቁጭ ብላ፡፡ ከራሷ ጋር ምን የማታነሳ የማትትጥለው ጉዳይ አለ?

የእናት አገር ጥሪ መዋጮ-— ለቀይኮከብ ዘመቻ መዋጮ--- ለአረንጓዴው ዘመቻ መዋጮ..... የመዋጮው ብዛት ማለቂያ የለውም፡፡ ለአንዱም ማዋጣት አትፈልግም፡፡ አላዋጣም ማለት ግን አትችልም፡፡ ፀረ-አብዮተኛ ያሰኛል፡፡ እሷ ደግሞ ያደማችውን አብዮት የመካስ ግዴታ አለባት፡፡ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ታስራ የተፈታችው ያደማችዉን አብዮት ልትከስ ማህላ ፈጽማ ነው፡፡

በኢሕአፓ አባልነት ተመልምላ በሕቡዕ የሠራችባቸውን አጭር ጊዜያት ስታስብ ግርም ይላታል፡፡ ሰው ከሞት ጋር ትንቅንቅ ገጥሞ እንዴት እንደዚያ ተደሰች ይሆናል? በሕቡዕ ተሰብስባ ኢሕአፓ ያገኘቻቸውን ድሎችና የሠራቻቸውን ገድሎች ሰምታ ወደ ቤቷ ስትመለስ አቤ--ት! የነበራት ደስታ! ቃላት አይገልፀውም፡፡ ሕዝባዊ መንግስት መቋቋሙ አይቀሬ መሆኑን ስታሰብ ደግሞ የነበራት ውስጣዊ እርካታ! በስንት መሽሎክሎክና በስንት ጥንቃቄ በድብቅ የሚካሄደውን የስብሰባ ጊዜ በናፍቆት ነበር የምትጠብቀው፡፡ ጎንደር ሄዳ የተሰጣትን ማቴሪያል ይዛ ስትመጣ የነበረው ጭንቅ የቱንም ያህል ከባድ ቢሆን መጨረሻ ላይ ከተፈለገው ቦታ ደርሶ ስትመለከት ምን ያህል ደስታ—ምን ያህል የመንፈስ እርካታ ይሰጣት እንደነበር ይበልጥ የገባት አሁን ነው፡፡ ለዘለዓለም የማትረሳው-—ውስጧ የተቀበረ ልዩ ትዝታ! አሁን ግን ያ ሁሉ ቀርቶ እንጻራዊ በሆነ ሰላም እየኖረች ውስጧ ደስታ የለውም፡፡ ውስጧ ሰላም አላገኘም፡፡ ውስጧ አንድም ቀን እርካታ አግኝቶ አያውቅም፡፡ ሕይወቷ ከእሷ ፍላጎት ውጭ በሆነ ሌላ ዘዋሪ ኃይል የምትሽከረከር ይመስላታል፡፡ እናም መኖር ትርጉም የለሽ ይሆንባታል፡፡ ልጅ መውለዷና የቤተሰብ ሐላፊነት መሸከሟ በጃት እንጂ ሕይወት የበለጠ መራራና እሰጠሊታ በሆነችባት ነበር፡፡

«ሕይወት የሚጥመው ለዓላማ ሲኖሩ ነው፡፡ ያለዚያ እሰልቺ ይሆናል» ትላለች አዝውትራ፡፡ ዛሬም ኑሮ እጅ እጅ ብሏታል፡፡ ከሥራ እንደ ተመለሰች ከሠራተኛዋ በስተቀር ቤት ውስጥ ማንም አልነበረም፡፡ ቀጥታ ወደ መኝታ ከፍሏ ገባች፡፡ አልጋዋ ላይ ጥቂት ቁጭ ካለች በኋላ ወደ ኋላ ገለል ብላ በጀርባዋ ተኛች፡፡ እጇን ደረቷ ላይ አጣምራ ጣራ ጣራውን መመልከት ጀመረች፡፡ የመኝታ ቤቷ ጣርያ በላስቲክ ተሸፍኗል፡፡ ኮርኒስ መሆኑ ነው፡፡ በእበት የተለቀለቀው ግድግዳ እንዲሁ ዙሪያውን ላስቲክ ለብሷል፡፡ በስተምዕራብ በኩል ባለው የመኝታ ቤቷ መስኮት የማታ ፀሐይ ይገባል፡፡ ዐይኗን ወደ መስኮቱ ወርወር አደረገች፡፡ ውስጧ ይብለሰላል፡፡ የለየለት ሐሳብ ግን በአዕምሮዋ ውስጥ